# አዲስ ልሳን

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ADDIS MEDIA NETWORK

ቅጽ 32 ቁጥር 3535 | ቅዳሜ ነሐሴ 17 ቀን 2017 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር







# "የኮሪደር ልማቱ ለአፍሪካ ምሳሌ ሆኗል"

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

- አዲስ አበባን የማስዋብ ስራ በተገባው ቃል መሰረት መፈጸሙን ገልጸዋል

→ 3



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የመደመር መንግስት መፅሐፍን አስመልክቶ ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት

## ሆቴሎች እጃቸው ላይ ያለውን እድል እንዴት ሊጠቀሙት ተዘጋጅተዋል?

→ 6



ፎቶ- ከገፀ ድር

ባለ ኮከብ ሆቴሎች መገኛ በሆነችው ካዛንቺስ አካባቢ የተከናወነ የኮሪደር ልማት ከፊል ገጽታ

## በተግባር እየተገለጠ ያለው የትውልድ ድምፅነት

→ 5



ፎቶ- ከገፀ ድር

አቶ ጥላሁን ካሳ እና አቶ ዲዳ ድሪባ የስራ ስምምነት ሲያደርጉ

## የጥበብ ፋና ወጊው ሲታወስ

→ 12



ፎቶ- ከገፀ ድር

አርቲስት ደበበ እሸቱ "ሻፍት ኢን አፍሪካ" የተሰኘው ፊልም ላይ በሰራበት ወቅት



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡ የገበያ ማዕከላትን፣ የመኪና ማቆሚያዎችን እና ተርሚናሎችን ባስመረቁበት ወቅት

# "አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለጎብኚዎቿ ሳቢ ሆናለች"

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

**በሳህሉ በርሃኑ**

አዲስ አበባ ከተማ እንደ ስሟ እያበበች ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለጎብኚዎቿ ሳቢ ሆናለች ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ተናገሩ፡፡

ከንቲባ አዳነች ይህን ያሉት በትናንትናው ዕለት በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች የገበያ ማዕከላትን፣ የመኪና ማቆሚያዎችን

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ማንኛውም የሕዝብ አገልጋይ

"'ሀገሬ ይህን ካደረገችልኝ፤ እኔ ደግሞ የምችለውን ሁሉ ላድርግላት' በሚል ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል"

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ከፍተኛ ተመራማሪ ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር)

**በደረጀ ታደሰ**

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነሐሴ 12 ቀን 2017 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ፤ ከመስከረም 2018 ዓ.ም ጀምሮ ለመንግስት ሠራተኛው ተጨማሪ የደመወዝ ማሻሻያ ለማድረግ መንግስት መወሰኑን አሳውቋል፡፡ በመግለጫው ላይ እንደተጠቆመው፤ ይህ የደመወዝ ማሻሻያ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶችን በመሠረታዊነት ለመፍታት ሀገራችን እየተገበረቻቸው ባሉ ማሻሻያዎች የተያዙ ሁለት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል




# ርዕሰ አንቀፅ



## የደመወዝ ማሻሻያው የታለመለትን ግብ እንዲያሳካ ከወዲሁ መስራት ያስፈልጋል!

በኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶችን በመሠረታዊነት ለመፍታት ልዩ ልዩ ሪፎርሞች በመተግበር ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ሪፎርሞች ካነገቧቸው ሁለት ዓላማዎች መካከል የዛሬንና የነገን ትውልድ ጥያቄዎች በመመለስ፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና በአስተማማኝ መሠረት ላይ መገንባት አንዱ ነው፡፡ ትግበራው ውጤት እያመጣ ስለመሆኑ ግብርናው ሁነኛ ማሳያ ነው፡፡ ዘርፉ ላይ በተሰራው ስራ ስንዴን ከራስ ፍጆታ አልፎ ወደ ውጭ መላክ መቻሉ ደግሞ የዚህ አብነት ነው፡፡ በሌሎች ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ምሰሶዎች ላይም ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ትግበራውን ተከትሎ የሚፈጠረው ጫና በተለይም በቋሚ ገቢ በሚተዳደሩ የመንግስት ሰራተኞች ላይ ተፅእኖ ማሳደሩ ተጠባቂ ነው፡፡ መንግስትም ይኸንኑ አስቀድሞ ከግምት ያስገባ ዝግጅት በማድረግ የሰራተኛውን ብሎም በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደሩ ዜጎችን ጫና ለማቅለል እየሰራ መሆኑን በተደጋጋሚ እየገለፀ ነው፡፡ ሆኖም የሚወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች የመንግስትን አቅም የሚፈታተኑ ስለሚሆኑ ጥንቃቄ የተሞላባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የደመወዝ ማስተካከያም ከዚህ አንፃር ተመዝኖ የሚተገበር ነው፡፡

ከሰሞኑ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያወጣው መረጃ፣ መንግሥት ለደመወዝ የሚያውለው ከአጠቃላይ የመንግሥት ወጪ አንጻር ያለው ድርሻ ከ30 እስከ 32 በመቶ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ይህም ሆኖ በየዓመቱ ወደ አንድ መቶ ሺህ ገደማ እየጨመረ ካለው የመንግስት ሰራተኛ ቁጥር አንጻር ለእያንዳንዱ ሠራተኛ የሚከፈለው ወርሃዊ ደመወዝ አነስተኛ ነው፡፡

መንግስት ይህን ከግምት ባስገባ መልኩ የተለያዩ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፤ አሁንም በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ከሰሞኑ ከመስከረም 2018 ዓ.ም ጀምሮ ለመንግሥት ሠራተኛው የደመወዝ ማሻሻያ ለማድረግ መወሰኑ የተግባር አስረጂ ነው። ይህ ውሳኔ የመንግሥት ሠራተኛው የኑሮ ውድነቱን ጫና እንዲቋቋም በማድረግ ረገድ አበርክቶው ትልቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የደመወዝ ማስተካከያው ከ160 ቢሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ በጀት የጠየቀ፣ ለደመወዝ የሚወጣውን ጠቅላላ ዓመታዊ የመንግሥት ወጪ 560 ቢሊዮን ብር ያደረሰ መሆኑን ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም፡፡ ይህን እና መሰል ሰራተኛውን ተጠቃሚ የሚያደርጉ እርምጃዎቹን አጠናክሮ ለማስቀጠል ሀገራዊ ኢኮኖሚውን ጡንቻ ማፈርጠም ያስፈልጋል፡፡

ለዚህ የመንግስት ሰራተኛው ህዝቡን ያለመሰሰት ማገልገል ይጠበቅበታል፡፡ ከሙስናና ብልሹ አሰራር ራሱን ማራቅ፣ ሌሎችም እንዳይሳተፉ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ይገባዋል፡፡ በጥቅሉ ተቆጥሮ የተሰጠውን ብቻም ሳይሆን ከዚያ በላይ መስራት አለበት፡፡

የንግዱ ማህበረሰብም በኢኮኖሚው ውስጥ ምንም አይነት ምክንያታዊ ለውጥ ሳይኖር የሸቀጦችን ዋጋ ከማናርና የደመወዝ መጨመሩ ሊያስገኝ የሚችለውን የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም ትግበራ ሂደት መሳለጥ እንዲደናቀፍ ሳንካ ከመሆን መቆጠብ አለበት፡፡

መንግስት የሰራተኛውን ኑሮ ለማሻሻል ያሳየው ቁርጠኝነት በበጎ የሚታይ፣ የሚጠበቅም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርሙን በታለመለት ልክ በመተግበር የሰራተኛውን የመፈጸም አቅም ማሳደግ፣ ከዘርፉ የሚጠበቀው ውጤት እንዲመጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ ኃላፊነት በጎደለው መልኩ ሸቀጦች ላይ ዋጋ ለመጨመር በሚዳዳቸው ነጋዴዎች ላይ አስተማሪ የሆኑ እርምጃዎችን በመውሰድ የገበያውን ጤናማነት መቆጣጠር ለነገ የማይባል የቤት ስራ መሆን ይገባዋል፡፡ ሌሎች አካላትም የደመወዝ ማሻሻያ ውሳኔው አስፈላጊነትን በሚገባ በመረዳት ለትግበራው አቅም በሚሆን መልኩ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የደመወዝ ማሻሻያ የታለመለትን ግብ እንዲያሳካ ሁላችንም ኃላፊነታችንን እንወጣ!

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## የምስራቹ እንዳይበላሽ በጋራ እንከላከል!

**በወርቅነህ አለማየሁ**

ሰሞኑን የመንግስት ሰራተኞች የሰሙት ብስራት መቼም ድንቅ ነው፤ ‘የጎመን ድስት ውጣ የገንፎ ድስት ግባ’ የሚሉት ሰሞኑን ይመስለኛል። የጎመንን ድስት የሚቀይረው መስከረም መጥባቱ ብቻ ነው ብለን ካሰብን በአንዳንድ እጅ አጠሮች ዘንድ ስህተት ይሆንብናል። በመሆኑም ያቺን ድስት የሚቀይራት አንድም እንደተባለው ወቅቱ አንድም ደግሞ ኪሳችን ነው። ወዳጄ ኪስ ባዶ ከሆነ እንኳን ጎመን ቀርቶ ከጎመን በታችም ጥሬም ሊያስቆረጥም ይችላል። ለማንኛውም ይህ ብስራት የደመወዝ ማሻሻያው መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ታድያ “የመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ ማሻሻያ ይደረጋል” መባሉ የብዙዎችን ልብ ያሞቀ ዜና ሆኖ ከርሟል፡፡ ወደ ብዙሃኑ ቤትም ደስታን ይዞ የገባ የአዲስ ዓመት ዋዜማ ብስራት ነው። ነገር ግን ይህንን ደስ የሚል ዜና በሰማ ጆሮአችን ሌላ ደስ የማይል ነገር ሰምተን ስሜታችን እንዳይጎዳብን እሰጋለሁ። ምክንያቱም የብዙዎቹ የሀገራችን የነጋዴዎች ሁኔታ ‘ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ’ እንደሆነ ይሰማኛል፤ ስለዚህ የምስራቹ እንዳይበላሽ በጋራ እንከላከል እላለሁ፡፡

‘የእናት ሆድ ዥንጉርጉር’ እንደሚባለው በመልካም ጎኑ የሚወሱ ነጋዴዎች የመኖራቸውን ያህል ለጥቅማቸው ያደሩም አይጠፉም። ታድያ በዚህ የደመወዝ ማሻሻያ አሳብበው የሰራተኛውን አንጀት ‘የሚያሳርር’ የዋጋ ጭማሪ እንዳያደርጉ እሰጋለሁ፡፡

የደመወዝ ማሻሻያውን ተከትሎ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ ነጋዴዎች የዚህን ውሳኔ ዋና ዓላማ በማጣመም የዜጎችን በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ኑሮ የበለጠ አስቸጋሪ ሊያደርጉት ይችላሉ። እነዚህ ነጋዴዎች ለጊዜው የራሳቸውን ጥቅም ለማሳደድ ቢያስቡም፣ በመጨረሻ ግን የራሳቸውን ማህበረሰብ የሚጎዱ ናቸው። ይህ ድርጊት ከሞራል የራቀ ከመሆኑም በላይ በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል አሻጥር ነው።

የኑሮ ውድነትን የሚያባብስ የዋጋ ጭማሪ በህብረተሰቡ ላይ ኢ-ፍትሐዊ ጫና ይፈጥራል። ይህ ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ አለመግባባት፣ የሞራል ውድቀት እና ማህበራዊ ቀውሶች እንዲከሰቱ ያደርጋል። ስለዚህ እንደዚህ አይነት ጎጂ ድርጊቶችን ለመከላከል የሁሉም አካላት ትብብር ያስፈልጋል ባይ ነኝ።

በእርግጥ መንግስት እንዲህ ያለውን ድርጊት የሚፈፅሙ አካላትን እንደማይታገስና አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስድ ማስታወቁ ይታወሳል፡፡ ህብረተሰቡም እንዲህ ያሉ ድርጊቶችን ሲመለከት በፍጥነት ለመንግስት አካላት መጠቆም እና አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ማገዝ ይኖርበታል፡፡ ይህን ድርጊት መከላከል የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት መሆን እንዳለበትም ይሰማኛል። ምክንያቱም የዋጋ ጭማሪው ሁሉንም በእኩልነት ይጎዳል፡፡ ህብረተሰቡ አንድ ላይ በመሆን እነዚህን አሻጥሮች መከላከል የሚችሉበትን አቅም ማጠናከር አለበትም እላሉ።

መንግስትም የዜጎችን ጥቆማዎች በቁም ነገር መመልከት እና እርምጃ መውሰድ አለበት እላለሁ። የደመወዝ ማሻሻያው የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ያለመ በጎ ተግባር ነውና ይህንን በጎ ተግባር የራሳቸውን ጥቅም ብቻ በማሰብ የሚያበላሹ ነጋዴዎች ካሉ በህዝብ እና በሀገር ላይ የሚፈፅሙት በደል መሆኑን በመገንዘብ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ከመንግስት ጋር እጅ እና ጓንት በመሆን ድርጊቱን ለመከላከል የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበርክት እላለሁ።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
ከሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
አብርሃም ገብሬ
ሄለን ጥላሁን
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሰገነት አስማማው

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# “የኮሪደር ልማቱ ለአፍሪካ ምሳሌ ሆኗል”

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

- አዲስ አበባን የማስዋብ ስራ በተገባው ቃል መሰረት መፈጸሙን ገልጸዋል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የመደመር መንግስት መፅሐፍን አስመልክቶ ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት

**አዲስ አበባ ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ሀብት ሃምሳ በመቶውን ትይዛለች፡፡ ብዙ ንግድ፣ ኢንዱስትሪ እና ፈጠራ ያለባት ከተማ ናት**

**በመለሰ ተሰጋ**

“ከተሜነት የሰው ልጅ የብልጽግና መዳረሻ ነው፡፡” ይህን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ናቸው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመደመር መንግሥት በተሰኘው አዲሱ መጽሐፋቸው ዙሪያ ከፋና ሚዲያ ኮርፖሬሽን ጋር ባደረጉት ቆይታ፣ የመደመር መንግስት ለከተማና ከተሜነት ባለው መረዳት መሰረት ከተሜነት የሰው ልጅ የብልጽግና መዳረሻ መሆኑን ጠቅሰው፣ የኮሪደር ልማትን ጨምሮ ሌሎች መሰረተ ልማቶችን በማሟላት ለነዋሪው ምቹ ከተማን በመፍጠር ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ከተማ እና ከተሜነት ለሀገር ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ ድርሻ ስለሚይዝ የመደመር መንግስት የላቀ ትኩረት እንደሚሰጠውም አብራርተዋል። የከተሞችን እድገት በማጣጣል ብልጽግናን ማረጋገጥ እንደማይቻል ጠቁመው፣ የመደመር መንግስት ለገጠሩም ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እየሰራ ይገኛል፡፡ በኮሪደር ልማት በርካታ ዜጎች የስራ እድል ከማግኘታቸውም በላይ ለዝርፊያ እና ለተለያዩ ወንጀሎች ተጋላጭ የነበሩ ወገኖች ደህንነታቸው መረጋገጡን ገልፀዋል፡፡

በርግጥም “የከተሞችን እድገት በማጣጣል ብልጽግናን ማረጋገጥ አይቻልም” የሚለውን የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሀሳብ ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ አያሌ መረጃዎችን እና የሀገራትን ተሞክሮ መጥቀስ እንችላለን፡፡

ለዚህ ደግሞ በከተሞች ኢኮኖሚና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጥናታዊ ጽሑፎችን እና መፅሐፍትን ያሳተሙት ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ግላይዘር እ.ኤ.አ በጥር 31 ቀን 2012 “የከተሞች እውነት ወይም ድል” (Triumph of the City) የተሰኘው ጥናታዊ መፅሐፋቸው አንዱ ምስክር ነው፡፡

ፕሮፌሰር ኤድዋርድ በመፅሐፋቸው እንዲህ ይላሉ፤ ከተሞች የሀገራት ልብ ምት፣ የስልጣኔ መግቢያ በር፣ የምጣኔ ሀብት ርካብ፣ ቀን ነፍስና ስጋን ማስደሰቻ፤ ማታ ደግሞ ጨለማውን መርቻ የድል መቅረዝ ናቸው፡፡

ፕሮፌሰሩ በመፅሐፋቸው የከተማ ኑሮ መሻሻል፣ ምርታማነትን፣ ባህልን እና የሰው ልጆችን ደስታ ከፍ በማድረግ ለሀገራት ሁለንተናዊ ከፍታ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት አሁን በተምሳሌትነት የምንጠቅሳቸው የዓለም ሀገራት የዕድገታቸው ምስጢር የከተሞቻቸው ከፍታ እንደሆነ በተጨባጭ መረጃዎች እያጣቀሱ ገልፀዋል፡፡

ከተሜ መሆን ማለት ወደ ብልፅግና መቀራረብ ማለት መሆኑን የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይህም የሰው ልጆች ኑሮን ምቹ የሚያደርግ አገልግሎትን የሚያቀልል እና ነገሮች በተሻለ መንገድ የሚቀርቡበት ኑሮ ከተሜነት ነው፡፡ ለአብነትም ህክምና፣ ትምህርት እና ትራንስፖርትን ለማግኘት ቀላል፤ ብዙ ነገሮችም የዘመኑና ቀለል ያሉ ናቸው፡፡ ይህም የከተሜነት መገለጫ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ከተማና ከተሜነትን ይበልጥ ለመገንዘብ በአራት መነፅሮች እንመልከታቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የመጀመሪያው በማህበራዊ እይታ ነው፡፡ ይሄውም ከተሞች ቅይጥ ባህል መፈጠሪያ ማዕከላት ናቸው፡፡ በአንድ ከተማ ውስጥ ከዚህም ከዚያም ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነት ... ያለው ሰው ስለሚመጣ የቅይጥ ባህል መፍጠሪያ ማዕከል አድርገን የምንወስደው ከተሞችን ነው፡፡

ከተሜነት ደግሞ ስርዓት ያለው ህብር መፍጠሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ለአብነትም በትራንስፖርት፣ በቆሻሻ አወጋገድ፣ በአገልግሎት እና በልዩ ልዩ ነገሮች ስርዓት ባለው መንገድ በአንድነት እንዲፈስሱ የማድረግ ማህበራዊ አቅም እንዳለው ተናግረዋል፡፡

ሁለተኛው መነፅር ኢኮኖሚ ነው። ለአብነትም ከተሞች ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለስራ ፈጠራ እና ለቴክኖሎጂ ቅርብ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ የዓለማችን ከተሞች ያላቸው ሀብት ከአጠቃላይ የሀገር ሀብት ጋር ሲነፃፀር ለውድድር የሚበቃ አይደለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለአብነትም አዲስ አበባን ጠቅሰዋል፡፡

አዲስ አበባ ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ሀብት አምሳ በመቶውን ትይዛለች፡፡ ለዚህ ደግሞ ብዙ ንግድ፣ ኢንዱስትሪ እና ፈጠራ ያለባት ከተማ መሆኗን በምክንያትነት አንስተዋል፡፡ በመሆኑም ከተሜነት የላቀ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው ብለዋል፡፡

እድገትን የምናስብ ከሆነ ከተሞች ላይ ኢንዱስትሪን እና ፈጠራን ማስፋት አለብን፡፡ ምክንያቱም ኢንዱስትሪ ሰው ይፈልጋል፡፡ ሰው የምንቀጥር ከሆነ ደግሞ መኖሪያ ቤት ይፈልጋል፡፡ መኖሪያ ቤት ካለ በቂ ውሃ፣ መብራት፣ ጤና፣ ለልጆች ትምህርት ቤት እና መሰል አገልግሎቶችን እና መሰረተ ልማቶችን ይፈልጋል፡፡

ሦስተኛው መነፅር ፖለቲካ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከተሞች የዳበረ የፖለቲካ ስርአት መፍለቂያ ማዕከላት ናቸው፡፡ የፖለቲካ ስርአት ዳብሮና በስሎ ለሀገር በሚበጅበት መንገድ የሚታይበት አንዱ አውድ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ ከተሜነት ደግሞ ስልጣኔ፣ ውይይት እና ንግግር መፍትሔ ማምጫ ማዕከል ነው፡፡

አራተኛው መነፅር አካባቢያዊ ዕይታ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከተማ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ስርዓት ጋር ውስብስብ ስነ ምህዳር ውስጥ የሚኖርበት ነው፡፡ ለምሳሌ በገጠር ቆሻሻን ማስወገድ እንደ ከተማ ስርዓት ያለው ማስወገጃ ላይፈልግ ይችላል፡፡ በከተሞች ግን ከእያንዳንዳችን ቤት የሚወጣው ነገር በተንሰላሰለ መንገድ መጓዝ አለበት፡፡ በመሆኑም ከተፈጥሮ ስርዓቶች ጋር ውስብስብ ስነ ምህዳር መፍጠር ካልተቻለ ይበላሻል፡፡

ስለዚህ ከተሜነት የውበት፣ የጤናማነት እና የዘመናዊ አኗኗር ዘዬ መገለጫ መሆኑን ያብራሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ከተማን በመተው፣ በማናናቅ፣ በማራከስ የሆነ ስፍራ እሰራለሁ ብሎ በተናጠል ማሰብ ብልፅግናን እንደማያረጋግጥ በአፅንኦት ተናግረዋል፡፡

አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ ለማድረግ በታቀደው መሰረት ሰፋፊ ስራዎች መሰራታቸውን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአብነትም የሰው ልጆችን ኑሮ ምቹ ማድረግ፣ አገልግሎትን ማቅለል፣ ነገሮችን በተሻለ መንገድ ማቅረብና ማሟላት መሆኑን በመገንዘብ የከተሜነትን የኑሮ ዘዬ ለማስፋፋት እየተሰራ ነው፡፡ በዚህም ውጤት ተገኝቷል፡፡ አዲስ አበባን የማስዋብ ስራ ቃል ገብተን ፈፅመናል፡፡ ብልፅግና ከተማን ብቻ እያለማ ገጠርን የሚተው አይደለም በሁለቱም ጥሩ እና ውጤታማ ስራ እየሰራን እንገኛለን ብለዋል፡፡

ለዚህም በቅረቡ የሚመረቀው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የተጀመረው የገጠር ኮሪደር ልማት የሚያስደምም ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የአርሶ አደሩን ህይወት በብዙ የሚያዘምንና የሚያሻሽል ነው ይህም መንግስት ገጠርንም ያካተተ ዘላቂነት ያለው ስራ እያከናወነ ስለመሆኑ ማሳያ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የኮሪደር እና የወንዞች ዳርቻ ልማት በምናባዊ እይታ በብዙ መትጋት የመጣ ለውጥ፣ በተለያየ መልኩ ለአፍሪካውያን ከተሞች ተምሳሌት የሆነ እና ሀገርን የሚያኮራ ስራዎች የተሰሩበት እንደሆነም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አብራርተዋል፡፡

በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ጀማ ሀጂ እንደሚሉት በአዲስ አበባ ተጀምሮ ወደ ሌሎች ከተሞች በመስፋፋት አስደናቂ የከተሞች ለውጥን እያሳየ ያለው ኮሪደር ልማት በከተሞች መካከል የትብብር መንፈስን ያበረታታል፤ ለተሻለ የኑሮ ሁኔታ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና ለዘላቂ እምርታ ትልቅ መሰረት የሚጥል ነው፡፡ እንዲህ አይነት ልማት በተለይም አሁን ያለው ብቻ ሳይሆን መጭው ትውልድ በተጎሳቆለ አካባቢና ሁኔታ ውስጥ ሕይወቱን በአስቸጋሪ መልክ እንዳይገፉና ደስተኛ ሆኖ የሀገሩን ከፍታ እንዲያስቀጥል ትልቅ አበርክቶ አለው፡፡ ዓለም አቀፍ እውነታውም የሚያሳየው ይህንኑ ነው ብለዋል፡፡

ፕሮፌሰር ጀማ ሀጂ በገለፃቸው፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከአዲስ አበባ ጀምሮ በኮሪደር እና በወንዞች ዳርቻ ልማት ከተሞችን ማስዋብ፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ምቹ ማድረግና አዳዲስ የመስህብ ስፍራዎችን የመገንባት ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ ይህንን ስራ እያዩ እንደ ሰው በተቃራኒው መቆም አይቻልም። ለአብነትም አዲስ አበባ ተለውጣለች፤ ይህንንም ዐይተን እየመሰከርን ነው ብለዋል፡፡

በከተማዋ እየመጣ ያለው ለውጥም “ለካ በሀገራችን እንዲህ አይነት ነገር መስራት ይቻላል? እኛም ማድረግ እንችላለን?” የሚል ስሜትን የሚፈጥር ነው፡፡ እነዚህ ተግባራት የከተማዋን ኢኮኖሚ በማነቃቃት እንደ ሀገር የሚኖራቸው ድርሻ ከፍ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም በዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንዲቀጥል ሁሉም ዜጋ ይህንን ልማት በተለያዩ መንገዶች ማገዝ ይኖርበታል ሲሉ አክለዋል፡፡

በርግጥም ከተማዋን ከስልጡን የዓለማችን ከተሞች ተርታ ለማሰለፍ እየተሰሩ ባሉ የኮሪደር ልማት ስራዎች አዲስ አበባ በትክክልም አዲስም፣ አበባም እየሆነች መምጣቷን በተከታታይ እየተከናወኑ ያሉ ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ታላላቅ ጉባኤዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም ከቦሌ እስከ መገናኛ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ፒያሳ፣ ከፒያሳም በቸርቸር ጎዳና ወደ ሜክሲኮ፣ ከስድስት ኪሎም እስከ እንጦጦ. . . ቢያሻን በመኪና ቢለንም በእግር ዘወር ዘወር ብንል ልማቱ እራሱ ይናገራል፡፡

# ማስታወቂያ



## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በዋና ስራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ግዥ አስተዳደር ቡድን የ2018 በጀት ዓመት ከዚህ በታች በሎት የተጠቀሱትን ዕቃዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ሎት 1 አላቂ የቢሮ እቃዎች

ሎት 2 ቋሚ የቢሮ እቃዎች

ሎት 3 የደንብ ልብስ እና የፅዳት እቃዎች

ሎት 4 የ ምግብና መጠጥ መስተንግዶ

ሎት 5 የትራንስፖርት ኪራይ

ሎት 6 የህትመት ስራዎች እና የመድረክ ስራዎች

ሎት 7 የቢሮ ማሽኖች ጥገና አገልግሎት

ሎት 8 የቢሮ መገልገያ እቃዎች ጥገና

ሎት 9 የእንስሳት መድኃኒት የጓሮ አትክልት ዘር እና እንቁላል ጣይ ዶሮ

ሎት 10 የመኪና ጎማና ጌጣጌጦች

ሎት 11 የተለያዩ የጉልበት ስራዎች

በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ጨረታውን ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ከተ.ቁ 1-3 የተዘረዘሩትን በማሟላት መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ እና በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ
2. የግብር ከፋይነት (tin number) ማቅረብ የሚችሉ
3. ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስረከቢያ ሎት 1 5,000.00 ብር ሎት 2 500,000.00 ብር ሎት 3 ብር 5,000.00 ብር ሎት 4 12,000.00 ብር ከሎት 5 እስከ ሎት 12 ብር 10,000.00 ብር በCPO ማስያዝ ይኖርባቸዋል
5. ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር የያዘ ሰነድ የማይመለስ 250.00(ሁለት መቶ ሀምሳ ብር) በመክፈል ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ10(አስር) ተከታታይ የሥራ ቀናት ሆኖ የጨረታው ሰነድ ዘወትር በሥራ ሰዓት ሃይሌ ጋርመንት ላፍቶ አደባባይ በሚገኘው የክፍለ ከተማው ህንጻ ዘጠነኛ ፎቅ በመቅረብ መግዛት ይኖርባቸዋል ፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያውን ዋጋ በመሙላት እና ከተ.ቁ 1-4 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ኦርጅናልና ኮፒ በማሸግ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 10(አስር) የስራ ቀናት እስከ ቀኑ 11፡30 ሰዓት ድረስ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል በ 10ኛው ቀን 11፡30 ሰዓት ሳጥኑ ይታሸጋል፡፡
7. ጨረታው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግልጽ ይከፈታል
8. የጨረታው አሸናፊ ለመልካም አፈጻጸም (ለውል ማስረከቢያ) ያሸነፉበትን ዋጋ 10% ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
9. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

- ተጫራቾች ለሚኖራቸው ጥያቄ በስልክ ቁጥር 011-8-34-27-15 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት የአስተዳደርና ፋይናንስ ቱል**

---

አቶ ሌ/ፍ አዲሱ ከበደ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የካርታ ቁጥር ቦሌ03/304/64-2684/00 ሴሪ ቁጥር 033320 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ዶ/ር ማሩ አረጋዊ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የካርታ ቁጥር 5855 ሴሪ ቁጥር 013112 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአለም በላይ መሰለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA000080203873570004 በሴሪ ቁጥሩ 084604 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የጨረታ ማስታወቂያ

ድርጅታችን ኪቢሽ ኮንስትራክሽን በተለያዩ ፕሮጀክቶች ያሉ የአስፓልት ሬንጅ በርሜሎችን በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

**1. ቡልቡላ አላጌ ከአዲስ አበባ (185 ኪ.ሜ)**

| ተ.ቁ | የበርሜል አይነት | መለኪያ | ብዛት | የሚገኙበት ፕሮጀክት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 60/70 | ቁጥር | 7497 | ቡልቡላ አላጌ መንገድ ስራ ፕሮጀክት |
| 2 | 80/100 | ቁጥር | 1428 | |
| 3 | MC-30 | ቁጥር | 1498 | |
| 4 | የዘይት | ቁጥር | 120 | |
| | | ድምር | 10,543 | |

**2. ሚዛን ቴፒ (ግዝ መሬት ከዩኒቨርሲቲው 35 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል)**

| ተ.ቁ | የበርሜል አይነት | መለኪያ | ብዛት | የሚገኙበት ፕሮጀክት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 60/70 | ቁጥር | 867 | ሚዛን ቴፒ (ግዝ መሬት) ከዩንቨርሲቲው 35 ኪሎ ሜትር ርቀት |
| 2 | MC-30 | ቁጥር | 80 | |
| | | ድምር | 947 | |

**ማሳሰቢያ**

1. የበርሜሎችን ሁኔታ በቦታው በመገኘት ማየት የሚቻል ሲሆን ዝርዝሩን የያዘ የጨረታ ሰነድ በዋናው መስሪያ ቤት መውሰድ ይቻላል፡፡
2. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ሠነድ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በሲፒኦ በማስያዝ ከጨረታ ሰነዱ ጋር በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ከ ነሀሴ/19 ቀን እስከ ነሀሴ/29 ቀን 2017 ዓ.ም ጠዋት 4፡00 ሰዓት ድረስ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
3. ጨረታው ነሀሴ 30 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት ግቢ ውስጥ ይከፈታል፡፡
4. ጨረታውን ሲጫረቱ የሚጫረቱበትን ቦታ ለይተው ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. አሸናፊ ተጫራች የጨረታው ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር (10) የስራ ቀናት ውስጥ ቀሪ ክፍያቸውን ከፍለው ንብረቱን ያነሳሉ፡፡ ንብረቱን ማንሳት ካልቻሉ በዋስትና ያስያዙት ገንዘብ ገቢ ተደርጎ ጨረታው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡
6. የአሸናፊ ተጫራቾች ዝርዝር በማስታወቂያ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ሌሎች ተጫራቾች ያስያዙትን ገንዘብ የከፈሉበትን ኦርጅናል ደረሰኝ በማቅረብ ተመላሽ ማድረግ ይችላሉ፡፡
7. ድርጅቱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
8. የበርሜሉ መጠን ከተጠቀሰው ቁጥር ሊያንስ ወይም ሊበዛ ይችላል፤ በመጨረሻ ቀን በተገኘው ነጠላ ቁጥር ይፈፀማል፡፡

**ለበለጠ መረጃ Tel- 011-4-70-19-54 ወይም 09-12-21-83-79 ይደውሉ**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 5 ክልል ውስጥ በግሎባል ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ስም በካርታ ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ሊዝ/127/99/1 ሴሪ ቁጥር 0128802 በሆነ የተመዘገበው ለድርጅት አገልግሎት የሚውል ይዞታ፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጇ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወረዳ 11 ሽሮ ሜዳ ጤና ጣቢያ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር- ካርታ ቁጥር 40678 ተመዝግቦ በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## “አዲስ አበባ ... ከገጽ 1 የዞረ

እና ተርሚናሎችን መርቀው ለአገልግሎት ክፍት ባደረጉበት ወቅት ነው፡፡

ከንቲባዋ በዕለቱ ባደረጉት ንግግር “በቀድሞዋ አዲስ አበባ ይከናወኑ የነበሩ በጣት የሚቆጠሩ ዓለም አቀፍ ኩነቶች በመጡ ቁጥር የከተማዋን የተጎሳቆሉ ገፅታዎች፣ የተበከሉ አካባቢዎች፣ አንገት አስደፊ ገፅታዎች በጥቅሉ ገመናችንን ሌሎች እንዳያዩት በረጃጅም ባነር የመሸፈን ታሪክ በልጆቿ የሌት ተቀን ትጋትና በነዋሪዎቿ ትብብር ታሪክ ሆኗል።” ብለዋል፡፡

የተመረቁት ፕሮጀክቶች በከተማዋ የመንገድ ትራፊክ መጨናነቅ በነበረባቸው እና የቆሸሹ እና የተጎሳቆሉ ቦታዎችን በማጽዳት እና የትራፊክ እንቅስቃሴውን ማሳለጥ የሚያስችሉ እና የስራ እድልን ጭምር የሚፈጥሩ መሆናቸውን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገልጸዋል።

በአራዳ፣ በሜክሲኮ፣ በለገሀር እና ሳር ቤት የአፍሪካ ህብረት አካባቢ የሚገኙና የከተማዋን ገፅታ ይበልጥ የሚያሻሽሉ፣ ለወጣቶችና ሴቶች ሰፊ የስራ ዕድል የሚፈጥሩ፣ የትራፊክ ፍሰቱን እሚያሳልጡ፣ የሚያዘምኑ፣ የአካባቢዎቹን ውበት የሚጨምሩ ፕሮጀክቶችን ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መርቀን ለአገልግሎት ክፍት አድርገናልም ሲሉም ተናግረዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡ የገበያ ማዕከላትን፣ የመኪና ማቆሚያዎችን እና ተርሚናሎችን ባስመረቁበት ወቅት

ከሜክሲኮ እስከ ለገሀር ባለው አካባቢ ብቻ 2 ሺህ 145 ተሽከርካሪዎችን በአንድ ጊዜ ማቆም የሚችሉ 13 የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች እና 1 ሺህ 624 ታክሲና አውቶብስ በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችሉ መጫኛ እና ማውረጃዎች ለአገልግሎት ክፍት ተደርገዋል፡፡

የአፍሪካ ህብረት የገበያ ማዕከልና ፓርኪንግ ለዲፕሎማሲው ማህበረሰብ የተለያዩ የስጦታና የባህል መሸጫዎችን በአቅራቢያው እንዲያገኙ የሚያስችሉ ሲሆን፣ በ28 ሺህ 500 ሜትር ስኩር ላይ የተገነባ ዘመናዊ ማዕከል ነው፡፡ ሁለት ቤዝመንትና ፕላዛ፣ 250 ሱቆች እና 250 መኪኖችን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚያስችል፣ በተጨማሪም የህጻናት መጫወቻ እና ማረፊያዎች፣ 45 መጋዘንና የመጸዳጃ ክፍሎች፣ ፋውንቴን፣ አምፊ ቴአትር እና ፕላዛ በውስጡ ይዟል።

ሌላኛው ባሻ ወልዴ ችሎት ጋር የተሰራው ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያና ገበያ ማዕከል ሲሆን፣ በተመሳሳይ ካፍቴሪያዎች፣ ሱፐርማርኬት፣ ሱቆች፣ ሬስቶራንቶች፣ ፕላዛ እና 200 የመኪና ማቆሚያ በውስጡ የያዘ ነው። ሁለቱም ማዕከላት ዘመናዊ የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያና የደህንነት ካሜራ የተገጠመላቸው ሲሆን፣ ለህፃናት፣ ለአቅመ ደካሞችና አረጋውያን ምቹ ሆነው የተሰሩ ስለመሆናቸው ተገልጿል፡፡

በጥቅሉ ከሜክሲኮ እስከ ለገሀር እና አፍሪካ ህብረት ዙሪያ ባሉ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ 13 የመኪና ማቆሚያና፣ 10 ተርሚናሎች እስከ 3 ሺህ 769 ተሽከርካሪዎችን ማስተናገድ የሚችሉ የፓርኪንግ እና ተርሚናል መሰረተ ልማቶች ጭምር ይገኙበታል ተብሏል።

የተሽከርካሪ ማቆሚያዎቹና የታክሲና የአውቶብስ መጫኛ እና ማውረጃዎቹ 300 የሚደርሱ ሱቆች፣ 50 መጋዘኖች፣ 80 የሚደርሱ መጸዳጃ ቤቶች፣ የደህንነት ካሜራዎች፣ ከአንድ ማዕከል ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የተሟሉላቸው ናቸው፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ባስተላለፉት መልዕክት፣ እነኚህ ለከተማዋ እድገት ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶች በታለመላቸው ጊዜ እና በጀት እንዲጠናቀቁ ሌት ተቀን ለደገፉ አመራሮች፣ ባለሙያዎችና የአካባቢው ማህበረሰብ ልባዊ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ከተሽከርካሪ ማቆሚያዎች እና የገበያ ማዕከላት በተጨማሪ የታክሲና የአውቶብስ መጫኛ እና ማውረጃዎች ተመርቀው ስራ የጀመሩ ሲሆን፣ በዚህ ክረምት ወደ 19 ሺህ የሚጠጉ ፕሮጀክቶች ተገንብተው ወደ አገልግሎት እየገቡ ስለመሆኑ ተነግሯል፡፡

በቅርብ ጊዜም በመዲናዋ 4 ኪሎ ፕላዛ፣ 4 ኪሎ የገበያ ማዕከል እና መኪና ማቆሚያ ተመርቆ ለአገልግሎት ክፍት መደረጉ ይታወሳል። ፕሮጀክቱ ከመሬት በታች የተገነቡ እጅግ ዘመናዊ 102 የስጦታ እና የአልባሳት መደብሮች፣ ካፍቴሪያዎች፣ ማንበቢያ ስፍራዎች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ ከ100 በላይ ተሽከርካሪዎችን በአንድ ጊዜ የሚያስተናግድ የመኪና ማቆሚያ እና በአንድ ጊዜ እስከ 5 ሺህ ሰዎችን መሰብሰብ የሚያስችል የፕላዛ፣ የአንፊ ቴአትርና የተለያዩ የጥበብ ስራዎችን ማቅረቢያ ስፍራዎችን የያዘ እና ከወዲሁ ከ500 በላይ ለሚሆኑ ወጣቶችና ሴቶች የስራ ዕድል የፈጠረ እንደሆነም ይታወቃል፡፡

# በተግባር እየተገለጠ ያለው የትውልድ ድምፅነት

- **አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የከተማዋን ትናንት በወጉ ሰንዶ፣ ዛሬዋን በልኩ ቀምሮ ነገዋን አሻግሮ በመመልከት ከፍታዋን ለማስጠበቅ እየሰራ መሆኑ ተመላክቷል**

**በመለሰ ተሰጋ**

አዲስ አበባ ትናንትን፣ ዛሬን እና ነገን አሻግረው በሚያሳዩ አስደማሚ ህንፃዎች፣ በታሪካዊ ስፍራዎች እና በልዩ ልዩ ቅርሶች ያሸበረቀች ውብ ከተማ ናት። ወዲህ ደግሞ ኢትዮጵያውያን የሚያምር ማንነታቸውን በጠንካራ አንድነታቸው ሸምነው በፍቅር የሚኖሩባት ማዕከል ናት፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ደግሞ በህትመት፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን እንዲሁም በማህበራዊ ሚዲያ አውታሮቹ እንደ ስሟ እየፈካች ያለችውን ከተማ፣ ትናንቷን በወጉ ሰንዶ፣ ዛሬዋን በልኩ ቀምሮ ነገዋን አሻግሮ በመመልከት ከፍታዋን ለማስጠበቅ እየሰራ ነው። በስራው ጥራትን፣ ፍጥነትን እና የላቀ አክብሮትን ምርኩዝ አድርጎ ሰላምና ልማትን፣ ተዝናኖት እና ቁም ነገርን በየፈርጁ እየከሸነ የትውልድ ድምፅነቱን እያስመሰከረ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በቅርቡ በከተማም ሆነ በሀገራዊ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ባሳየው ትጋት ያገኛቸው እውቅናና ሽልማቶች ምስክር ናቸው፡፡

በእርግጥም እንደ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ያሉ ተቋማት ከተሞች ከስልጣኔ ጋር እንዲወዳጁ፣ የብዝሃነት ማዕከልነታቸው ለዛና ውበቱን ጠብቆ እንዲቀጥል፣ ያለፈውን በትውስታ፣ ያለውን በጥበብ እንዲሁም መጭውን በተስፋ እያስዋቡ ለመጓዝ ያላቸው ድርሻ ከፍ ያለ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ምክትል ስራ አስፈጻሚና የቴሌቪዥን ዘርፍ ኃላፊ አቶ ጥላሁን ካሳ ከከተማዋ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ዲዳ ድሪባ ጋር የስራ ስምምነት ሲያደርጉ

ለዚህ ደግሞ የሊድስ ዩኒቨርሲቲ የሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ቤት ተባባሪ ፕሮፌሰሯ ጆርጂያ አይኤሎ፣ በጄኔቫ ዩኒቨርሲቲ ተባባሪ ፕሮፌሰር ማትዮ ታራንቲኖ እና በሊድስ ዩኒቨርሲቲ የሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ቤት የባህል ፖሊሲ ፕሮፌሰር ኬት አክሌይ በጋራ ባሳተሙት “Communicating the City” የተሰኘውን መፅሐፍ በአስረጂነት ማቅረብ ይቻላል፡፡

በመፅሐፉ ላይ በሰፈረው ሀሳብ መሰረት በአስደማሚ ውበትና ጥበብ፣ ከከተሞች የህንፃ፣ የመንገድ እና መሰል መሰረተ ልማቶች እንዲሁም ብዝሃ መገለጫ ያላቸው ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩነታቸውን እንደ ውበት ደምቀውበት አንድነታቸውን ደግሞ ለሁለንተናዊ ከፍታቸው እንደ ብርቱ ምሰሶ ተጠቅመውበት እንዲኖሩ ለማስቻል ከምንም በላይ የሚዲያ ጉልበት ከፍ ያለ ነው፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በከፍተኛ የለውጥ ምዕራፍ ውስጥ ይገኛል፡፡ ዋርካና አገልጋይን በመሳሰሉ የቴሌቪዥን፣ የህትመት፣ የሬዲዮ እና የማህበራዊ ሚዲያ ስራዎቹ ወደ ህብረተሰቡ ልብ የቀረበ በመሆኑ በየጊዜው ተወዳጅነቱና ተመራጭነቱ እየጨመረ በመምጣቱ ከተለያዩ ተቋማት “የአብረን እንስራ” ጥያቄዎች እየቀረቡለትና ስምምነቶችንም በየጊዜው በማድረግ ላይ ነው፡፡

ለአብነትም ባሳለፍነው ሐሙስ በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የተደረገው ስምምነትን በዋቢነት መጥቀስ እንችላለን፡፡ ስምምነቱ በተደረገበት ወቅትም የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ እና የቴሌቪዥን ዘርፍ ኃላፊ አቶ ጥላሁን ካሳ፣ ሚዲያው የተለያዩ የልማት እና መሰል ሀገርን እና ማህበረሰብን የሚጠቅሙ ስራዎች የጋን ውስጥ መብራት ሆነው እንዳይቀሩ ትልቅ ሚና አለው ብለዋል፡፡

በመሆኑም ከተቋሙ ጋር የተደረገው ስምምነት በቴሌቪዥን ብቻ ሳይሆን በአንጋፋዋ አዲስ ልሳን ጋዜጣ፣ በኤፍ.ኤም 96.3 እንዲሁም በማህበራዊ ሚዲያው በኩል ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር አብረን እንሰራለን ያሉት አቶ ጥላሁን፣ ሁለቱ ተቋማት በቤተሰብነት አብረው እንደሚሰሩ ጠቁመዋል፡፡ አክለውም፣ ስራዎቹን ከማስተዋወቅ ባሻገርም የትውልድ ድምፅ የሆነው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ሚዲያ አቅም ያለው በመሆኑ ሌሎችም እንደ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በመምጣት ልምድ የሚወስዱበትንም ዕድል የሚፈጥር ስምምነት እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዲዳ ድሪባ በበኩላቸው፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ስለ አካባቢ ጥበቃ ልምድና ዕውቀት ያላቸውን ምሁራን በመጋበዝ የተሰሩ ስራዎች በተሻለ ሁኔታ ለህዝብ ጆሮ የሚደርሱበት እና የአካባቢ ጥበቃ ዘመን መሆኑን የሚያሳይ እንዲሁም መንግስት ለአካባቢ ጥበቃ በሰጠው ትኩረት ልክ ሚዲያው ሽፋን እንደሚሰጠው እናምናለን ብለዋል። አክለውም፣ ፅዱ ኢትዮጵያን ባህል እናድርግ የሚለው ንቅናቄ ውጤታማ እንዲሆን አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለውም መስክረዋል፡፡

ከዚህ በፊትም አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እና የከተማዋ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ፣ ስራና ክህሎት ቢሮ፣ ትምህርት፣ ትራንስፖርትና በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን ስምምነት መፈራረማቸው ይታወሳል፡፡

ሚዲያው ከተቋማት ጋር በአደረጋቸው ሌሎች ስምምነቶች መካከል የአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ ጋር ያደረገው ስምምነት የሚታወስ ነው፡፡ ተቋማቱ በጋራ ለመስራት የተስማሙት “የሚሰሩ እጆች ወግ” የተሰኘ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሲሆን፣ የስራ ባህል ለማዳበር ብሎም በቂ የስራ ዕድል የሚፈጠርበትን መደላድል መፍጠርን ያለመ ስለመሆኑም በተፈራረሙበት ወቅት መገለፁ ይታወሳል፡፡

# ሆቴሎች እጃቸው ላይ ያለውን እድል እንዴት ሊጠቀሙት ተዘጋጅተዋል?

- ከ25 ሺህ በላይ ታዳሚዎች የሚሳተፉበት የአየር ንብረት ጉባኤ በአዲስ አበባ ሊካሄድ ነው

**በሳህሉ በርሃኑ**

የዓለም አቀፍ ጉባኤዎችና ኮንፈረንስ ቱሪዝም ዘርፍ እጅግ ግዙፍና በፍጥነት እያደገ ያለ ኢንዱስትሪ ነው። ይህ ዘርፍ በተለያዩ ጥናቶች ስር ‘MICE’ (Meetings, Incentives, Conferences and Exhibitions) ወይም “የቢዝነስ ዝግጅቶች” በመባል ይታወቃል። ኢቨንት የተሰኘ ገፀ ድር እ.ኤ.አ በ2024 ማይስ ምንድን ነው? (What Is MICE? ) በሚል ርዕስ ባስነበበው መረጃ፣ የዓለም አቀፍ የማይስ ኢንዱስትሪ ገቢ ከ1 ነጥብ 1 ትሪሊዮን ዶላር በላይ እንደነበር አስፍሯል። ይህ ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዶ እስከ 2032 ድረስም ወደ 2 ነጥብ 4 ትሪሊዮን ዶላር ሊደርስ እንደሚችል ትንበያው አስቀምጧል።

ይሁንና ዓለም በዚህ ደረጃ ከዘርፉ የሚገባውን እየተቋደሰ ቢሆንም አህጉረ አፍሪካ ግን የሚገባትን ያህል እየሰራችም እየተጠቀመችም አለመሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የዓለም አቀፍ ኮንግረስ እና ኮንቬንሽን ማህበር (ICCA) መረጃም የሚያሳየው ይህንኑ ነው፡፡ የተቋሙን መረጃ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት አህጉሪቱ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ማህበራት ስብሰባዎች ከገቢ አንጻር ያላት ድርሻ ከ10 በመቶ ያነሰ ነው፡፡

ከዚህ ቀደም ከተለመዱ ውስን ጉባኤዎች በእጥፍ የላቁ ዓለም አቀፍ ኩነቶችን በስኬት በማስተናገድ ላይ የምትገኘው አዲስ አበባ ይህንን የአህጉሪቱን መልክ ለመቀየር እየጣሩ ካሉ ከተሞች በቀዳሚነት ትጠቀሳለች፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደሚገልጹትም መዲናዋ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ያህል ጎብኚዎች የተሳተፉበትን 150 ዓለም አቀፍ ኩነቶችን በከፍተኛ ስኬት አስተናግዳለች። በዚህም 143 ቢሊዮን ብር ያህል ሀብት ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ገቢ ሆኗል።

ይህ የገቢ ስሌት ታዲያ ለጉባኤዎቹ ከሚከፈለው ቀጥተኛ ክፍያ በተጨማሪ፣ ተሳታፊዎች በቆይታቸው የሚያወጡት ወጪን ጭምር ሲሆን፣ በተለይም ጉባኤው በሚካሄድበት ከተማ የሚገኙ ሆቴሎችና የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ሆቴሎች፣ ካፌዎች እና ሌሎች ተቋማት የሚያገኙትን ገቢ ያካትታል፡፡ እንደዚሁም ጉባኤውን ተከትሎ ተሳታፊዎች ለግል ግብይትና ለሌሎች መዝናኛዎች የሚያወጡት ገንዘብን ጨምሮ እንደሆነ ልብ ይሏል።

በመጪዎቹ የዳጉሜ እና የመስከረም ወራት ደግሞ መዲናዋ የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ሳምንት፣ 2ኛው የአፍሪካ የአየር ንብረት ጉባኤ፣ 2ኛው የካረቢያን እና አፍሪካ መሪዎች “ካሪኮም” ጉባኤን ታስተናግዳለች፡፡ ይህንንም ተከትሎ ከ25 ሺህ በላይ ታዳሚዎች የሚሳተፉበት የአየር ንብረት ጉባኤ ለማስተናገድ በዝግጅት ላይ ትገኛለች፡፡ የምስራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ የህገ ወጥ ገንዘብ ዝውውር ወንጀልን መከላከል ቡድን ዓመታዊ ጉባዔ ደግሞ ከነሐሴ 16 እስከ ነሐሴ 24 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ይካሄዳል፡፡ ለመሆኑ እንደዚህ አይነት ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን ማስተናገድ ለመዲናዋ ያለው ትርጉም ምንድነው? በተለይም በመዲናዋ የሚገኙ ሆቴሎች እድሉን ለመጠቀም ምን ያህል ተዘጋጅተዋል? የሚሉና መሰል ጉዳዮችን መፈተሽ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡



ባለ ኮከብ ሆቴሎች መገኛ በሆነችው ካዛንቺስ አካባቢ የተከናወነ የኮሪደር ልማት ከፊል ገጽታ

ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከሆቴል ኢንዱስትሪ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በቅድመ ዝግጅት ስራዎች ዙሪያ ውይይት ባካሄዱበት ወቅት እንደገለፁት ባለፉት የለውጥ ዓመታት ለዘርፉ ልማት የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት አመላክተዋል፡፡ የሀገራት መሪዎችን፣ የዓለም አቀፍ ተቋማትን፣ የአየር ንብረት ተመራማሪዎችን፣ ዓለም አቀፍ የሚዲያ አካላትን ጨምሮ ከ25 ሺህ በላይ ታዳሚዎች የሚሳተፉበት የአየር ንብረት ጉባኤ በመዲናዋ መካሄድም መንግስት ለዘርፉ ትኩረት ስጥቶ የመስራትን ተገቢነት የሚያረጋግጡ ማሳያዎች ናቸው ብለዋል።

አክለውም ለውጤቱ መመዝገብ አዲስ የተገነቡ፣ የታደሱ ነባር የቱሪዝም መሰረተ ልማቶች፣ የከተማዋ ነዋሪዎች የእንግዳ ተቀባይነትና ተባባሪነት፣ የግሉ ዘርፍ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የመንግስት የተናበበ ቅንጅት ጉልህ ድርሻ እንዳላቸውም እንደዚሁ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አንስተዋል።

ሆቴሎች የቱሪዝም ዘርፍ ዋነኛ አካል ስለመሆናቸው የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡ በደቡብ አፍሪካ በስቴለንቦሽ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጥናት ትምህርት ክፍል የቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያ ሮኒ ዶናልድሰን እንደሚሉትም ሆቴሎች ለሀገሪቱ ባህልና ቅርስ ትልቅ ማስተዋወቂያ መድረክ ሆነው ያገለግላሉ። ብዙ ሆቴሎች የሀገራቸውን ባህላዊ ምግቦችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ የሀገርን ማንነት ለውጭ ጎብኚዎች ያስተዋውቃሉ። ይህም የባህል ቅርሶች እንዲጠበቁና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዲኖራቸው ይረዳል፤ በዚህም የሀገርን ታሪካዊና ባህላዊ ቅርስ የመጠበቅና የመንከባከብ ሥራ ይደገፋል።

ከዚህ አንጻር ሲመዘን በቅርቡ በአዲስ አበባ የሚከናወነው የአየር ንብረት ጉባኤ በከተማዋ ለሚገኙ ሆቴሎች በአንድ በኩል ትልቅ ኃላፊነት የሚሰጥ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ትልቅ እድል እንደሚፈጥር እሙን ነው፡፡ ከ25 ሺህ በላይ ሰዎች በአንድ ጊዜ ወደ ከተማዋ ሲመጡ ለመኝታ፣ ለመመገቢያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ያለው ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል። የጉባኤው ተሳታፊዎች በቆይታቸው ሆቴሎች ሙሉ በሙሉ የመያዝ ዕድል አላቸው። ይህም ከኪራይ ገቢ በተጨማሪ በምግብና በመጠጥ አገልግሎቶችም የላቀ ጥቅም ያስገኛል። ከዚህም ባሻገር፣ ጉባኤው ከተማዋን እንደ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች እና ኤግዚቢሽኖች (MICE) መዳረሻነት እንድትታይ ያደርጋታል። ይህም በቀጣይነት ሌሎች ተመሳሳይ ትላልቅ ጉባኤዎችን ለመሳብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

አዲስ አበባ ከዚህ በፊትም የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችንና የዩኒየን ጉባኤዎችን በተደጋጋሚ አስተናግዳለች። ከእነዚህ ልምዶች መረዳት እንደሚቻለው በጉባኤ ወቅት የሚስተናገዱ እንግዶች ለሆቴሎች የገንዘብ ፍሰት ከመፍጠራቸው በተጨማሪ፣ ዘላቂ የንግድ ግንኙነቶች እንዲመሰረቱ ያግዛሉ። በርካታ ሆቴሎች በጉባኤው ላይ ከሚሳተፉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ኩባንያዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለወደፊትም እንግዶችን የማግኘት ዕድላቸውን ያሰፋሉ። በተጨማሪም ትልልቅ ዝግጅቶችን ለማስተናገድ የሚያስፈልገው ዝግጅት የሆቴሎችን የአገልግሎት ደረጃ የሰራተኞችን አቅምና የደህንነት ስርዓት ያሻሽላል።

ጉባኤው በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድና የጉባኤው ተሳታፊዎችም ምቹ ቆይታ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ሆቴሎች የተለያዩ ዝግጅቶችን እያደረጉ ስለመሆኑ ይገልጻሉ። በቦሌ ሻላ መናፈሻ አካባቢ የሚገኘው ሳውዝ ሴንተራል ሆቴል ባለቤት የሆኑት አቶ ኤራንጎ ቴራሳ እንደሚገልጹት፣ ከንግድ ስራ ባለፈ ጉዳዩን እንደ ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነት ቆጥረው እንግዶችን በኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት ለማስተናገድ መዘጋጀታቸውን ይገልጻሉ፡፡

የአገልግሎት ደረጃ ለማሻሻል ይረዳ ዘንድ እና የጉዳዩን ግዝፈት እንዲገነዘቡ ሆቴሉ ከሰራተኞቻችን ጋር በስልጠና መልክ አጫጭር ውይይቶችን አካሂደናል የሚሉት አቶ ኤራንጎ፣ የእንግዶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ከፀጥታ አካላት ጋር በቅርበት እየሰሩ ስለመሆኑ ያስረዳሉ። እንግዶች ያለምንም ችግር ጉዳያቸውን እንዲከውኑም ለማገዝ መስተካከል ያለባቸውን ፈጣን እና አስተማማኝ የኢንተርኔት አገልግሎት ዝግጅት ተደርጓል። የአካባቢውን ንጽህና ለማስጠበቅ ስራዎች እየተሰሩ ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

እንደዚህ አይነት ሰፊ ዕድል የሚፈጥር ሁነት ሲገኝ ታዲያ ሆቴሎች ይህንን ጉባኤ ስኬታማ ለማድረግና የሀገሪቱን ገጽታ ለመገንባት በጋራ መስራት ይገባል የሚሉት ደግሞ የሞሲ ሆቴል ስራ አስኪያጅ ተረፈ ድጉማ ናቸው፡፡ እንግዶችን በአክብሮትና በፈገግታ መቀበል፣ የባህል ምግቦችንና መስተንግዶዎችን ማቅረብ ይገባልና ከወትሮ በተለየ መልኩ እየሰራንበት ነው ብለዋል፡፡

የትራንስፖርት አገልግሎት ማሻሻል፣ የደህንነት ስጋቶችን ማስወገድ፣ ከአካባቢው የጸጥታ ተቋማት ጋር እየሰሩ ስለመሆኑም አስረድተዋል፡፡ አንድ ሆቴል ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስን ሲያስተናግድ፣ በአዳራሾቹ ጥራት፣ በሠራተኞቹ የሙያ ብቃት፣ በአገልግሎት ደረጃውና በአስተዳደር ቅልጥፍናው ትልቅ ስም ሊገነባ ይችላል። በዚህም ዓለም አቀፍ እውቅና ሊያስገኝልንም ይችላል ይላሉ።

በመዲናዋ በስፋት እየተሰሩ ያሉ የኮሪደር እና የወንዝ ዳር የልማት ስራዎች ለሆቴሎች እና የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍ ውጤታማነት አስተዋፅኦው ከፍተኛ መሆኑን የሚገለፁት ደግሞ የግዮን ሆቴሎች ድርጅቶች ተወካይ አቶ በረከት መልካሙ፣ በመዲናዋ የተሰሩ የልማት ስራዎችን አድንቀው፣ የሚመጡ እንግዶችን በሞቀ የኢትዮጵያዊ አቀባበል ተቀብለው ለማስጎብኘት መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል። በከተማዋ የሚካሄዱ ዓለም አቀፍ ሁነቶች እንግዶችን ከማስተናገድ ባሻገር፣ በከተማዋ የሚኖራቸውን ቆይታ ለማራዘም የሚረዱ በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን የሚያመላክት እንደሆነም ገልፀዋል።

ለዝግጅት ክፍላችን ሀሳባቸውን ያካፈሉ የሆቴል ባለቤቶች እንደሚገልጹት እንደዚህ አይነት ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች በመዲናዋ መዘጋጀታቸው በተለይም ሆቴሎች ተደጋጋሚ እንግዶችን እንዲያገኙ በር ይከፍትላቸዋል። የኮንፈረንስ ቱሪዝም ፍላጎት ሲጨምር፣ ሆቴሎች አገልግሎታቸውን ለማሻሻል ወይም አዳዲስ ቅርንጫፎችን ለመክፈት ይበረታታሉ። ይህ ደግሞ በሆቴሉ ዘርፍ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል። ሆቴሎች የኮንፈረንስ አዳራሾቻቸውን ያስፋፋሉ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ይተገብራሉ እንዲሁም የውስጥ አገልግሎት ደረጃቸውን ከፍ ያደርጋሉ። ይህም ሆቴሉ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ያስችለዋል ብለዋል።

አክለውም ጉባኤዎቹ ሲዘጋጁ ብዙ የሥራ ዕድሎች ይፈጠራሉ። ለምሳሌ የዝግጅት አስተባባሪዎች፣ የጉብኝት መሪዎች፣ አስተርጓሚዎች፣ የሆቴል ሰራተኞች፣ ሾፌሮች እና የደህንነት ሰራተኞች ያስፈልጋሉ። እነዚህም የሥራ ዕድሎች ቀጥተኛ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ተያያዥ ዘርፎችንም ያካትታሉ። ለሆቴሎች ብቻ ሳይሆን ለመዲናዋም ይዞት የሚመጣው ትሩፋት ቀላል አለመሆኑን አንስተው፣ በዘላቂነት ዘመናዊ ሆቴሎች፣ የተሻሻሉ መንገዶች፣ የትራንስፖርት ሥርዓቶች እና የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎቶች እንዲገነቡ ያበረታታል። ይህም ለከተማዋ ነዋሪዎች የረጅም ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን፣ ለወደፊትም ተጨማሪ ጉባኤዎችን ለመሳብ ይረዳል ይላሉ።

ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በተሳካ ሁኔታ ማስተናገድ የከተማውንና የሀገሩን ገፅታ ከፍ ያደርጋል። ከተማዋ እንደ ዓለም አቀፍ የንግድ፣ የዲፕሎማሲ እና የባህል ማዕከል እንድትታወቅ ይረዳል። ይህም ለወደፊት ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችንና ቱሪዝምን ለመሳብ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋልና ሆቴሎች ትልቅ ኃላፊነት አለብን ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

# ማንኛውም ... ከገጽ 1 የዞረ

ዓላማዎች አካል በመሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ዓላማዎች ተብለው የተጠቀሱት፤ ነባር ሀገራዊ ስብራቶችን መጠገንና የተንከባለሉ ዕዳዎችን ማቃለል እንዲሁም የዛሬንና የነገን ትውልድ ጥያቄዎች በመመለስ የኢትዮጵያን ብልጽግና በአስተማማኝ መሠረት ላይ መገንባት የሚሉ ናቸው፡፡ የደመወዝ ጭማሪውም ከሁለተኛው ዓላማ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ከመስከረም ወር 2018 ዓ.ም. ጀምሮ ለሚፈፀም የመንግስት ሠራተኛ ደመወዝ ማሻሻያ ወጪ ከ160 ቢሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ በጀት ጠይቋል፡፡ ይሄም እንደ ሀገር ለመንግስት ሠራተኛው ለደመወዝ የሚወጣውን ጠቅላላ ዓመታዊ የመንግሥት ወጪ 560 ቢሊዮን ብር ያደርሰዋል።

ከፍተኛ በጀት ወጪ የተደረገበት የመንግስት ሠራተኛ ደመወዝ ማሻሻያ በውጤታማነት ተፈፃሚ እንዲሆን፣ በተለይም የደመወዝ ማሻሻያው ተጠቃሚ የሆነው በመንግስት ተቋማት መዋቅር ውስጥ ያለው የሠው ኃይል በተሰማራበት መስክ ምርታማነቱ እንዲጨምር እና የሚሰጠው አገልግሎት እንዲሻሻል በማድረግ ረገድ መከናወን ስላለበት ስራ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) ሃሳባቸውን አጋርተውናል፡፡

የደመወዝ ማሻሻያውን በበጎ እርምጃ እንደሚመለከቱት የጠቆሙት ሞላ (ዶ/ር)፤ “የገንዘብ የመግዛት ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መሄድ ተፈጥሯዊ ነው። በዚህ ዑደት ውስጥ በአብዛኛው ተጎጂ የሚሆኑት በቋሚ ወርሃዊ ደመወዝ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች ናቸው፡፡ በተለይ የገንዘብ የመግዛት አቅም ፈጣን በሆነ ለውጥ ውስጥ ሲሆን፤ በማይለዋወጥ ደመወዝ የሚሠሩና ኑሯቸውን በደመወዝ ገቢ የሚመሩ ሠዎች ተጎጂ ይሆናሉ። መንግስትም ከመስከረም ወር 2018 ዓ.ም. ለሠራተኞች የደመወዝ ማስተካከያ ለማድረግ መወሰኑ የሚደገፍ እርምጃ ነው፡፡ ይህም በኑሮ ጫና እየተፈተኑ የሚገኙት የመንግስት ሠራተኞች ቢያንስ መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ያለመጨናነቅ ማሟላት የሚችሉበትን ዕድል ይፈጥራል” ሲሉ አንስተዋል፡፡

ከፍተኛ ተመራማሪው እንዳብራሩት፤ የአንድን ሀገር ልማትና ብልፅግና ከሚያመጡ ወሳኝ አቅሞች መካከል፤ የሠው ኃይል፣ ገንዘብ (ካፒታል) እና መሬት (የተፈጥሮ ሃብት) ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ ሁሉ ደግሞ የሠው ኃይል ቁልፉና ቀዳሚው ነው፡፡ ምክንያቱም ሌሎቹ አቅሞች (ገንዘብ እና መሬት) ካለሠው ምንም ናቸው፡፡ የሠው ኃይል ሲባል ደግሞ፤ የተማረ እና የሠለጠነ መሆን አለበት፡፡ ዕውቀት፣ ሙያዊ ክህሎት እና ልምድ ያለው የሠው ኃይል ከሁሉም የበለጠ አቅም መሆኑን በተግባር ለማረጋገጥ፣ ሥራዎቹን በተነሳሽነት፣ በብቃት እና በአግባቡ መከወን ይኖርበታል፡፡

“እንደሀገር ካለው አቅም አንፃር ለደመወዝ ማሻሻያ የተመደበው ገንዘብ በጣም ከፍተኛ የሚባል ነው፡፡ ይህ ገንዘብ ቀላል ለማይባሉ የመሠረተ ልማት ግንባታ




ፎቶ- ከገፀ ድር

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባሳለፍነው ሳምንት ለመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ ማሻሻያ ማድረጉ ይታወሳል

እና ሌሎች ሥራዎች ማከናወኛ ሊውል የሚችል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለሠራተኛ ደመወዝ እንዲውል በመንግስት መወሰኑ፤ የሠው ኃይሉ ዘላቂነት ላለው የሀገር ልማት እና ዕድገት ምን ያክል አስፈላጊ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው” ያሉት ሞላ (ዶ/ር)፤ “የደመወዝ ማሻሻያ የተደረገለት ማንኛውም የሕዝብ አገልጋይ ‘ሀገሬ ከሌላት ሃብት ላይ ቀንሳ ይህንን ካደረገችልኝ፤ እኔ ደግሞ የምችለውን ሁሉ ላደርግላት ይገባል’ በሚል አስተሳሰብ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት ሊወጣ ይገባል፡፡ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዩን ህብረተሰብ እርካታ ማሻሻል ይኖርበታል። ሥራዎችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መከወንን የየዕለት ተግባሩ ማድረግ ይጠበቅበታል” በማለት ምክረ ሃሳባቸውን ለግሰዋል፡፡

አክለውም፤ እንደ ሀገር ምርታማነት እንዲጨምር እና ገቢ እንዲያድግ ሳይታክት መሥራት ከዚህ የሠው ኃይል የሚጠበቅ ቁልፍ ተግባርና ኃላፊነት መሆኑን አንስተዋል፡፡ ምርታማነት ከጨመረ፣ የሀገር ዕድገት እና ብልፅግና ከተረጋገጠ፣ የደመወዝ ጭማሪ ብቻ ሳይሆን ከዚህም ከፍ ያለ ጠቀሜታን ማግኘት እንደሚችል መገንዘብና የሚጠበቅበትን መወጣት አለበትም ብለዋል፡፡

“የደመወዝ ማሻሻያ ካለን የልማት ፍላጎት አንጻር አገልግሎቶችና መሠረተ ልማት ለማስፋፋት የሚያስፈልገንን ሀብት የሚሻማ ቢሆንም፣ የመንግሥት ሠራተኛውን ኑሮ ማሻሻል ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ የተደረገ ነው” ያለው ነሐሴ 12 ቀን 2017 ዓ.ም. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን መግለጫ፤ ከደመወዝ ማሻሻያው ባሻገር የመንግሥት ሠራተኛው ችግር በደመወዝ ማሻሻያ ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ በቀጣይ የቤት አቅርቦትን እና የጤና መድን ሽፋኑን ጨምሮ የተለያዩ መፍትሔዎች እንደሚወሰዱ አሳውቋል፡፡

መንግሥት ይሄንን የደመወዝ ማሻሻያ ሲያደርግ ጭማሪው በቂና የመጨረሻ እንዳልሆነ፣ በቀጣይነት የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ማሻሻያው እየተተገበረ ሲሄድ ውጤትን መሠረት ያደረጉ ማሻሻያዎች እንደሚደረጉ፣ በተጨማሪም የተጀመረው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ይበልጥ ውጤት እያስመዘገበ በሄደ ቁጥር፣ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የትሩፋቱ ተቋዳሽ እንደሚሆን በመግለጫው ተጠቅሷል፡፡

“የመንግሥት ሠራተኞችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በተገቢ ደረጃና መጠን ለመክፈል ከተፈለገ፣ ያንን የሚሸከም ሀገራዊ ኢኮኖሚ መገንባት አለብን” ያለው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፤ ኢትዮጵያ ለአገልጋዮቿ ተገቢውን ክፍያ እንድትከፍል የሚያስችላትን ኢኮኖሚ የመገንባት ኃላፊነት ደግሞ፣ በመንግሥት ሠራተኛው ላይ ጭምር የተጣለ ብሔራዊ ግዴታ መሆኑን አፅንኦት በመስጠት አመላክቷል፡፡ “ካልተከልነው ዛፍ ፍሬ፣ ካልዘራነው ሰብል ምርት ልናገኝ አንችልም” የሚል ጥልቅ ሃሳብ የያዘ አባባል በመጠቀምም፤ እንደ ሀገር ኢኮኖሚያችን ካላደገ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ሊያድግ እንደማይችል ተገልጿል፡፡ በሀገር ደረጃ የታክስ ገቢን በአንድ በመቶ ማሳደግ ቢቻል፤ ከ300 ቢሊዮን በላይ ተጨማሪ ሀገራዊ ገቢ የሚገኝበት አቅም እንደሚፈጠር በምሳሌ በማሳየት፤ ይሄንን ለማሳካት ደግሞ በየመስኩ የሚገኙ የመንግሥት ሠራተኞች ከፍተኛውን ሚና መጫወት እንደሚገባቸው አሳስቧል፡፡

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር መኩሪያ ኃይሌ (ዶ/ር) ከጥቂት ቀናት በፊት፤ የገንዘብ ሚኒስቴር የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርምን ወደ ሙሉ ትግበራ ማስገባቱን በማስመልከት በተዘጋጀ መድረክ ላይ ተገኝተው እንደተናገሩት፤ ተሿሚዎችን፣ የጸጥታ አካላትን፣ ዳኞችን ጨምሮ ቁጥራቸው ከ3 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ የመንግስት ሠራተኞች የደመወዝ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ ከፌዴራል ጀምሮ እስከታችኛው አስተዳደራዊ መዋቅር ድረስ ትምህርት ቤቶችንና

> “ለደመወዝ ማሻሻያ የተመደበው ቀላል ለማይባሉ የመሠረተ ልማት ግንባታ እና ሌሎች ሥራዎች ማከናወኛ ሊውል የሚችል ነው። ይሁን እንጂ ለሠራተኛ ደመወዝ እንዲውል በመንግስት መወሰኑ፤ የሠው ኃይሉ ዘላቂነት ላለው የሀገር ልማት እና ዕድገት ምን ያክል አስፈላጊ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው”

ጤና ተቋማትን ጨምሮ 1 ሺህ 720 የሚደርሱ ተቋማት አሉ፡፡ የመንግስት ተቋማትን አደረጃጀትና አሰራር በማዘመን በክህሎትና በባህሪ የበቃ የሰው ኃይል አስተዳደርና ልማትን በመዘርጋት ለተገልጋዩ ኅብረተሰብ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የተለያዩ ሪፎርሞች እየተካሄዱ ናቸው። ከሪፎርሞቹ መካከል የመንግስት ተቋማት አሠራራቸውን በማዘመን ለተገልጋዩ ኅብረተሰብ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ፤ የመንግስት ሰራተኛው ስራውን በውጤታማነት በመፈፀም፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ እና አገልግሎት በማሻሻል፣ የሥራ ዲሲፕሊንን በማክበር፣ የሥራ ሰዓትን በአግባቡ በመጠቀም፣ የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ በመወጣት ለሀገራዊ ዕድገት የድርሻውን ሊወጣ ይገባል በማለት አሳስበዋል፡፡

የመንግስት ሠራተኛው ይህንን በአግባቡ መፈፀም ከቻለ፤ እንደ ሀገር የተቀመጠው የሪፎርም ዕቅድ ውጤታማ እንደሚሆን ኮሚሽነር መኩሪያ (ዶ/ር) አንስተዋል። የመንግስት ሠራተኛው ተጠቃሚነት በደመወዝ ማሻሻያ ብቻ የተገደበ ሳይሆን፤ እንደውጤታማነቱ በየጊዜው ማትጊያና ማበረታቻ እየተሰጠው፣ ከዕድገቱና ከልማቱ ተጠቃሚነቱ እየተረጋገጠ፣ መካከለኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ አካል እስከሚሆንበት ደረጃ ድረስ ይቀጥላል፡፡ ለዚህ ደግሞ በአርሶ አደሩ እና በአርብቶ አደሩም ሆነ በከተማው ነዋሪ ዕድገት ላይ ቁልፍ ሚና ያለው የመንግስት ሠራተኛው የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡና በውጤታማነት ሊወጣ ይገባል ብለዋል፡፡

“መንግስት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ያካሄዳቸው ዘርፈ ብዙ ሪፎርሞች ተጨባጭ ውጤት አምጥተዋል” ያሉት የገንዘብ ሚኒስትሩ አህመድ ሽዴ በበኩላቸው፤ የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርሙ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን በማሳደግና ኢኮኖሚውን በማነቃቃት ዓይነተኛ ሚና መጫወቱን አንስተዋል። የውጭ ምንዛሬ ተመን በገበያ እንዲወሰን መደረጉ በተለይም የዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ ዜጎችን ጫና ውስጥ እንዳይከት መንግስት የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰዱንም አስታውሰዋል። መንግስት የቋሚ ደመወዝ ተከፋይ ዜጎችን የኑሮ ጫና ለማቃለል ቁርጠኛ አቋም ይዞ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከመስከረም ጀምሮ የተደረገው ማሻሻያም የዚህ ማሳያ ነው። የመንግስት ሠራተኛውም ሥራዎችን በምርታማነት፣ በወጪ ቆጣቢነት እና በውጤታማነት ማከናወን ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

“ለሠራተኞች ደመወዝ ማስተካከያ እንዲሆን የተያዘው ከ160 ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ነው፡፡ ይህ ከፍተኛ ገንዘብ በደመወዝ መልኩ ወጪ ተደርጎ ወደ ኢኮኖሚው የሚገባ ነው፡፡ በዚህ ላይ በጥናት የተመሠረተ ቀጣይነት ያለው ሥራ ካልተሠራ ገንዘቡ በገበያው ላይ የሚታየውን የዋጋ ግሽበት አባባሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ የዋጋ ግሽበትን ሊያቃልሉ የሚችሉ የአጭር እና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን በማቀድ ተፈፃሚ ማድረግ ይገባል” ያሉት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ከፍተኛ ተመራማሪ ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር)፤ ይህን መነሻ በማድረግ በገበያው ላይ የምርት እጥረት በመፍጠር፣ በምርትና አገልግሎቶች ላይ ያልተገባ ጭማሪ በማድረግ እና በመሳሰሉ ምክንያቶች የዋጋ ግሽበት እንዲባባስ የሚያደርጉ አካላትን ካሉ ከግንዛቤ ፈጠራ ጀምሮ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ አለፍ ሲልም አስተማሪ እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ መክረዋል፡፡

# የመንገድ ፕሮጀክቱ የት ደረሰ?

## “የፕሮጀክቱ አፈጻጸም መጓተት በእንቅስቃሴያችን ላይ እንቅፋት ፈጥሮብናል”

ነዋሪዎች

## “ፕሮጀክቱ በበጀት ዓመቱ ተጠናቅቆ ወደ አገልግሎት እንዲገባ ይደረጋል”

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን

**በለይላ መሀመድ**

ውድ አንባቢያን፤ ስለአየር ጤና ወለቴ ሱቅ - አለምገና አደባባይ አስፋልት ግንባታ ፕሮጀክት በመጋቢት 27 ቀን 2017 ዓ.ም ዕትማችን መዘገባችን ይታወሳል። በወቅቱም የፕሮጀክቱ አፈጻጸም 10 በመቶ እንደነበር ተመላክቷል፡፡ ለመሆኑ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም አሁን ምን ደረጃ ላይ ደርሷል? ሲል የዝግጅት ክፍላችን የአካባቢውን ነዋሪዎች፣ የፕሮጀክቱን የስራ ተቋራጭ፣ አማካሪ መሀንዲስ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣንን አነጋግሯል፡፡

ወይዘሮ ሳራ ታደሰ በአጃምባ ኮንዶምንየም መኖር ከጀመሩ 5 ዓመታትን አስቆጥረዋል፡፡ የመንገድ ግንባታ ስራው ከመጀመሩ በፊት ከአየር ጤና እስከ ካራ ለመድረስ ከአንድ ሰዓት በላይ ይፈጅ ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- ማታ ከስራ ቦታ 11፡45 ሰዓት ተነስተን እስከ ሩብ ጉዳይ ለሁለት ድረስ እናመሽ ነበር። ጠዋትም ቢሆን ሰርቪስ ካመለጣቸው በትራንስፖርት በሰዓቱ ስራ ቦታ መድረስ እጅግ በጣም ፈታኝ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ከስራ ኃላፊዎቻቸው ጋር ግጭት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸው ነበር። ቅዳሜና እሁድም ቢሆን በማህበራዊ መስተጋብራቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድር ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የግል መኖሪያ ቤታቸውን አከራይተው ወደሌላ ሰፈር ተከራይተው ለመኖር ውሳኔ ላይ ደርሰው እንደነበርም ያስታውሳሉ፡፡ የመንገድ ስራው ከጀመረ ከ2016 ዓ.ም ወዲህ በተለይም ከአየር ጤና እስከ ካራ ድረስ ግማሹ የመንገድ ክፍል የአስፋልት ስር ንጣፍ እንዲሁም ድልድዮች በመሰራታቸው የትራንስፖርት ችግሩ መሻሻል አሳይቷል፤ የግል ቤታቸውን ትተው ከመከራየት ታድጓቸዋል፡፡

ሌላዋ አስተያየት ሰጪያችን በጫማ ንግድ የተሰማራችው ወይዘሪት ሳራ ሀሰን ናት፡፡ መንገዱ ከተቆፋፈረ ወዲህ በስራዋ ላይ እንቅፋት እንደፈጠረባት ትገልጻለች። በበጋ አቧራው የጫማዎቹን አዲስነት በመቀነስ ዋጋ እንዲያጣ አድርጎባታል። ከዚህ በተጨማሪ በመቆፋፈሩ ሱቋ ዳገት ላይ እንዲንጠለጠል፣ መውጫ መግቢያ መንገዱ ገደልና ጭቃ እንዲሆን በማድረግና በዚህም የተነሳ ደንበኞቿን እንዳሳጣት ነው የምትገልጸው፡፡ አሁን ላይ ኪሳራ ውስጥ መግባቷን ገልጻ “የመንገድ ስራው ሲጠናቀቅ በአዲስ ስራ እጀምራለሁ” በሚል በተስፋ እየጠበቀች እንደሆነ ነው የገለጸችው፡፡

በአካባቢው በትራፊክ ማስተናበር ተሰማርተው ያገኘናቸው ሳጂን አዲስ አስረስም ስለመንገዱ አስተያየት ሰጥተውናል፡፡ እንደ እሳቸው ገለጻ፣ በዚህ መስመር መስራት ከጀመሩ አንድ ዓመት አስቆጥረዋል፡፡ መጀመሪያ ላይ ሲመጡ መንገዱ ጠባብ ከመሆኑም በተጨማሪ ሌላ ምንም አይነት አማራጭ የሌለው ከመሆኑ የተነሳ የትራፊክ ፍሰቱ እጅግ በጣም አስቸጋሪ፣ በተለይም በሰው ህይወትና አካል እንዲሁም በንብረት ላይ ጉዳት ይደርስ ነበር፡፡ የማስተናበር ስራውን ያለእረፍት ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ መሀል ላይ ቆመው ለመስራት ይገደዱም ነበር፡፡



ፎቶ -በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ከአየር ጤና ወለቴ ሱቅ - አለምገና አደባባይ አስፋልት ግንባታ ፕሮጀክት ከፊል ገፅታ

በሂደት የመንገዱ የትራፊክ ፍሰት መሻሻል አሳይቷል፡፡ አሁን ላይ ከአየር ጤና እስከ ካራ አጃንባ መገንጠያ የሚገኘው ግማሽ የመንገድ ክፍል ላይ አንጻራዊ ለውጥ እየመጣ ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ የመንገድ ስራው ካልተጠናቀቀ በትራፊክ ፍሰቱ ላይ አሉታዊ ጫና ማሳደሩ ስለማይቀር በተቻለ መጠን ትኩረት ተሰጥቶት በፍጥነት ቢሰራ መልካም ነው ብለዋል፡፡

ካራ ቆሬ ተወልዶ ያደገበት ሰፈር እንደሆነ የሚገልጸው የራይድ አሽከርካሪ ወጣት አሚት ተስፋዬ የመንገዱን አስቸጋሪነት ሲገልጽ፤ “እጅግ በጣም ይዘጋጋ ነበር፡፡ በተለይም ሁለት ሰዓት ካለፈ በኋላ ከካራ መውጣት ይከብድ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ከወጣሁ ማታ አራት ሰዓት ካልሆነ በስተቀር አልመለስም። በመንገዱ መጨናነቅ ምክንያት ሳልፈልግ አመሽ ነበር፡፡ እንዳጋጣሚ ከመጣሁ ደግሞ በውስጥ ለውስጥ መንገድ ስለምጓዝ መኪናዬ እየተጎዳብኝ፣ ለአላስፈላጊ ወጪም ስዳረግ ቆይቻለሁ” ይላል፡፡ የመንገዱ የተወሰነ አካባቢ ስራ ከጀመረ ወዲህ የትራፊክ መጨናነቁ ቀለል ማለቱንም አክሏል፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ምን ልርዳዎ?

### የሸማች መብት እና የነጋዴው ግዴታ

**በንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 መሰረት፡-**

### የሸማች መብቶች

1. መረጃ ወይም መግለጫ የማግኘት፡- ማንኛውም ሸማች ስለሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራትና ዓይነት አስመልክቶ በቂና ትክክለኛ መረጃ ወይም መግለጫ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. አማርጦ የመግዛት፡- ለመሸመት የሚፈልጋቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶችን አማርጦ የመግዛት መብት አለው፡፡
3. እንዲገዛ ያለመገደድ፡- ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ጥራት ወይም አማራጮችን በማየቱ ወይም የዋጋ ድርድር በማድረጉ ምክንያት እንዲገዛ ያለመገደድ፣
4. በአክብሮት የመስተናገድ፡- ሸማች በነጋዴው ከሚደርስበት የስድብ፣ የዛቻ፣ የማስፈራራት እና የስም ማጥፋት ተግባር የመጠበቅ መብት አለው፡፡ በእርግጥ እነዚህ ተግባራት ስድብ፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት እና ስም ማጥፋት እራሳቸውን ችለው ወንጀል እንደሆኑ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መገንዘብ ይቻላል፡፡
5. ካሣ እንዲከፍልለት የመጠየቅ፡- ሸማች ወይም ገዢ የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በመግዛቱ ወይም በመጠቀሙ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ካለ፣ ለደረሰበት ጉዳት ካሳ የማግኘት መብት አለው፡፡

### የነጋዴ ግዴታዎች

ሸማቾች ያላቸውን መብት ከላይ ከተዘረዘሩት መብቶቻቸው በተጨማሪም የነጋዴዎች ግዴታ ለሸማቾች መብት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነጋዴዎች በርካታ ግዴታዎች ያሉባቸው ቢሆንም በዋናነት የዋጋ ዝርዝር በንግድ ቤቱ ላይ መለጠፍ፣ የንግድ ዕቃዎች ላይ መግለጫ መለጠፍ፣ ደረሰኞችን መስጠትና ቀሪዎችን መያዝ፣ የራሱን /የንግድ ስሙን/ ስለመግለጽ፣ የንግድ ማስታወቂያ ትክክለኛ መሆን እና ሌሎች ግዴታዎች አሉባቸው፡፡

**ምንጭ፡-** የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ**

# የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012

## ክፍል አንድ

በመላኩ ተፈሪ (ዐቃቤ ህግ)

### የአዋጁ አስፈላጊነት

- በኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት መንግስታዊ አሰራር ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ ለማድረግ፤
- ማናቸውም የመንግስት ባለሥልጣን ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን፤
- የአስተዳደር ተቋማት ውሳኔዎች በሰዎች መብቶችና ጥቅሞች ላይ የሚያስከትሉትን ጣልቃ ገብነት በህግ የሚመራና ለህግ የሚገዛ ለማድረግ፤
- የአስተዳደር ተቋማት የውሳኔ አሰጣጥና የመመሪያ አወጣጥ መርሆዎችና ሥነ-ሥርዓት ለማካተት፤
- በአስተዳደራዊ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ቅር የተሰኘ ሰው የውሳኔዎቹንና የመመሪያዎቹን ሕጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓት በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትህን ለማስፈን ነው፡፡

### የተፈጻሚነት ወሰን

- በሁሉም የአስተዳደር ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ሲሆን በወንጀል ሥነ ሥርዓት ህጉ በሚመሩ የዐቃቤ ህግ እና የፖሊስ ተግባራት እንዲሁም በመከላከያና፣ የደህንነት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተቋማት አገልግሎት የመስጠትና የቁጥጥር ስራዎችን ሲያከናውኑ፣መመሪያ ሲያወጡ እና አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ሲወስኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
- ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን የውጪ ምንዛሪ ተመንና የወለድ ተመንን እና ሌሎች ተመሳሳይ ምስጢራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ መመሪያ ሲያወጣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ከ7 እስከ 10 የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመተግበር አይገደድም፡፡

### የአስተዳደር አካል ምንነት

- እንደ ብላክ ሎው የሕግ መዝገበ ቃላት የአስተዳደር ተቋም ማለት አንድን የተለየ ሕግ ለማስፈጸም ስልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል ነው በማለት ያስቀምጣል። በመሆኑም የአስተዳደር አካል በሕግ አስፈጻሚው የመንግስት ቅርንጫፍ ስር የሚገኝ ተቋም ሆኖ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም ሥልጣን በሕግ የተሰጠው አካል ነው፡፡



### መመሪያ ስለማውጣት

- ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም በሕግ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡
- የአስተዳደር ተቋም መመሪያ የሚያወጣው በዚህ አዋጅ በተደነገገው ሥነ-ሥርዓት መሠረት ብቻ ነው፡፡

### መመሪያ ስለሚወጣበት ጊዜ

የአስተዳደር ተቋም ሊያወጣ የሚገባውን መመሪያ አስመልክቶ በእናት ህጉ መመሪያ እንዲወጣ በአስገዳጅ ሁኔታ በተደነገገ ጊዜ በሦስት ወራት ውስጥ አስገዳጅ ባልሆነ ሁኔታ በተደነገገ ጊዜ ደግሞ በተገቢው ጊዜ ውስጥ መመሪያውን ማውጣት አለበት፡፡

### መመሪያ እንዲወጣ ጥያቄ ስለማቅረብ

ማንኛውም ሰው አንድ የአስተዳደር ተቋም ሊያወጣው የሚገባውን መመሪያ በተገቢው ጊዜ ሳያወጣ ቢቀር መመሪያውን እንዲያወጣ በጽሑፍ ሊጠይቀው ይችላል።

ጥያቄው የቀረበለት የአስተዳደር ተቋም በሠላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ መመሪያውን የማውጣት ሂደት መጀመር ወይም ምክንያቱን በመግለጽ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ያላወጣ ቢሆንም የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት አለው፡፡

የአስተዳደር ተቋም ሊያወጣ የሚገባውን መመሪያ አለማውጣቱ በሕግ በተሰጠው ኃላፊነት ሊሰጥ የሚገባውን አገልግሎት ወይም አስተዳደራዊ ውሳኔ ላለመስጠት ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

### የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም የሚያወጣውን መመሪያ በተመለከተ የሚከተሉትን የያዘ መዝገብ ማደራጀት አለበት፡-

- በተቋሙ በመታየት ላይ ያለ ረቂቅ መመሪያ ርዕሰ ጉዳይ እና የመመሪያውን አወጣጥ መርሃ ግብር፤
- የረቂቅ መመሪያው ዝግጅት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመለክት መረጃ፤
- ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ የታተሙ ማስታወቂያዎች፤
- በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት ስለሚቀርብበት ጊዜ፤
- ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ በጽሑፍ እና በቃል የተሰበሰቡ አስተያየቶችንና በአስተዳደር ተቋሙ በአስተያየቶቹ ላይ የተወሰዱ አቋሞችን መያዝ አለበት፡፡

ማንኛውም ሰው ከላይ በተዘረዘረው መሰረት የሚደራጀውን መዝገብ መመልከት ወይም አስፈላጊውን ወጪ ሸፍኖ ቅጂውን መውሰድ ይችላል።

### ማስታወቂያ ስለማውጣት

የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ከማውጣቱ በፊት ስለሚያወጣው ረቂቅ መመሪያ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና የተቋሙን ድረ ገጽ ጨምሮ በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት።

- የመመሪያውን ረቂቅ ለማዘጋጀት መሰረት የሆነውን ሕጋዊ ሥልጣን እና በመመሪያው ስለሚካተቱት ርዕሰ ጉዳዮች፤
- የረቂቅ መመሪያውን ቅጂ ማግኘት የሚቻል ስለመሆኑና የሚገኝበትን ሁኔታ፤
- በረቂቅ መመሪያው ላይ ሰዎች አስተያየታቸውን መቼ እና እንዴት ሊያቀርቡ እንደሚችሉ፤
- በተደራጀው መዝገብ ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን የትና መቼ ማግኘት እንደሚቻል የሚገልፅ መረጃ መያዝ አለበት፡፡

### ረቂቅ መመሪያን ለአስተያየት ስለመላክ

- የአስተዳደር ተቋም ለሕዝብ ያሳወቀውን ረቂቅ መመሪያ ለሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ለአስተያየት መላክ አለበት፡፡
- የሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት ካላቸው አስተያየታቸውን ተቋሙ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሑፍ መላክ አለባቸው፡፡ ሆኖም ተቋሙ የሚወስነው የጊዜ ገደብ በማናቸውም ሁኔታ ከ15 የሥራ ቀናት ማነስ የለበትም።

### የውይይት መድረክ ስለማዘጋጀት

- የአስተዳደር ተቋሙ በመመሪያው ረቂቅ ላይ የጽሑፍ አስተያየት መቀበያ ጊዜ ካበቃ በኋላ መመሪያው ከመፅደቁ በፊት ማንኛውም ሰው የሚሳተፍበት የውይይት መድረክ ማዘጋጀትና ግብዓት መሰብሰብ አለበት፡፡
- በመድረኩ የሚሳተፍ ሰው አስተያየቱን በጽሑፍ ጭምር ሊያቀርብ ይችላል፡፡
- የአስተዳደር ተቋሙ በሚያዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ አስተያየቶችን ማስተናገድ የሚያስችል በቂ ጊዜ መመደብ አለበት፡፡

የፅሁፉን ቀጣይ ክፍል በሚቀጥለው ዕትም ይዘንላችሁ እንቀርባለን

# ተናፋቂዎቹ የሴቶች የነፃነት በዓላት

- **በዓላቱ ሴቶች አስተዳደራዊ ስርዓት የሚማሩባቸው፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችንም የሚያዳብሩባቸው እንደሆኑ ተገልጿል**

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ለኢትዮጵያዊ አብሮነትና አንድነት፣ ለህዝቡ የእርስ በርስ ትስስር፣ ለማህበራዊ መስተጋብር... መሰረት ተብለው ከሚጠቀሱት መካከል የበዓላት እሴቶች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ እሴቶች አበርክቶቸው ብሔርን፣ ጾታን፣ የዕድሜ ክልልን፣ የእውቀት ደረጃንና ሌሎችንም የማይለዩ መሆኑ ዋጋቸውን የበለጠ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ተናፋቂ የሴቶች የነጻነት በዓላት የሆኑትን ሽኖዬ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬ፣ ሶለል እና አሸንዳን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የልጃገረዶች የነጻነት በዓላት ከሆኑት መካከል ሽኖዬ አንዱ ነው። ይህም ክረምት አልፎ የፀደይ ወቅት መምጣቱን የሚያበስሩበት ጨዋታ ነው። በሽኖዬ ልጃገረዶች በተለያዩ ባህላዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች አምረውና ደምቀው አደባባይ በመውጣት ባህላዊ ዜማዎችን ያቀርባሉ።

በዓሉን በተመለከተ የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት ሀደ ሲንቄ አረጋሽ ገዳ ለዝግጅት ክፍላችን ሀሳባቸውን አጋርተዋል፡፡ ሀደ ስንቄ አረጋሽ በማብራሪያቸው፣ “አበባ ይዘን ቤት ለቤት በመሄድ እንጨፍራለን። ዳቦ አልያም ገንዘብ ይሰጠናል፤ እንመረቃለን፡፡ በዕለቱ ቤተሰብ ‘ለምን?’ ብሎ አይቆጣንም” ሲሉ ከቀደመ ትውስታቸው ጋር በማስተሳሰር የነጻነት በዓል መሆኑን ገልጸውልናል፡፡

የበዓሉ ዕለት ልጃገረዶች በወጣቶች የሚታጩበት አጋጣሚዎች ስለሚፈጠሩ ትውውቅን ከማጠናከርና አብሮነትን ከማጎልበት አንጻር ያለው አበርክቶ ትልቅ መሆኑን አክለዋል፡፡

በዋግህምራና በሰቆጣ አካባቢዎች “ሻደይ”፣ በላስታ ላሊበላና ጎንደር “አሸንድዬ” እንዲሁም በራያ ቆቦ “ሶለል”፣ በእንደርታና ተምቤን “አሸንዳ”፤ በአክሱም “አይኒዋሪ” እንዲሁም በአዲግራት አካባቢዎች “ማርያ” የሚሰኘው ሌላኛው የሴቶች የነጻነት በዓል ነው። ሴቶች ልጃገረዶችም ሆኑ እናቶች አምረውና ተውበው የሚታዩበት፣ ከሚሰሩት ስራና የቤተሰብ ቁጥጥር ነፃ የሚሆኑበት፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ደስታቸውንና ናፍቆታቸውን በአደባባይ የሚገላለፁበት ነው። በዓሉን ሴቶች እንደ ነጻነታቸው ቀን በመቁጠር አሸንዳ የተባለውን ቅጠል ሰፊ ቄጤማ መሳይ አረንጓዴ ሳር አቀጣጥለውና እንደጉርድ ቀሚስ በወገባቸው አስረው ከበሮ እየመቱ ከንጋት እስከ ምሽት ድረስ በጨዋታ ያሳልፉታል።

የሰቆጣ ከተማ ተወላጅ እና የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ወይንሀረግ አዳነ፤ በዓሉ በጉጉት የሚጠበቅ፣ ሴቶች ነፃነታቸውን የሚያውጁበትና በአደባባይ የሚነግሱበት እንደሆነ ይናገራሉ። “በዓሉን ለማክበር ሦስት እና አራት ቀናት ሲቀሩ ከምንተዋወቃቸውና በእድሜ እኩያ የሆንን ልጃገረዶች ተሰባስበን ቡድን እንመሰርታለን፤ ሹሩባ እንሰራለን፤ በዋዜማውም ከስር ነጭ ከላይ አረንጓዴ የሆነውን የሻደይ ቅጠል


ፎቶ- ከገፀ ድር
በበዓላቱ ሴቶች ከሚያሳዮቸው ጭፈራዎች በከፊል

ቆርጠን እንመጣለን፡፡ ከዚያም ወገብ ላይ ለማሰር በሚመች መልኩ እንሰራለን” ሲሉ ለበዓሉ ስለሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት ይገልፃሉ።

ነሐሴ 16 ቀን በጠዋት አዳዲስ ልብስና ጫማ በመልበስ፣ አሸንዳውን ወገባችን ላይ እንታጠቃለን፡፡ ከዚያም የሃብታምና የድሃ ሳይባል በሁሉም ቤት እየገባን በነፃነት እንጨፍራለን፤ እንጫወታለን። ይህ ሂደትም እስከ አራት ቀን ድረስ ይቀጥላል፡፡ በአራተኛው ቀን ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የተሰጠንን ምግብ በመመገብ ለቀጣይ ዓመት “በሰላም አድርሰን” ብለን ጨዋታችንን እንቋጫለን ሲሉ ስለበዓሉ አከባበር ተናግረዋል፡፡

“በዓሉ ለእኔ ትልቁ የነፃነቴና የደስታዬ ቀን ነው” የሚሉት ወይዘሮ ወይንሀረግ፤ “ከዝግጅቱ ጀምሮ በዓሉ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ማንኛውም የቤተሰብ አባል ‘የት ወጣሽ፣ የት ገባሽ’ የሚል ቁጥጥርና ቁጣ ሳይኖር ውሃ ከመቅዳት፣ እንጀራ ከመጋገር፣ ወጥ ከመስራት በአጠቃላይ ከቤት ውስጥ ስራ ነፃ ሆነን በደስታና በጨዋታ የምናሳልፈው ቀን በመሆኑ ነው” ሲሉ ምክንያቱን አብራርተዋል፡፡

ይህን እንደሚናፍቁት የሚናገሩት ወይዘሮ ወይንሀረግ፣ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላም በድምቀት ያከብሩታል፡፡ ለአንድ ዓመት ሳያገኙ ከቆዩት ጓደኛና ከተለያዩ የበዓሉ ተሳታፊዎች ጋር መገናኘትና መተዋወቅ አብሮነትን እና አንድነትን ለማጠናከር ትልቅ አስተዋፅኦ አለው ብለዋል፡፡

ወይዘሮ ዓለም አብርሃ የአሸንዳ በዓል አከባበርን በተመለከተ በሰጡት አስተያየት ደግሞ፣ “በዓሉ መከበር የሚጀምረው ነሐሴ 16 ሲሆን፤ እስከ ነሐሴ 18 ቀን በድምቀት መከበሩን ይቀጥላል፡፡ በልጃገረዶች ዘንድ በጉጉት የሚጠበቅ፣ የነፃነትና የደስታቸው ቀን ነው፡፡ በዓሉ ከመከበሩ አስቀድሞ ፀጉራቸውን ይሰራሉ፤ ባህላዊ አልባሳት ገዝተው፣ ያላቸውን አጥበው ወይም ከጎረቤት አሊያም ከዘመድ ተውሰው ይጠቀማሉ” ሲሉ ነግረውናል፡፡

ወይዘሮ ዓለም አክለውም፣ “በዋዜማው የሚደረገው አሸንዳውን የማዘጋጀት ስራ በጉጉት ይጠበቃል፡፡ የበዓሉ እለት ደግሞ ተሰባስበው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ እለቱን በምስጋና ያሳልፋሉ፡፡ በእያንዳንዱ ቤት በመሄድ ደግሞ ያዜማሉ” በማለት ስለከዋኔውና እሳቸውም ይኼንኑ ያደርጉ እንደነበር በማስታወስ ነግረውናል፡፡

የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን የባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ አቶ እዮብ ዘውዴ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፤ “ሻደይ ኃይማኖታዊና ባህላዊ እሴትን አጣምሮ የያዘ በየዓመቱ ከነሐሴ 16 እስከ 21 ቀን በታላቅ ድምቀት የሚከበር በዓል ነው፡፡ የበዓሉ ዋነኛ ባለቤቶችም ህፃናት፣ ወጣት ልጃገረዶች እና እናቶች ናቸው፡፡” ብለዋል፡፡

አቶ እዮብ አያይዘው እንደተናገሩት፤ በበዓሉ ሴቶች አምረው፣ ደምቀውና ተውበው በአደባባይ ይታያሉ። በተለየ ሁኔታ እናቶች ለህፃናቱና ልጃገረዶች ስለ በዓሉ አከባበር ስርዓት የሚያሳውቁበትና ባህሉም ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ የሚያደርጉበት ነው፡፡ በእነዚህ ቀናት ሴቶች ከምንም ዓይነት ቁጥጥር ነፃ ሆነው የሚጫወቱበት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ራሳቸውን ማዘዝ፣ መምራት ኃላፊነት መውሰድና በትብብር መስራትን የሚለምዱበትም ነው፡፡ ይህም ነፃነታቸውን የሚያውጁበት ማለት ነው፡፡

የአሸንዳ በዓል ሴቶች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ፣ ሀሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ፣ አቅም እንዳላቸው እንዲረዱና ለተለያየ ተልዕኮ ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ነው፡፡ ሴቶች በዓሉን ለማክበር ከቤት የወጡበትን ዓላማ ከውነው በታማኝነት መመለሳቸው፤ በተሰማሩበት የአመራርነትም ይሁን የሙያ ዘርፍ ምን ያህል ታማኝና ብቁ መሆናቸውን የሚያሳዩበት ነው ሲሉም በዓሉ ለሴቶች ያለውን ትርጉም አስረድተዋል፡፡

የሀደ ሲንቄ አረጋሽን ሀሳብ የሚያጠናክሩት ግርማ በቀለ (ዶ/ር) ናቸው፡፡ ግርማ (ዶ/ር) በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ መምህርና የአንቦ ዩኒቨርሲቲ የርቀት ትምህርት አስተባባሪ ናቸው፡፡ በዩኒቨርስቲው ፎክሎርና የቋንቋ ብዝሃነትን ሲያስተምሩም ቆይተዋል። ዶክተሩ በማብራሪያቸው፣ “ሽኖዬ፤ ልጃገረዶቹ በባህላዊ አለባበስ በማጌጥ፣ የልምላሜ መገለጫ የሆኑ ሳር ወይም እንግጫ ይዘው በአደባባይ መውጣታቸው ነፃነታቸውን የሚጎናፀፉበት ማሳያ ነው። በዓሉ ክረምቱ አልፎ ለአዲሱ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞታቸውን የሚገልፁበት ነው። ልጃገረዶቹ በአደባባይ ሃሳባቸውን በግጥም የሚገልፁበት፣ እርስ በእርሳቸው የወደፊት ተስፋቸውንና ህይወታቸውን በግልፅ የሚመካከሩበትና የሚማማሩበት፣ ማመስገን እንደሚችሉ የሚያውቁበት ነው” ብለዋል፡፡

አክለውም፤ “ልጃገረዶቹ ይህንን በዓል ለማክበር ሲወጡ የወደዱትን (ያፈቀሩትን) በግልፅ መናገር ባይችሉም በግጥሞቻቸው የማመስገን እና ፍላጎታቸውን የሚገልጹበት ነው፡፡ የትዳር አጋራቸውንም የመምረጥ እድል የሚያገኙበትና ማስተዳደር እንደሚችሉ የሚረዱበት በመሆኑ ትልቁ ነፃነታቸው ነው፡፡

የልጃገረዶች የእኩልነታቸው፣ የአንድነታቸው መገለጫ የሆነው የሽኖዬ በዓል ለትውልድ እንዲተላለፍ ታሪኩን፣ እሴቱንና ወጉን በጠበቀ ማክበሩን

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የመዲናዋ ኪነ-ጥበባዊ መሰናዶዎች




ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

በአብርሃም ገብሬ

በመዲናችን አዲስ አበባ ባለፉት ቀናት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ከዛሬ ጀምሮ ባሉት ቀናት ከሚቀርቡ መሰናዶዎች መካከል የሙዚቃ አልበም ምርቃት፣ የመጽሐፍት ህትመት፣ የሥዕል ዓውደ ርዕይ፣ የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል:: ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የዝግጅት ክፍላችን የተወሰኑትን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል::

## መጽሐፍት

“የግሬጌ ማስታወሻ ደብተር” የተሰኘ የትርጉም መጽሐፍ ለንባብ በቅቷል። “diary of a wimpy kid” የተሰኘው ይኸ መጽሐፍ በተርጓሚ ፍሎረንስ አሰበ አማካይነት ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው:: መጽሐፉ ልጆች የአማርኛ ንባብ እንዲያዳብሩና ስልቹ እንዳይሆኑ አድርጎ የሚያለማምድ የተባለ ሲሆን፣ በዋልያ መጽሐፍት አሳታሚ አማካይነት ታትሞ ለገበያ ቀርቧል::

በሌላ ዜና “የህላዌ ዘለሰኛ” የተሰኘው የግጥም መጽሐፍ ለንባብ ሊበቃ ነው። የፍቃዱ አስራት የግጥም ስብስቦችን የያዘው የህላዌ ዘለሰኛ መጽሐፍ 202 ገጽ ያለው ሲሆን፤ ወደ ማተሚያ ቤት መግባቱን ገጣሚው በማህበራዊ የትስስር ገጹ አስታውቋል:: በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥም አንባብያን እጅ እንደሚደርስ አክሏል::

በተመሳሳይ “የሕይወት ዕጥፋት” መጽሐፍ ለንባብ በቅቷል:: በደራሲ ደሳለው አዳነ የተደረሰው “የሕይወት እጥፋት” መጽሐፍ ፍቅርና የህይወት መልከ ብዙ ገጽታዎችን አጉልቶ የሚያሳይ ነው ተብሏል:: መጽሐፉ በተለያዩ የመጽሐፍ ማከፋፈያ መደብሮች ውስጥ ይገኛል::

## ሙዚቃ

የድምፃዊት ፍቅርአዲስ ነቃጥበብ አዲስ አልበም ሊወጣ ነው:: የድምፃዊት ፍቅርአዲስ አዲስ አልበም “ደህና ሰው” የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን፤ አልበሙ ሙሉ በሙሉ መጠናቀቁን ለመገናኛ ብዙሃን አሳውቃለች:: ድምፃዊቷ አዲሱን አልበሟን ለማስተዋወቅ እና በይፋ ለህዝብ ለማድረስ የፊታችን ማክሰኞ ነሐሴ 20 ቀን 2017 ዓ.ም ቀጠሮ ይዛለች:: ፍቅርአዲስ በ2008 ዓ.ም ለመጨረሻ ጊዜ ለህዝብ ያደረሰችው “ምስክር” የተሰኘ አልበሟን እንደሆነ የሚታወስ ነው::

በሌላ መረጃ፣ “ማስታወሻ” የተሠኘው የወጣቱ ድምፃዊ አዲስ ለገሠ የሙዚቃ አልበም በዛሬው ዕለት ይለቀቃል። በርካታ የሀገራችን የሙዚቃ ባለሙያዎችን ያሳተፈው ይህ አልበም፣ አዲስ ለገሥ የራሱን ቀለም እና አቀራረብ ያስተዋወቀበት ስራ እንደሆነ ተነግሯል::

“ማስታወሻ” 14 ዘፈኖችን ያካተተ አልበም ሲሆን በዜማና ግጥም ይልማ ገብረዓብ፣ ሞገስ ተካ፣ አብነት አጎናፍር፣ ቢንአሚር አህመድ፣ ዓለማየሁ ደመቀ፣ አንተነህ ወራሽ፣ እሱባለው ይታየው፣ ናትናኤል ግርማቸው፣ አስታወሰኝ ረጋሳ፣ እዮብ ዕድሉ፣ ዳዊት ተስፋዬ እና ራሱ አዲስ ለገሰም ተሳትፈውበታል። በሙዚቃ ቅንብሩ ደግሞ ሚካኤል ሃይሉ፣ ኪሩቤል ተስፋዬ፣ ብሩክ አፈወርቅ እና ኤርሚያስ ሞላ ተሳትፈዋል:: የማስተሪንግ ስራው በኪሩቤል ተስፋዬ ተከናውኗል። አልበሙ ከ10፡00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ ለገሰ ይፋዊ ዩትዩብ ቻናልና በሁሉም ዓለም አቀፍ የሙዚቃ መተግበሪያዎች በኩል ለአድማጮች ይደርሳል:: ድምፃዊ አዲስ ለገሰ ከዚህ በፊት ለህዝብ ባደረሳቸው “እንጆሪ”፣ “እንኳ”፣ “እወድሻለሁ” እና ከአንድ ወር በፊት በለቀቀው “እቱ” የተሰኙ ነጠላ ዜማዎቹ ይታወቃል::

## ሥዕል

የቡድን የግራፊክስ ጥበብ ዓውደ ርዕይ በመታየት ላይ ነው:: ሐምሌ 30 ቀን 2017 ዓ.ም በይፋ የተከፈተው እና የተለያዩ ሰዓሊያን ስራዎችን የያዘው የጥበብ ዓውደ ርዕይ በመታየት ላይ ይገኛል። በዚህ አውደ ርዕይ ሥራዎቻቸውን ካቀረቡ ከያኒያን መካከል ታደሰ ባይሳ፣ ሚኪያስ ሰለሞን፣ ቤርሳቤህ አለማየሁ፣ ምህረት እሸቱ፣ ዳግማዊ ጸጋዬና ሱራፌል መክብብ ይገኙበታል:: አውደ ርዕዩ እስከ ፊታችን ነሐሴ 28 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ሲሆን፣ እየታየ ያለው ደግሞ በህያት ሪጀንሲ ሆቴል ውስጥ በሚገኘው የፈንድቃ የባህል ማዕከል ውስጥ ነው::

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር:: የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል:: ከላይ የተቀመጠው ቁጥር በግራ በኩል ከታች ከተቀመጠው ቁጥር ጋር እናባዛዋለን:: አባዝተን ባገኘነው ውጤት ላይ ደግሞ በታችኛ በኩል በስተቀኝ ክብ ውስጥ ያለው ቁጥር እንቀንሳለን:: ቀንሰን ያገኘነው ውጤት የመሐለኛው ቁጥር ወይም የጥያቄው መልስ ይሆናል ማለት ነው:: በዚህ መሰረት የመጀመሪያ ረድፍ ላይ የተቀመጠው ክብ የጥያቄ መልስና አሰራር አብረን እንሰራለን:: 6 x 7 = 42 ይሆናል:: ከዚያ በኋላ 42 - 8 = 34 ይሆናል ማለት ነው:: በዚህ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ መልስና አሰራር እንደሚከተለው ይሆናል:: 6 x 6 = 36 ይሆናል:: 36 – 12 = 24 ይሆናል:: የጥያቄው መልስ 24 ይሆናል ማለት ነው::




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል:: በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ:: የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን::



# የጥበብ ፋና ወጊው ሲታወስ



ፎቶ- ከገፀ ድር

አርቲስት ደበበ እሸቱ “ሻፍት ኢን አፍሪካ” የተሰኘው ፊልም ላይ በሰራበት ወቅት

**በጊዜው አማረ**

የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ለስድስት አስርት ዓመታት የመጣበት መንገድ ሲታወስ፣ ከፊት የሚጠቀሱ አንጋፋ ስሞች መኖራቸው አይቀሬ ነው። ከእነዚህ መካከል አርቲስት ደበበ እሸቱ አንዱ ነው። የክብር ዶክተር አርቲስት ደበበ እሸቱ በ60 ዓመታት የጥበብ ህይወቱ፣ በርካታ ድራማዎች፣ ፊልሞች እና ቴአትሮች ላይ በመተወን በኢትዮጵያ የጥበብ ታሪክ የማይረሳ አሻራውን አኑሯል፡፡ ወጣቶችን በመቅረጽ እና ልምድን በማካፈል ለኪነ ጥበብ እድገት ትልቅ ሚና ተጫውቷል።

ከአርቲስት ደበበ እሸቱ ጋር በአንድ መድረክ በተደጋጋሚ ከተወኑና አብረው ከሰሩ የጥበብ ባለሙያዎች መካከል ቢኒያም ብርሃኑ ተጠቃሽ ነው፡፡ ቢኒያም ዘወልድን፣ ሀገር ማለትን፣ ጎህ ሲቀድን፣ የብርሃን መንገድን፣ የሀገር ብሌንን ጨምሮ ከ18 በላይ ቴአትሮች ላይ ሰርቷል፡፡ መላ፣ የእኔ መንገድ፣ ጉዞ፣ ዘዴ፣ ሙሽሪት፣ ጥቁር ጉንዳ፣ ንጉስ ቆስጠንጢኖስ እና ሌሎችም ፊልሞች ላይ በድርሰት፣ በዳይሬክተርነትና በተዋናይነት ተሳትፏል። በተጨማሪም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባህል ማዕከል እንዲሁም በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በተጋባዥነት የቴአትር ትምህርት ያስተምራል፡፡ ሌሎች በርካታ የኪነ ጥበብ ስራዎችን በማዘጋጀትም ይታወቃል። ይህ የጥበብ ስራው ደግሞ ከአርቲስት ደበበ እሸቱ ጋር ወዳጅ አድርጎታል። ከቅርበታቸው አንጻርም ሲጠራው አርቲስት ደበበ ሳይሆን “ጋሼ” እያለ ነው፡፡ አርቲስት ደበበ እሸቱና ቢኒያም “ከፈተና ወደ ልዕልና” የሚል ቴአትር በጋራ ሰርተዋል፡፡ የእርቅ መርሃ ግብር ላይም በጋራ ተውነዋል፡፡ “ነቢይ ዜሮ” የተሰኘው ቴአትር ደግሞ ሌላው በጋራ የተወኑበት የጥበብ ስራ ነው፡፡

ቢኒያም ከአርቲስት ደበበ እሸቱ ጋር የተገናኘነው በስራ አጋጣሚ ነው፡፡ የኪነ ጥበብ ስራ ለመስራት ከተገናኘን በኋላ እጅግ ሰው አክባሪና ቅን የኪነ ጥበብ ሰው መሆኑን ተረዳሁ፡፡ እውነተኛ የጥበብ ሰው መሆኑ ከሚታወቅበት አንዱ ሰው አክባሪነቱ ነው፡፡ አርቲስት ደበበ የኪነ ጥበብ መድረክ ላይ የክብር እንግዳ አድርገን ስንጠራው በፍጹም ቅንነት ይገኛል፡፡ ደስ የሚልና ልዩ ሰው ነበር ይላል፡፡

በቀላሉ ከሰው ጋር መግባባት የሚችል ነው፡፡ ከአንጋፋና ወጣት ባለሙያዎች ጋር ስራን መስራት ይችልበታል፡፡ ባለፉት 60 ዓመታት ውስጥ በሀገራችን ኪነ ጥበብ ውስጥ የማይዘነጋ አሻራውን አኑሯል። ከሀገራችንም አልፎ በሆሊውድ ደረጃ መስራት የቻለ ሰው ነው፡፡ ለዚህም “ሻፍት ኢን አፍሪካ” የተሰኘውን ፊልም መጥቀስ ይቻላል ሲል ይጠቅሳል፡፡

“አርቲስት ደበበ እሸቱ በኪነ ጥበብ መድረክ ሁሉ ወጣቶችን በማነቃቃትና ተስፋ በማሳየት ይታወቃል፡፡” በማለትም ቢኒያም አብራርቷል፡፡

አርቲስት ደበበ እሸቱ ተፈጥሯዊ የሆነ የትወና ችሎታ የነበረው ሲሆን፤ የሚተውናቸውን ገጸ-ባህሪያት ማንነት በመላበስ ተመልካችን መማረክም ችሏል፡፡ በተለይም በኢትዮጵያ ቴአትር እና በተለያዩ የፊልም ስራዎች ላይ የነበረው ድርሻ እጅግ የጎላ ነው። በርካታ ተውኔቶች እና የሀገራችን ፊልሞች ላይ ተሳትፎ በማድረግ፣ በብዙ አድናቂዎቹ ልብ ውስጥ ለዘላለም የሚኖር ትውስታ ጥሎ አልፏል፡፡

የአርቲስት ደበበ እሸቱ የጥበብ ሰውነት ከትወና ችሎታም ባሻገር ነበር የሚለው ቢኒያም፣ ስለ ጥበብ ያለው ግንዛቤ ስፋትና ለሀገር ፍቅር ያለው ስሜት የተለየ ነበር። ይህንንም ወደ ሌሎች አርቲስቶች በማስተላለፍ ለብዙዎች መምህር እና አማካሪ ሆኖ ያገለገለ ሰውም ነበር፡፡

የኢፌዴሪ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የኪነ ጥበብ፣ ስነ ጥበብና ፈጠራ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ እና የአዲስ አበባ ባህል እና ኪነ ጥበብ ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) የሰጡት ምስክርነትም የቢኒያምን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

ነብዩ ባዬ፣ “በእውቀት ፍለጋ ጥማት እና ትምህርት፣ በሙያ ሥነ ምግባር፣ ባመነበት በመቆም ጽናት አብሬው ሰርቼ ተጠቅሜያለሁ። በልጅነት አዘጋጁ ሆኜ እሱ ግዙፉ ተዋናይ ሆኖ ስንሰራ ያየሁት ሙያ አክባሪነት ስንቄ ሆኗል” በማለት ሲገልጹት፣ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) በበኩላቸው ደበበ እሸቱን ስመጥር የጥበብ ሰው በማለት ገልጸውታል፡፡

ቢኒያም እንደተናገረው፣ አርቲስት ደበበ እሸቱ የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ታሪክ አካል ነው። የዘመኑን የቴአትር እና የፊልም ጥበብ መሰረት የጣለ እና ለቀጣይ ትውልድ አርቲስቶች ታላቅ አርአያ የሆነ የጥበብ ሰው ነበር። እሱ ለጥበብና በጥበብ አማካኝነት ለሀገር ያበረከተው የማይረሳ አስተዋጽኦ ለዘላለም የሚታወስ ይሆናል።

## ለአርቲስቱ ከተበረከቱ ሽልማቶች በጥቂቱ

አርቲስት ደበበ እሸቱ ዘመን ተሻጋሪ ሃሳቦችንና ስራዎችን አበርክቶ አልፏል። ዋናው ጉዳይ አርቲስቱ በመጪው ትውልድ ዘንድ እንዲታወስ ከስራዎቹ በተጨማሪ ምን መደረግ አለበት የሚለው ነው፡፡

የኪነ ጥበብ ባለሙያው ቢኒያም ብርሃኑ በሌላው ዓለም አንጋፋ አርቲስቶች በህይወት እያሉ ጭምር መታወሻዎች ይሰሩላቸዋል፡፡ አደባባዮች በስማቸው ይሰየማሉ፡፡ ሐውልት ይሰራላቸዋል፡፡ እኛ ሀገር ይህ ባህል ብዙ አልተለመደም ይላል፡፡

የደበበ እሸቱ ስራዎች ከመቃብር በላይ ናቸው፡፡ አበርክቷቸውን ለመግለጽና ለማክበር የጥበብ ትምህርት ቤቶች በስሙ ቢሰየሙ እንዲሁም ጎዳናዎች በደበበ ስም ቢሰየሙ ያንሳል እንጂ አይበዛበትም ሲልም ሃሳቡን አንስቷል፡፡

በእርግጥ ደበበ እሸቱ በህይወት ሳለ በርካታ ሽልማቶችንና እውቅናዎችን አግኝቷል፡፡ ለአፍሪካ ቴአትር ባደረገው አስተዋጽኦ የዚምባብዌን ማላካይት አዋርድ ተሸላሚ ነበር፡፡ ጣይቱ ኢንተርቴይመንት በዋሽንግተን ዲሲ በቴአትር ዘርፍ የህይወት ዘመን ሽልማት አበርክቶለታል፡፡ የጥበብ ሰዎችን ታሪክ በመሰነድ የሚታወቀው ተወዳጅ ሚዲያ እንዳሰፈረው ደግሞ፣ በአትላንታ ጆርጂያ የከተማው ምክር ቤት ለዓለም ቴአትር ላደረገው አስተዋጽኦ ኖቬምበር 24ን “የደበበ እሸቱ ቀን” በሚል ሰይሞታል፡፡

የቀድሞው የኢትዮጵያ ባህል ሚኒስቴርም ደበበ እሸቱን ለኢትዮጵያ ፊልም እድገት ላበረከተው አስተዋጽኦ ሸልሞታል፡፡ በጉማ አዋርድ ደግሞ የህይወት ዘመን ተሸላሚ ነበር፡፡ በተጨማሪም እ.ኤ.አ በ2015 በቫንኮቨር ዓለም አቀፍ ፊልም ፌስቲቫል በምርጥ መሪ ተዋናይ ዘርፍ አሸናፊ በመሆን ተሸልሟል፡፡ በ2015 ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ባበረከተው አስተዋጽኦ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ አበርክቶለታል፡፡

## የአርቲስቱ ሙያዊ አበርክቶ

ክቡር ዶክተር አርቲስት ደበበ እሸቱ ከ40 በላይ ተውኔቶች ላይ ተሳትፏል። ከተወነባቸው ቴአትሮች መካከል እናት ዓለም ጠኑ፣ ዋናው ተቆጣጣሪ፣ የአዛውንቶች ክበብ፣ ኪንግ ሊር፣ ዳንዴው ጨቡዴ፣ ያላቻ ጋብቻ፣ ናትናኤል ጠቢቡ፣ የቬኒሱ ነጋዴ፣ የከርሞ ሰውና ጠልፎ በኪሴ የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

የመንግስቱ ለማን “ጠያቂ”፣ የተስፋዬ ገሰሰን “ተሐድሶ”፣ የአያልነህ ሙላትን “ሻጥር በየፈርጁ”፣ የነጋሽ ገብረማርያምን “የአዛውንቶች ክበብ” እና የዊልያም ሼክስፔርን (የመስፍን አለማየሁ ትርጉም) “ሊር ነጋሲን” (በኋላም “ንጉሥ ሊር”) ጨምሮ 28 ተውኔቶችን አዘጋጅቶ ለእይታ ማቅረቡን የተወዳጅ ሚዲያ እና ህልፈታቸውን አስመልክተው ዘገባ ከሰሩ መገናኛ ብዙሃን መረዳት ይቻላል፡፡

በተዋናይነትና ተርጓሚነት ከተሳተፈባቸው በርካታ የመድረክ ሥራዎቹ ውስጥ ያላቻ ጋብቻ፣ ሮሚዎና ዡልየት፣ ዳንዴው ጨቡዴ፣ የበጋ ሌሊት ራዕይ፣ አንድ ዓመት ከአንድ ቀን፣ እናት ዓለም ጠኑ፣ በቀይ ካባ ስውር ደባ፣ ተሓድሶ፣ ኪንግ ሊር፣ ዋናው ተቆጣጣሪ፣ የወፍ ጎጆ፣ የቬኒሱ ነጋዴ፣ ናትናኤል ጠቢቡ፣ ድብልቅልቅ፣ ጠልፎ በኪሴ፣ ጠያቂ፣ የአዛውንቶች ክበብ፣ ዘ ጌም ኦፍ ቼዝ (በእንግሊዝኛ)፣ አዳ አክ አራክል (በእንግሊዝኛ)፣ ኦቴሎ (በእንግሊዝኛ) ይጠቀሳሉ፡፡

በዓለም አቀፍ የሲኒማ ጥበብ ትወና በብዛት ከተሳተፉት ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ቀደምት የሆነው ደበበ በፊልም ስራም በኢትዮጵያውያን የተዘጋጁ የተለያዩ የሀገር ውስጥ ፊልሞችን ጨምሮ ከሪቻርድ ራውንድትሪና ከሰር ፍራንክ ፊንሊ፣ ከቴሬንስ ስታምፕ፣ ከጃን ሞንሮና ከሂዩ ግሪፍዝ፣ ከሶፊያ ሎሬን ጋር የተወነባቸው ፊልሞች “ሻፍት ኢን አፍሪካ”፣ “ዘ አፍሪካን ስፓይ”፣ ”ዘ ሴይለር ፍሮም ጂብራልታር”፣ “ኤ ሲዝን ኢን ሔል”፣ “ዜልዳ”፣ “ዘ ግሬቨ ዲገር”፣ “ዘ ግራንድ ሪቤሊየን”፣ ሬድ ሊቨስ “ጉማ” በሚሉት ላይም ተሳትፏል፡፡

በስነ ጽሑፍ ዘርፍም “የተዋናይ ሀሁ” መጽሐፍ ለበርካታ የዘርፉ ባለሙያዎች የሙያቸው ፊደል መቁጠሪያ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከትርጉም ሥራዎቹ የሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ “የደም እንባ” መጽሐፍ፣ “ድብልቅልቅ የመድረክ ተውኔት”፣ “ያልታመመው በሽተኛ” እና ሌሎችንም ስራዎች ወደ አማርኛ ተርጎሟል አበርክቶው ከትወና የተሻገረ እንደነበር ማሳያ ነው፡፡

በተጨማሪም ደበበ እሸቱ የአፍሪካ መድረክ ባለሙያዎች ማህበር መስራች፣ የዓለም ኮንቴምፖራሪ ቴአትር ኢንሳይክሎፒዲያ ቦርድ አባል፤ የዓለም አቀፍ ቴአትር ኢንስቲትዩት የአፍሪካ አስተባባሪና የኢትዮጵያ ተጠሪ፤ በብሔራዊ ቴአትር የፕሮግራምና ፕሮዳክሽን ኃላፊ፤ በሀገር ፍቅር ቴአትር የኪነ ጥበብ አገልግሎት ኃላፊ፣ በራስ ቴአትር ዋና ስራ አስኪያጅነት፣ በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በርካታ ማህበራዊ፣ የልማትና እርዳታ አገልግሎቶች ላይ አስተባባሪ፣ የሰላምና እርቅ ኮሚቴ አባል፣ የጌርጌሴኖን የአዕምሮ ህሙማን ማዕከል አምባሳደር፣ በኩላሊት ሞት ይብቃ አምባሳደር በመሆን ያደረገው አስተዋጽኦ ከብዙ በጥቂቱ ይጠቀሳል፡፡

አርቲስት ደበበ እሸቱ የተወለደው በ1934 ዓ.ም አዲስ አበባ ነው። የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የተከታተለ ሲሆን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፐርፎርሚንግ አርትስ ተምሯል። እ.ኤ.አ በ1965 ደግሞ ወደ ሃንጋሪ በማቅናት የቴአትር ጥበብን አጥንቷል። ወደ ሃንጋሪ ከማቅናቱ በፊት በ1964 ዓ.ም ከወ/ሮ አልማዝ ደጀኔ ጋር ትዳር መስርቶ 4 ልጆችንና 8 የልጅ ልጆችን አፍርቷል።

## ህልፈት

የክቡር ዶክተር ደበበ እሸቱ ህልፈተ ዜና የተሰማው ባሳለፍነው እሑድ ነሐሴ 11 ቀን 2017 ዓ.ም ነበር፡፡ በተወለደ በ83 ዓመቱ ያለፈው ደበበ የቀብር ሥነ ስርዓቱ ባሳለፍነው ማክሰኞ ነሐሴ 13 ቀን 2017 ዓ.ም ቤተሰቡ፣ ወዳጅ ዘመዶቹ፣ የሙያ አጋሮቹና የመንግስት የስራ ኃላፊዎች በተገኙበት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል፡፡ የክብር ዶክተር አርቲስት ደበበ እሸቱ የትወና ችሎታው፣ ስለ ኪነ ጥበብ የነበረው ጥልቅ ግንዛቤ እና በስራዎቹ የፈጠረው አይረሴ አበርክቶ ለጥበብ ዓለም ትቶት የሄደው ሀብት ነው።

# ልጆች በክረምት ወቅት ከምን መጠንቀቅ እንዳለባችሁ እናስታውሳችሁ

**በለይላ መሀመድ**

ልጆች እንዴት ከረማችሁ? ክረምቱን እንዴት እያሳለፋችሁት ነው? ይህንን የክረምት ወቅት በጨዋታ፣ በመዝናኛ ስፍራዎች፣ ለቀጣይ ትምህርታችሁ ዝግጅት በማድረግ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በክረምት ወቅት ራሳቸውን ለአደጋ በሚያጋልጥ ቦታ የሚያሳልፉ አንዳንድ ልጆች ይኖራሉ፡፡ ድንገተኛ ጎርፍ ሊከሰት ይችላል፡፡ ተቆፍረው ባልተደፈኑ ጉድጓዶች ውስጥ የዝናብ ውሃ ሊጠራቀም ይችላል፡፡ ልጆች፤ እነዚህ አካባቢዎች ላይ ካልተጠነቀቃችሁ ለአደጋ እንደምትጋለጡ ታውቃላችሁ አይደል? ጎበዞች፡፡ ያነጋገርናቸው ልጆች በዚህ ዙሪያ ያላቸውን ሀሳብ አካፍለውናል፡፡



ፎቶ- በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ህፃን ዮሴፍ ኃይሉ



ፎቶ- በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ህፃን ሲሳይ መላኩ

ህጻን ዮሴፍ ሀይሉ ይባላል፡፡ ያገኘነው አንበሳ ግቢ ፓርክ ሲዝናና ነው፡፡ “የክረምት የእረፍት ጊዜዬን ወላጆቼ አንበሳ ግቢን ጨምሮ በተለያዩ ስፍራዎች እንድዝናና ያደርጉኛል፡፡ የዓድዋ ድል መታሰቢያንም ጎብኝቻለሁ፡፡ ቤተሰቦቼ ወስደው ከሚያዝናኑኝ በተጨማሪ ከሰፈር ጓደኞቼ ጋር ኳስ እና የተለያዩ ጨዋታዎችን እጫወታለሁ፡፡ በዘንድሮው ክረምት በምጫወትበት ወቅት ያጋጠመኝ አንድ ክስተት አለ፡፡ ክረምት እንደገባ ከጓደኞቼ ጋር ስጫወት ጫማዬን ጎርፍ ወሰደብኝ፡፡ ይህ የሆነው እየተጫወትን ባለበት ጊዜ ከባድ ዝናብ በመዝነቡ ነው። እኔና ጓደኞቼ ዝናቡ እስከሚያባራ ድረስ ትልልቅ ሰዎች ከተጠለሉበት ሱቅ ውስጥ በመግባት ተጠልለን አሳለፍነው፡፡ ዝናቡ ከቆመ በኋላ ወደቤታችን ስንሄድ በብዛት የመጣው ጎርፍ የአንድ እግር ጫማዬን ወሰደብኝ፡፡ እኔም በባዶ እግሬ ወደቤቴ ተመለስኩኝ፡፡ ወላጆቼም በዝናብ ወቅት ከቤት መውጣት እንደሌለብኝ መከሩኝ፡፡ ከዛን ቀን በኋላ ዝናብ ቀድሞ ከዘነበ ከቤት አልወጣም፡፡ እየተጫወትን መዝነብ ከጀመረ ደግሞ፤ ሁላችንም ወደቤታችን እየሮጥን እንሄዳለን፡፡” ብሏል፡፡

ህጻን ሲሳይ መላኩ በበኩሉ ከክረምት ጎርፍ ጋር በተያያዘ ያለውን ገጠመኝ ሲገልፅ፤ “ከሁለት ዓመታት በፊት ከጓደኞቼ ጋር ስሯሯጥ ለግንባታ በተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ ገብቼ አውቃለሁ። ከዚያን ጊዜ በኋላ አነስተኛ ኩሬ አካባቢ መንቀሳቀስ እና ውስጡ መግባት እፈራለሁ፡፡ ዝናብ ሲዘንብም ሆነ ከዘነበ በኋላ ወደውጭ አልወጣም፡፡

ምክንያቱም አንዳንድ ጎድጓዳ ስፍራዎች ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ውሀ ይዘው ስለሚቆዩ አካባቢው እስኪደርቅ በጥንቃቄ ነው የምንቀሳቀሰው፡፡” ሲል አብራርቷል፡፡

ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ አንዲት እናት ከክረምት ወቅት ጋር በተያያዘ በህጻን ልጃቸው ላይ የደረሰባቸውን አሳዛኝ አጋጣሚ እንዲህ ያስታውሳሉ፤ “ክረምት ሲመጣ መጥፎ ስሜት ነው የሚሰማኝ፡፡ ምክንያቱም ከሦስት ዓመት በፊት በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ልዩ ስሙ ኮሽም በተባለ አካባቢ በጎርፍ አደጋ የስምንት ዓመት ዕድሜ ላይ ይገኝ የነበረው ልጄ ሊጫወት እንደወጣ ሳይመለስ መቅረቱ ልቤን በሀዘን ሰብሮታል፡፡” ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ደሳለኝ ፉፋ ለልጆች ባስተላለፉት መልዕክት “ልጆች፤ በክረምት ወቅት ዝናብ ይጥላል፡፡ ዝናቡ ደግሞ ጎርፍ ያስከትላል፡፡ ጎርፍ ደግሞ ተገቢ ጥንቃቄ ካልተደረገበት በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡ አንዳንድ ወንዞች ደግሞ በክረምት ወቅት ይሞላሉ፡፡ የዋና ችሎታ ሳይኖራችሁ እንዋኛለን ብላችሁ መግባት የለባችሁም፡፡ እንዲሁም ማዕድን ለማውጣት የተቆፈሩ ጉድጓዶች በክረምት ወቅት በጎርፍ ስለሚሞሉ ልጆች እንዲህ አይነት ጉድጓዶች ውስጥ ትንሽ መስሏችሁ ከመግባት ልትቆጠቡ ይገባችኋል፡፡ ሌላው በከባድ ዝናብ የሚፈጠር የሜዳ ጎርፍን በመናቅ ጎርፍ ውስጥ ከመግባት ራሳችሁን መጠበቅ አለባችሁ” ብለዋል፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ሊሰርቅ ሲመጣ በስውር ፤ ሰርቆ ሲወጣ በግርግር**

**መልስ፡-** ሐ. ሞት

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ከመሬት ወድቆ አንስቼ ብይዘው አለቀ**

ሀ. ሳንቲም

ለ. በረዶ

ሐ. ልብስ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ተቋሙ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ምን ሰራ?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

የመንገድ መብራት የከተሞች የስልጣኔ፣ የዘመናዊነት፣ የገፅታና ውበት መገለጫ ነው፡፡ በምሽት እና በሌሊት የሚደረግ የሰዎችና የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ደህንነቱ የተጠበቀና የተሳለጠ እንዲሆን በማድረግም ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት በወጣው በአዋጅ ቁጥር 84/2016 መሰረት፤ በደንብ ቁጥር 166/2016 ዓ.ም የተቋቋመው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን በ2017 ዓ.ም ህዳር ወር ላይ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ያስተዳድራቸው የነበሩ የመንገድ መብራቶችን ርክክብ በማድረግ ወደ ስራ ገብቷል፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰብስብ ሁሴን እንደገለፁት መስሪያ ቤቱ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ አዲስ አበባ እያሳየች ካለው ፈጣን እድገት አኳያ ለነዋሪዎቿ የምትስማማ፣ ዘመናዊ፣ ቀንና ምሽት የሚሰራባት ከተማ እንድትሆን ለማስቻል የመንገድ መብራት የሚኖረውን ፋይዳ በመገንዘብ ነው፡፡

26 ተልዕኮዎችን ተረክቦ እየሰራ የሚገኘው መስሪያ ቤቱ፤ እነዚህ ተልዕኮዎች በከተማዋ ባሉ መንገድ መብራቶች ላይ የሚያጠነጥኑ መሆናቸውን ገልፀው፤ የመንገድ መብራት መሰረተ ልማቶችን የማስጠበቅ፣ የማልማት፣ የማስተዳደር እንዲሁም የመጠገንና ክትትል የማድረግ ስራዎችም ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡

በዚህ መሰረትም ወደ ስራ በገባበት የመጀመሪያ የ2017 በጀት ዓመት ከተሰሩ ስራዎች ውስጥ ከተማ አስተዳደሩ በሚያከናውነው የወንዝ ዳርቻዎችን ጨምሮ የኮሪደር ልማት ስራ ላይ በመሳተፍ ውጤታማ የመብራት ፖል መሰረተ-ልማት ዝርጋታና ተከላ ተከናውኗል፡፡ አገልግሎት የማይሰጡ ተብለው የተለዩትንና ለረጅም ጊዜ የህብረተሰቡ ቅሬታ የነበሩ የመንገድ መብራቶች የተያዘውን ዕቅድ በሙሉ ከሚመለከታቸው አካላትና ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ በመሆን በመጠገን የነዋሪውን የምሽት እንቅስቃሴ ምቹና ሰላማዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

ባለስልጣኑ ከዚህ ባሻገር የተገነቡ የስማርት ፖሎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የአንድ ማዕከል የቴክኖሎጂ ስራን በመስራት ከ75 በመቶ በላይ አፈፃፀም መድረሱንም አንስተዋል። ለእነዚህ ለተሰሩ ስራዎች የተለያዩ ተቋማትና የማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎም ትልቅ ሚና እንደነበራቸው ያነሱት አቶ ሰብስብ፤ የመንገድ መሰረተ ልማት ሲሰራ የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ መንገዶች ባለስልጣን፣ ኢትዮ ቴሌኮም



**ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰብስብ ሁሴን**

እንዲሁም የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ ሃይል የመሳሰሉት ተቋማት ጋር በጋራ ጥምረት በመፍጠርና መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም እየተሰራ ይገኛል፡፡

ባለስልጣኑ በተቋቋመ በአጭር ጊዜ ውስጥ የነበረውን ውስን የሰው ሀይልና የግብዓት አቅም አስተባብሮና አቀናጅቶ በመጠቀም ተልዕኮውን በብቃት መወጣት ቢችልም የተለያዩ ፈተናዎችም አጋጥመው እንደነበር ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ሰብስብ ያነሳሉ፡፡ ለአብነት ከ15 እና 20 ዓመታት በፊት ተሰርተው ለማህበረሰቡ አገልግሎት ሳይሰጡ የቆዩ የመንገድ መብራቶች አንዳንዶቹ ባለቤት አልባ መሆናቸው እንዲሁም ቀደም ብሎ ሌላ ተቋራጭ ይዟቸው የነበሩ በመሆኑ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተረክቦ ወደ ስራ ለመግባት ፈተና ሆኖበት ቆይቷል፡፡

እነዚህንም ችግሮች ለመፍታት ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ከሸሮ ሜዳ እንጦጦ፣ ከኮተቤ አራራት፣ ጀሞ 2 ኮንዶሚኒየም እና ቤተል 40 ችግሮቹ ተፈትተው ወደ ስራ የገቡና ርክክብ የሚደረግባቸው እንደሆኑ አቶ ሰብስብ ገልፀውልናል፡፡

ባለስልጣኑ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ዘመናዊ የመንገድ መብራት ተጠቃሚ በማድረግ፣ የተበላሹትን በመጠገንና በማደስ በርካታ ስራዎችን አከናውኗል። በተለይ የኮሪደር ልማት በተሰራባቸው 12 አካባቢዎች አዳዲስ ስማርት ፖሎችን በመትከል ለህብረተሰቡ ምቹ እንቅስቃሴ መፍጠር ተችሏል፡፡ ከእነዚህ መካከል በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ተገንብቶ ለአገልግሎት የበቃው ከአራት ኪሎ እስከ እንጦጦ ያለው አካባቢ ተጠቃሽ ነው፡፡

የዝግጅት ክፍላችንም ቅኝት ባደረገበት ወቅት እንደተመለከተው ከአራት ኪሎ እስከ እንጦጦ በተሰራውና ለአገልግሎት በበቃው የኮሪደር ልማት የተተከሉ ስማርት ፖሎቹ አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብና አዲስ እንድትሆን እንዲሁም ነዋሪዎቿ ያለምንም ችግር በእግርና በትራንስፖርት ቀንና ምሽት እንዲንቀሳቀሱ ዕድል ፈጥሯል፡፡ የነዋሪዎች አስተያየትም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ አቶ ጫላ ጫንታ የሸሮ ሜዳ ነዋሪና የዋን ላቭ ትምህርት ቤት የጥበቃ ሰራተኛ ናቸው፡፡ የበፊቱን ሸሮ ሜዳ አሁን ካለው ጋር ሲያነፃፅሩ “ልዩነቱ የድሃና የሃብታም ሳይሆን የሰማይና የምድር ያህል ነው” በማለት አስተያየታቸውን ይጀምራሉ፡፡ ከዚህ በፊት ጨለማ ከመሆኑ የተነሳ የተለያዩ ዝርፊያዎች፣ ስርቆቶች ስለሚያጋጥሙ በምንፈልገው ሰዓት መንቀሳቀስ የማያስችል ነበር፡፡ የመንገዱ መጥበብ እና መብራቱ በአንድ አቅጣጫ ብቻ በመሆኑ የመኪና አደጋ ሲከሰት መቆየቱንም ያስታውሳሉ፡፡

“መቆየት ደግ ነው” የሚሉት አቶ ጫላ፤ በኮሪደር ልማቱ የሸሮ ሜዳ መንገድ ሰፍቶና ስማርት ፖሎች ተተክለውለት ለእይታ ማራኪ፣ እንደልብ በሰፊው መንገድ መንቀሳቀስ የሚያስችልና በጨለማ ምክንያት የሚከሰቱትን የወንጀል ድርጊቶች ያስቀረ ነው፡፡ ለእኔም የምሰራው መንገድ ዳር በመሆኑ ምንም አይነት ችግር ይደርስብኛል ብዬ እንዳልሰጋ አድርጎኛል ሲሉ መደሰታቸውን በሚገልፅ ገፅታና አንደበት

> “የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ዘመናዊ የመንገድ መብራት ተጠቃሚ በማድረግ፣ የተበላሹትን በመጠገንና በማደስ በርካታ ስራዎችን አከናውኗል”

የተሰማቸውን አጋርተውናል፡፡

ሌላኛዋ ከአራት ኪሎ እስከ እንጦጦ በተሰራው የኮሪደር ልማት መደሰታቸውን የገለፁልን የአካባቢው ነዋሪ ወይዘሮ እታለም ወልደማርያም ናቸው፡፡ የመንገድ መብራቶቹ ዘመናዊ መሆናቸውና መንገዱም ተሰርቶ አገልግሎት መስጠቱ ማህበረሰቡን ከተለያዩ ችግሮች የሚታደግ እና ለገፅታ ግንባታም አበርክቶው ከፍተኛ መሆኑን ወይዘሮዋ አክለዋል፡፡

ተቋሙ በከተማዋ የመንገድ ዳር መብራቶችን ከመገንባት፣ ለብልሽት የሚዳረጉትን በመጠገንና እድሳት በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጡ፣ በማስቻል መሰረተ ልማቶቹም እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

የተሰሩት የመንገድ መብራቶች ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ የጥበቃ እንዲሁም በመሰረተ ልማቱ ላይ ጉዳት ያደረሱ አካላት ሲገኙ ደግሞ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ እንዲሁም ማህበረሰቡ በተቋሙ ነፃ የጥሪ ማዕከል በ9101 ጥቆማ በመስጠት በጋራ በመሆን የሚያጋጥሙ የስርቆት እና የግጭት ወንጀሎችን መቀነስ እና ንብረቶችን የመጠበቅ ስራ መሰራቱን ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

በመንገድ መብራት መሰረት ልማቶች ላይ ተሽከርካሪዎች የሚያደርሱት ጉዳት ለተቋሙ ተግዳሮት የነበረ ሲሆን፤ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር፣ የሚያጠፉትን ደግሞ ተጠያቂ በማድረግ መሰረተ ልማቱን የመጠበቅ ስራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ወደፊትም ከተቋማቱ ጋር በመቀናጀት የሚሰራው ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ነው አቶ ሰብስብ የሚያብራሩት፡፡

በቅርቡ የአዲስ አበባ ከተማ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ከተጠሪ ተቋማት ጋር በተገኙበት ባደረገው የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም የማጠቃለያ ጉባኤ ላይ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ላከናወነው የመንገድ መብራት መሰረተ-ልማት ስራ እውቅና እና ምስጋና ተበርክቶለታል፡፡

ተቋሙ በ2022 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ መብራት አገልግሎት ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ የጠበቀ ሆኖ የማየት ራዕይን አንግቦ እየሰራ ይገኛል። ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በ2017 በጀት ዓመት የነበሩ ክፍተቶችን በማረምና ጥንካሬዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል ተወዳዳሪና ብቁ ተቋም ለመሆን አቅዶና በጀት መድቦ በተያዘው በጀት ዓመት ለበለጠ ውጤት እንደሚተጋ አቶ ሰብስብ አመላክተዋል፡፡

ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየወሩ የሚቀርብ

# አካታቹ የእውቀት ቤት



ፎቶ- በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ
መስማት የተሳናቸው ሰልጣኞች በምልክት ቋንቋ አስተርጓሚነት የተግባር ልምምድ ሲያደርጉ

### በሰገነት አስማማው

አቤኔዘር አበበ መስማት የተሳነው ወጣት ነው፡፡ የአካል ጉዳቱ ሳያግደው ጉዳት አልባ ከሆኑ ሰልጣኞች እኩል በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በስዕል ዘርፍ በደረጃ አራት የአንደኛ ዓመት ስልጠናውን አጠናቅቋል፡፡ በዚህ ዘርፍ ለመሰልጠን ያበቃውን አጋጣሚ፣ “የ8 ዓመት አካባቢ ልጅ እያለሁ በቴሌቪዥን የአሻንጉሊት ፊልም እመለከት ነበር፡፡ ቤተሰቦቼም አሻንጉሊቶችን እያየሁ ስዕል እንድስል ያበረታቱኝ ነበር፡፡ የእነሱን ሐሳብ ተቀብዬ የአሻንጉሊት ስዕል መሳል ጀመርኩ፡፡ የቤተሰቦቼ መልካም ግፊት እና የእኔም ፍላጎት ታክሎበት ዛሬ ላይ የመሳል ፍላጎቴን በትምህርት ለማዳበር በዘርፉ መሰልጠን ቻልኩ፡፡ ይህም ሀሴትን ፈጥሮልኛል” ሲል አጫውቶናል፡፡

ሰልጣኝ አቤኔዘር እንደሚገልፀው፤ በኮሌጁ የሚሰጠው የልዩ ፍላጎት ስልጠና በንድፈ ሃሳብና በተግባር በአስተርጓሚ ተደግፎ ነው፡፡ አሰልጣኞችም እገዛ ያደርጉልናል፡፡ “መስማት ለተሳናቸው ትኩረት በመስጠት እንደማገኘውም ዜጋ በኮሌጅ ደረጃ በምንፈልገው የትምህርት ዘርፍ እንድንሰለጥን በመደረጉ ኮሌጁንም መንግስትንም ሳላመሰግን አላልፍም” ሲልም አክሏል፡፡ ስልጠናውን ሲያጠናቅቅም ለሌሎች እሱን መሰል ዜጎች በስዕል ዘርፍ ያለውን እውቀት ለማካፈልና የትምህርት ደረጃውንም ከፍ የማድረግ ዓላማ እንዳለው ጠቁሟል፡፡

ሌላዋ መስማት የተሳናት ወጣት ቀለሟ ተስፋዬም በደረጃ አራት በልብስ ስፌት ስልጠናዋን አጠናቅቃለች፡፡ “ስምንተኛ ክፍል ሆኜ በትምህርት ቤታችን ፋሽን ሾው መርሃ ግብር ሲካሄድ እመለከት ነበር፡፡ ሳድግ የፋሽን ዲዛይነር መሆን እንዳለብኝ ፍላጎት አደረብኝ፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮ በአዕምሮዬ ተቀርፆ አሁን በኮሌጅ ደረጃ ለመሰልጠን በቅቻለሁ” ብላለች። የግሏን የልብስ ስፌት ቤት መክፈትና በተለይ ፋሽን ሾው ለሚያሳዩ የተለያየ ዲዛይን ያላቸውን ልብሶች የማዘጋጀት ራዕይ እንዳላት ትናገራለች፡፡

በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የልዩ ፍላጎት ስልጠና አስተባባሪ አቶ ያሬድ ጨሞ በሰጡት መረጃ፣ ኮሌጁ የተለያየ የአካል ጉዳት ያለባቸው ዜጎች በልዩ ፍላጎት ሰልጥነው የሙያ ባለቤትና ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ እየሠራ ይገኛል፡፡ የልዩ ፍላጎት ስልጠና መስጠት የተጀመረው በ1994 ዓ.ም ነው፡፡ በወቅቱ መስማት የተሳናቸውን፣ ዓይነ ስውራንን፣ የእጅና የእግር ጉዳት ያለባቸውን ዜጎች በልብስ ስፌትና በስነ ጥበብ ዘርፍ ያሰለጥን ነበር፡፡

አስተባባሪው እንደሚገልፁት፤ የልዩ ፍላጎት ስልጠና ክፍል ሲሰጥ የነበረ ቢሆንም ራሱን ችሎ መስራት የጀመረው ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ሌሎች አካል ጉዳት ያለባቸው ሰልጣኞች ተጨማሪ አሰልጣኝ ሳያስፈልግ በክፍል ውስጥ ባለ አሰልጣኝ ብቻ የሚማሩ ሲሆን መስማት ለተሳናቸው ዜጎች ግን የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች በመቅጠር ነበር ስልጠናው ሲሰጥ የቆየው፡፡ የስልጠና ክፍሉ ራሱን ችሎ መስራት ከጀመረ በኋላ ሰባት የአካል ጉዳት ካለባቸው አሰልጣኞች በተጨማሪ አራት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አሰልጣኞች በቋሚነት ተመድበው ስልጠናው እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ከስልጠና ዘርፎች መካከልም ኮንስትራክሽን፣ አውቶሞቲቭ፣ ቢዝነስ፣ ስዕል፣ ልብስ ስፌት ይገኙበታል ብለዋል።

አቶ ያሬድ እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት ለልዩ ፍላጎት ሰልጣኞች ብቻ የሚሆን ራሱን የቻለ መፀዳጃ ቤት እንዲሁም መስማት ለተሳናቸው ሰልጣኞች መውጫና መውረጃ (ራምፕ) ተሰርቷል፡፡ በኮሌጁ መግቢያና መውጫ በር ለአብነት እንኳን ደህና መጣችሁ! በግቢው መስማት የተሳናቸው ሰልጣኞች ስላሉ በዝግታ ያሽከርክሩ! የሚል በምልክት ቋንቋ በባነር ተሰርቷል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት መጋቢት ወር ላይ 90 ለሚሆኑ አሰልጣኞች፣ ለዲፓርትመንት ኃላፊዎች፣ ለተቋሙ አስተዳደር ሰራተኞች መሰረታዊ የምልክት ቋንቋ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ይህም መስማት ለተሳናቸው ሰልጣኞች አቅጣጫ ከማሳየት ጀምሮ ሌሎች አስፈላጊ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው የሚያስችል ስልጠና እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

መስማት ለተሳናቸው ሰልጣኞች ያሉት አስተርጓሚዎች በቂ ባለመሆናቸው ተጨማሪ አስተርጓሚዎችን ማሟላት፣ ዓይነ ስውራን በኮምፒዩተር መፃፍ እንዲችሉ የሚረዳቸውን “ጃውስ” የተሰኘ ሶፍትዌር እንዲሰለጥኑ የማድረግ፣ የተቋሙ ማህበረሰብ ስለ ልዩ ፍላጎት ትምህርት በሚገባ እንዲረዳ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎች በቀጣይ በትኩረት የሚሰሩ መሆናቸውን አቶ ያሬድ ጠቁመዋል፡፡

የኮሌጁ ማህበረሰብ ለልዩ ፍላጎት ሰልጣኞች በልዩ ሁኔታ የበኩሉን ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡ ከግቢ በር ጀምሮ በመማሪያ ክፍልና በምድረ ግቢው ውስጥ ባሉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ አቅጣጫ ከማሳየት ጀምሮ መደገፍና መንከባከብ እንደሚገባ አቶ ያሬድ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

በ2016 ዓ.ም በደረጃ አራት በልብስ ስፌት 2 ሴት፣ በፀጉር ስራ 2 ሴት፣ በአውቶሞቲቭ 1 ወንድ፣ በቢዝነስ ወንድ 2፣ ሴት 1 በአጠቃላይ ስምንት መስማት የተሳናቸው ዜጎች ሰልጥነው ተመርቀዋል። ዘንድሮም በደረጃ አራት በልብስ ስፌት፣ በስዕል፣ በአውቶሞቲቭ፣ በምግብ ዝግጅት ዘርፎች 27 መስማት የተሳናቸው ዜጎች እየሰለጠኑ መሆኑንም አስተባባሪው ገልፀዋል፡፡

አካል ጉዳተኞች በማንኛውም መስክ የመማርና የመስራት ፍላጎትና ብቃት እንዳላቸው በተለያዩ የስራ መስኮች ተሰማርተው የሚገኙት ዜጎች ምስክር ናቸው፡፡ እነዚህ ዜጎች በሚፈልጉት ዘርፍ የመማር እድልም ሊኖራቸው ይገባል። ከዚህ አኳያ ተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በልዩ ፍላጎት ስልጠና ዘርፍ በተለይም መስማት ለተሳናቸው ዜጎች እያከናወነ ያለው ተግባር የሚደነቅ ነው። ሌሎች የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችም ተሞክሮውን በመቀመር መስራት ይኖርባቸዋል መልዕክታችን ነው፡፡

## የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት

### የአካቶ ትምህርትን አስፈላጊ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

- የተጠቃሚዎችን የኑሮ ደረጃ ከማሻሻሉም ባሻገር ለራሳቸው ክብርና ዋጋ ለመስጠት፤
- ስሜትን ያዳበሩ አምራች ዜጎችን ለማፍራት ስለሚያስችል፤
- ለግለሰቦችም ሆነ ለማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ስለሚያስገኝ፤
- መድልዎን በማጥፋትና ማህበራዊ ዕኩልነትን በማስፋፋት ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብን ለመፍጠር አስተዋፅዖ ስለሚያበረክት፤
- የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በማጠናቀቅ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለመምታት ስለሚረዳ፤
- ልዩ ትምህርት ቤቶችን ከማቋቋም ይልቅ አካቶ ትምህርትን መተግበር ወጭ ቆጣቢና አዋጭ በመሆኑ፤
- አካቶ ትምህርት ሁሉም ልጆች በትምህርት ቅስሞሽ (learning) ውስጥ ችሎታቸውን እንዲያውቁ፣ እንዲያዳብሩና እርስ በእርስ እንዲማማሩ ስለሚረዳ፣
- አካል ጉዳተኛ ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር እየኖሩ እንዲማሩ ስለሚያስችል፤
- የትምህርት አመራሩ ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ አገልግሎት ለመስጠት ስለሚያስችለው ነው።

**ምንጭ፡-**

ትምህርት ሚኒስቴር

# ተሻጋሪው ኃላፊነት

**በሄለን ጥላሁን**

የአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በ34 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፤ በውስጡም ከህክምና ጋር የተያያዘ አገልግሎት የሚሰጡ እድሜ ጠገብ ህንፃዎች አሉ፡፡ ከሕንፃዎቹ እና ከቅጥረ ግቢው ጋር በተጣጣመ መልኩ የተተከሉ የተለያየ ዝርያ ያላቸው ዛፎችም ይገኛሉ፡፡ ወደ ቅጥር ግቢው ውስጥ እግር ጥሎት የተገኘ ሰው በቅድሚያ አይኑ የሚያርፈው፤ በተዋበው የአትክልት ስፍራዎቹ ላይ ነው፡፡ የግቢው አትክልት ለታመመ፤ ሕመሙን አስረስቶ የጤና እስትንፋስን የሚቸር፣ ለግቢው ማህበረሰብ ደግሞ መልካም የሥራ ከባቢን የሚያድል ነው፡፡ በአግባቡ በተዘጋጀው የአትክልት ሥፍራ የተተከሉ እፅዋት ለጥላ፣ ለምግብነት ብሎም ለመድኃኒትነት አገልግሎት የሚውሉ መሆናቸው ደግሞ አንጋፋው የጤና ተቋም ለዘርፉ የሰጠውን ከፍ ያለ ትኩረት አመላካች ነው፡፡



ፎቶ- ከፋይል

የአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አረንጓዴ ልማት ከፊል ገጽታ

ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ መንደር የጋራ መኖሪያ ቤት ባለንብረቶች ማህበር አረንጓዴ ልማት ከፊል ገጽታ

ፅዱ፣ ምቹ እና ለሥራ ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢን መፍጠር ለነገ የሚባል ተግባር እንዳልሆነ የሚናገሩት የሆስፒታሉ ዋና ስራ አስኪያጅ ዶክተር ሽመልስ ገዛኸኝ፤ "ሁሉን አቀፍ አገልግሎት እየሰጠ መገኘቱን ተከትሎ ለአረንጓዴ ልማት ሥራዎችም የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ተቋሙ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችን በስፋት ማከናወን የጀመረው ከአራት ዓመት በፊት ነው፡፡ ዛሬ ላይ ይህ ሥራ እንደሆስፒታል ተጨባጭ ውጤት እያመጣ ይገኛል፡፡ ለዚህ ደግሞ፤ የተንጣለለውን የሆስፒታሉን ቅጥር ግቢ በአግባቡ መጠቀም መቻሉ ነው" በማለት አብራርተዋል፡፡

እንደ ዋና ስራ አስኪያጁ ገለፃ፤ በሆስፒታሉ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠሩ ዛፎች አሉ፡፡ ከአራት ዓመት ወዲህ ተግባራዊ በተደረገው ተቋማዊ አረንጓዴ ልማት ሥራም አዳዲስ ዕፅዋት ተተክለዋል፤ በባለሙያ የታገዘ እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይገኛል። የእንክብካቤውን ሂደት የሚከታተል እና የሚቆጣጠር ራሱን የቻለ ግብረ ሃይልም ተቋቁሟል፡፡ የውሃ አቅርቦት ችግር ቢያጋጥም እንኳን በቦቴ በማቅረብ የእፅዋቱ እንክብካቤ ሳይቋረጥ የሚቀጥልበት አሠራር እንደባህል ተይዞ እየተተገበረ ይገኛል፡፡

ለሀገር በቀል ዕፅዋት ትኩረት የሚሰጠው ሆስፒታሉ፤ በቅጥረ ግቢው ከተተከሉት ዕፅዋት መካከል፡- እንደ ወይራ፣ ብርብራ፣ ዋንዛ፣ ዝግባ የመሳሰሉ ሀገር በቀል ዛፎች በስፋት ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም፤ እንደ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ዘይቱና የመሳሰሉትን ለምግብነት የሚውሉ አትክልቶችን በመትከል ከፍሬያቸው መጠቀም ተጀምሯል፡፡ በተጨማሪም ለህክምና አገልግሎት ጥቅም ከሚሰጡ እፅዋት ጭምር አስፈላጊው ውጤት መገኘቱን የሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ አብራርተዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ አክለው እንደገለጹት፤ በሆስፒታሉ ቁጥራቸው 30 የሚሆኑ የጉልበት ሰራተኞች ችግኞችን በማረም፣ በመኮትኮት እንዲሁም ውሃ በማጠጣት ሥራ ተሰማርተዋል፡፡ የዕፅዋትን እንክብካቤ ሂደት የሚከታተለው እና የሚቆጣጠረው ግብረ ሃይል ሚናም፤ የአተካከል ችግር ያለባቸውን የማስተካከል፣ በበጋ ወቅትም እፅዋቱ ያሉበትን ደረጃ በቅርበት የመከታተል፣ የፅድቀቱን ውጤታማነት በዞን በዞን በመከፋፈል ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡

> **"ከተማዋ በሁሉም መዳረሻዎች በምታከናውናቸው ዘርፈ ብዙ የመሰረተ ልማት ስራዎች ላይ በመሪ ፕላን መሰረት የአረንጓዴ ልማትም ተቀናጅቶ እየተተገበረ ይገኛል"**

ዶክተር ሽመልስ አክለውም፤ "የሆስፒታሉ አመራርና ሠራተኛ በቅጥር ግቢ ያልተወሰነ የአረንጓዴ ልማት ተሳትፎ አላቸው፡፡ በአዲስ አበባ ዙሪያ በሚገኘው የሸገር ከተማ አስተዳደር በመጓዝ፤ በኤጀሬ እና በሆለታ አካባቢ በመገኘት ችግኞችን ተክለናል፡፡ በእንጦጦ አካባቢ ለጤና ሚኒስቴር በተሰጠው የመትከያ ቦታ ላይ ሆስፒታሉ ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆኑን ቀጥሎበታል፡፡ በአራት ዓመታት ውስጥም ሆስፒታሉ በሠራቸው የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች በጤና ሚኒስቴር እንዲሁም በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት እውቅና ተሰጥቶታል" ብለዋል፡፡

ሌላው በተለይ ሀገር በቀል ዛፎችን፣ የፍራፍሬ ተክሎችን ጨምሮ የተለያዩ ዕፅዋትን በስፋት እያለማ ያገኘነው የአዲስ መንደር የጋራ መኖሪያ ቤት ባለንብረቶች ማህበር ነው፡፡ ማህበሩ ከአያት አደባባይ ወደ መቄዶንያ የአዕምሮ ሕሙማንና የአረጋዊያን ማዕከል በሚወስደው መንገድ በስተቀኝ ይገኛል፡፡ በ20 ሺህ ካሬ ሜትር መሬት የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን በነዋሪው የጋራ ተሳትፎ እያለማ ይገኛል። እንደ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ካሮት፣ ቲማቲም እና ድንች ያሉትን በስፋት እያመረተ ነው። የተሰበሰበውን ምርት ደግሞ ለመንደሩ ነዋሪዎች በፍትሐዊነት ያሰራጫል፡፡ ቁጥራቸው አንድ ሺህ የሚሆኑ የሙዝ፣ ኢንጆሪ፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ እና ቡና ዝርያዎችን ተክሏል፡፡

አቶ ሰለሞን ፀሐይ የማህበሩ ሰብሳቢ እና በማህበሩ የአረንጓዴ ልማት አምባሳደር ናቸው፡፡ "አረንጓዴ ሥፍራ እኔነቴን ይስበዋል" የሚሉት አቶ ሰለሞን፣ እያንዳንዱ ነዋሪ ሀገር በቀል የሆኑ የጥላ ዛፎችን በመትከል እንዲሁም ደግሞ ግቢያቸውን ለማሳመር የውበት ተክሎችን ጭምር እንዲተክሉ በኮሚቴዎች ክትትል ይደረጋል፡፡ ማህበሩ ይህን የመሰለ የአረንጓዴ ልማት ሥራ በመኖሪያ ግቢው ውስጥ እንዲሁም በአካባቢው ላይ የመትከል ተግባሩን የጀመረው በ2011 ዓ.ም. ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የማህበሩ አባላት ጥሩ ተሳትፎ በማድረግ ሥራውን አስቀጥለውታል፡፡ በየጊዜው ለተክሎች ያለንን አመለካከት በማሳደግ መሻሻሎችን ማሳየት ተችሏል፡፡ የሚታይ ለውጥ እንድናመጣም የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽህፈት ቤት በቅርበት በመሆን ሙያዊ ድጋፍ እንዲሁም የዘር አቅርቦትን በማመቻቸት ጭምር ተገቢውን እገዛ አድርጓል" ብለዋል፡፡

"የተተከሉ ችግኞችን የፅድቀት መጠን ከዚህ በላቀ ከፍ ለማድረግ በበጋም ጭምር ሳይቋረጥ ይፈፀማል። በበጋ ወቅት ዕፅዋቱን ለመንከባከብ አካባቢያችን ከሚገኘው ወንዝ እንዲሁም የራሳችን የጉድጓድ ውሃ በማውጣት እንጠቀማለን።" የሚሉት አቶ ሰለሞን፤ የማህበሩ አባላት ስድስት ቋሚ አትክልተኞችን ቀጥረው እያሰሩ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ማህበሩ በሰራቸው የአረንጓዴ ልማት ስራዎች የተለያዩ እውቅና እና ሽልማቶችን አግኝቷል፡፡ በወረዳ እና በክፍለ ከተማ ደረጃ በአረንጓዴ ልማት ሥራው በተደጋጋሚ ሞዴል ተደርጎ የሚጠቀስ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በአካል በመገኘት ያደረጉትን ጉብኝት እና የሠጧቸውን ማበረታቻ የማህበሩ አባላት የማይዘነጉት መሆኑን አቶ ሰለሞን ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የአረንጓዴ ቦታዎች አያያዝ ክትትልና ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ አጥናፉ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት፤ ከተማዋ በሁሉም መዳረሻዎች በምታከናውናቸው ዘርፈ ብዙ የመሰረተ ልማት ስራዎች ላይ በመሪ ፕላን መሰረት የአረንጓዴ ልማትም ተቀናጅቶ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን፣ የዘላቂ ማረፊያ እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎችን በውበት ሚዛን እየለካ ለከተማዋ የአረንጓዴ ገፅታ ግንባታ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የሚሰራ ስለመሆኑም አስረድተዋል፡፡

እንደ አቶ ሲሳይ ገለፃ፤ በከተማዋ መዋቅራዊ ማስተር ፕላን መሰረት 30 በመቶ የሚሆነው ቦታ ለአረንጓዴ ልማት የተመላከተ ነው፡፡ የለሙ አረንጓዴ ስፍራዎችን ሙሉ ለሙሉ አረንጓዴነታቸውን አስቀጥሎ መሄድ የቢሯችን ተልዕኮ ነው፡፡ ካለፉት ዓመታት በተለየ ሁኔታ ፅድቀቱ ላይ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ለዚህም ዘላቂነት ያለው የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን በስፋት ለመስራት ያስችል ዘንድ ለከተማዋ ተስማሚ የሆኑ ዝርያዎችን እንደ አየር ንብረቱ ባህሪ በማጥናት ችግኞችን በ11ዱም ክፍለ ከተሞች የችግኝ ጣቢያዎችን በማቋቋም የማፍላት ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

አረንጓዴ ቦታዎችን ከመንከባከብ አንፃር ዓመቱን ሙሉ አረንጓዴነታቸውን ጠብቀው እንዲቀጥሉ የሳር ክርከማ፣ የአረም ማረም፣ ኩትኳቶ፣ ለም አፈር በማኖር፣ ማዳበሪያ ለሚያስፈልገው እንዲሁ ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ ፅድቀቱ ላይ በስፋት እየተሰራ ነው፡፡ በበጋ ወቅት የተተከሉ ችግኞች እንዳይደርቁ በተለይም የውሃ እጥረት እንዳይገጥም የጉድጓድ ውሃን በፓንፕ በመሳብ ተክሎች ውሃ እንዲያገኙ እየተደረገ ነው። በተጨማሪም በውሃ ማጠራቀሚያ ውሃ በመሙላት እና በውሃ ቦቴዎች አማካኝነት የማጠጣት ስራ በባለሙያዎች የሚሰራ ስለመሆኑ አስረድተዋል፡፡

ዕፅዋትን የማልማት ስራ ከተሰራ በኋላ የመፅደቅ ሂደቱን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት ምልከታ ይደረጋል። ለክትትል ያመቹ ዘንድ የአረንጓዴ ቦታን በባለቤትነት ለማልማት ፍቃድ የሚሰጣቸው ግለሰቦች አልያም ተቋማት የውል ሰነድ ይፈራረማሉ፡፡ እፅዋትን ለማልማት፣ ለመንከባከብ እንዲሁም

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## የመንገድ... ከገጽ 8 የዞረ

የጋዜጣዋ የዝግጅት ክፍል የፕሮጀክቱ አሁናዊ አፈጻጸም ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ሲልም የፕሮጀክቱን ተጠሪ መሀንዲስ ኢንጂኒየር ሰውነት ተሰራን አነጋግሯል፡፡ እንደ ኢንጂኒየር ሰውነት ገለጻ፤ ፕሮጀክቱ የተጀመረው መስከረም 15 ቀን 2015 ዓ.ም ነው፡፡ ፕሮጀክቱ አጠቃላይ የሚፈጀው 1 ቢሊዮን 302 ሚሊዮን ሰባት መቶ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ነው፡፡ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ወደ ስራ ቢገባም በተያዘለት የጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቁ 243 ቀናት (ስምንት ወር ከሶስት ቀናት) ተጨማሪ የማጠናቀቂያ ጊዜ ተሰጥቶት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ የመንገዱ አጠቃላይ ርዝመት 5 ነጥብ 67 ኪሎ ሜትር ሲሆን ከዚህም ውስጥ 3 ነጥብ 4ቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ቀሪው 2 ነጥብ 27ቱ በሸገር ከተማ አስተዳደር ውስጥ ይገኛል፡፡ የመንገዱ ጠቅላላ ስፋት 30 ሜትር ነው፡፡ የአስፋልት ስራው ከሌሎች የአስፋልት ስራዎች በተለየ ጥራት ባለው ሁኔታ እየተሰራ ነው፡፡

የአስፋልት ስር ንጣፍ(sub base) የተሰራው ከሌላ የመንገድ ስራ በተለየ በጠጠርና በሬንጅ ቅልቅል መሆኑን ለጥራቱ በማሳያነት ተጠቅሷል፡፡ የተለመደው የመንገድ ስራ የአስፋልት ስር ንጣፍ(sub base) የሚሞላው ከጠጠር ብቻ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኘው የመንገዱ ክፍል ላይ የፍሳሽ ትቦ ቀበራ፣ የድጋፍ ግንብ ግንባታ፣ የውሀ መውረጃ ንጣፍ፣ የአስፋልት ስር ንጣፍ (sub base) የመሳሰሉ ስራዎች በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም በተወሰነ ደረጃ የትራፊክ መጨናነቁን ማስተንፈስ ተችሏል፡፡ አሁን ላይ ያለው የፕሮጀክት አፈጻጸም 12 ነጥብ 36 ደርሷል፡፡

የወሰን ማስከበር ችግር(እንደ የቴሌ እና የመብራት የመሬት ውስጥ መሰረተ ልማት፣ የህንጻዎች፣ የቤቶችና አጥር እንዲሁም የኤሌክትሪክ ምሰሶ አለመነሳት) አፈጻጸሙን ከዚህ በላይ ማሳደግ ላለመቻሉ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ መንገዱ ከወሰን ማስከበር ነጻ ባለመደረጉ የፕሮጀክቱ ውል ከተፈረመበት ነሀሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ ነሀሴ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለስራ ተቋራጩ አስረክቦ ስራ ማስጀመር ሳይቻል መቆየቱንም ነው ኢንጂኒየር ሰውነት የገለጹት፡፡

ግንባታውን እያከናወነ የሚገኘው የይርጋለም ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ ፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ ኢንጂኒየር ገብረስላሴ ከሀሰ፤ ድርጅቱ እንደ የጠጠር መፍጫ እና የአስፋልት መስሪያ ማሽን፣ የቱቦ ማምረቻ ቦታ ወስዶ እና በቂ ዝግጅት አድርጎ በጥራትና በፍጥነት ለመስራት ወደ ስራ የገባ ቢሆንም ወሰን ማስከበሩ በፍጥነት ባለመጠናቀቁ በተደረገው ዝግጅት ልክ ስራውን ማስኬድ አልተቻለም ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከፕሮጀክቱ አጠቃላይ 5 ነጥብ 67 ኪሎ ሜትር ውስጥ ከወሰን ማስከበር ነጻ የነበረው መንገድ 800 ሜትር ብቻ እንደነበረና በሂደት ቀሪው ነጻ ይሆናል በሚል ወደ ስራ መግባቱን አክለዋል፡፡

ስራ አስኪያጁ አያይዘው እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኘው 3 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር የመንገዱ ሽፋን ውስጥ በቀኝ በኩል 2 ኪሎ ሜትሩ በወሰን ማስከበር ተይዟል። በሸገር ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኘው 2 ነጥብ 3 ኪሎ ሜትር የዲዛይን ክለሳ ተደርጎበት ግንቦት ወር 2017 ዓ.ም ላይ የተሰጣቸው ቢሆንም ሙሉ በሙሉ የግራና ቀኙ የቴሌኮምና የመብራት ኃይል የወሰን ማስከበር ችግሩ አልተፈታም። በዚህ ሁኔታ ጊዜው እየተራዘመ መጥቶ አሁን ላይ የግንባታ ግብአት ዋጋ እየጨመረ በመምጣቱ ስራው ላይ ጫና ፈጥሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለመንገድ መስሪያ ሶስት አራት ማሽኖችን በማስገባትና በማስወጣት ለሌላ ተደማሪ ኪሳራ ተዳርጓል፡፡ ምክንያቱም አሁን ላይ የሚቆፈርም፣ የሚሞላም፣ የቱቦ መቅበር ስራ የለም፡፡ ይህ እየተንከባለለ የመጣው ችግር ለ2018 ዓ.ም እንዳይዘልቅ ያላቸውን ስጋት በመግለጽ የሚመለከታቸው አካላት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው አፋጣኝ ምላሽ ቢሰጡ ለብዙዎች ቅሬታ ሆኖ የቆየውን ችግር መፍታት ይቻላል ሲሉ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

በታሰበው ልክ የመንገድ ስራውን ማፋጠን ባይቻልም እስካሁን ከአየር ጤና እስከ ካራ እንዲሁም ከአጃንባ መገንጠያ እስከ ወለቴ ደግነት ኮንዶምንየም ድረስ 830 ሜትር በግራ በኩል የአፈር ቆረጣ፣ የሙሌት ስራ፣ የውሀ ማፋሰሻ ቱቦዎች ቀበራ፣ የድልድይ ስራ ተከናውኗል። በፕሮጀክቱ ከሚገኙ 9 አነስተኛ ድልድዮች መካከል የ4ቱ ግማሽ ክፍላቸው ተጠናቅቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአየር ጤና እስከ ካራ ነጻ በሆነው የመንገድ ክልል ውስጥ የአፈር ቆረጣ ሙሌት የተጠናቀቀባቸውን ከአስፋልት ስር በታች የሚገኘውን የመሬት ክፍል ሙሌት ስራ ተሰርቷል፡፡ የእግረኛ የሸክላ ማንጠፍ ስራም እየተሰራ ነው፡፡ ቀሪውን አስፋልት የማንጠፍ ስራ የክረምቱ ዝናብ የሚወስነው በመሆኑ የአየር ጸባዩ ደረቅ የሚሆንበት ወቅት እየተጠበቀ ነው፡፡

የመንገድ ፕሮጀክቱን በባለቤትነት የሚያሰራው የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ግንባታ ኮንትራት አስተዳደር ቡድን መሪ ኢንጂኒየር ዴሳዊ ሀዲስ የአየር ጤና ወለቴ ሱቅ - አለምገና አደባባይ አስፋልት ግንባታ መጓተት ምክንያትን አስመልክተው ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡን አስተያየት፤ “የፕሮጀክቱን ግንባታ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ማጠናቀቅ አልተቻለም። ምክንያቱም አንደኛ የወሰን ማስከበር ስራው በወቅቱ አልተጠናቀቀም። ከዚህም በተጨማሪ የሸገር ከተማ አስተዳደር ከ አለም ገና አደባባይ ወደ ሰበታ የሚሄደውን የመንገድ ክፍል አዲስ አበባ ከሚገኘው መንገድ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የዲዛይን ማስተካከያ መጠየቁ እና የክለሳ ስራው ተጠናቅቆ ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላም የሚፈርሱና መነሳት ያለባቸው የመሬት ውስጥና ከመሬት በላይ የመብራት፣ የቴሌ፣ የውሀ መሰረተ ልማት እንዲሁም አጥር እና ቤቶች ያለመነሳት ችግሮች መኖራቸው ነው፡፡ ይህን የወሰን ማስከበር ችግር ለመፍታት ከሸገር ከተማ አስተዳደር ጋር የተግባቦት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከጥራት ጋር ተያይዞም በግንባታ ወቅት የሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮችን ከስር ከስር ማስተካከያዎች እንዲደረግ እንዲሁም ኮንትራክተሩ ነጻ በሆኑ መንገዶች ላይ ቀሪ ስራዎችን እንዲያጠናቅቅ አማካሪው በቅርበት እየተከታተለ ነው፡፡

መንገዱን ነጻ አድርጎ ኮንትራክተሩ በሙሉ አቅሙ ቀሪ ስራዎችን እንዲያጠናቅቅ ማድረግ የመንገዶች ባለስልጣን ኃላፊነት ከመሆኑ አንጻር የዝናብ ወቅቱ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የሚነሱ ነገሮችን ለይቶ ለሚመለከታቸው ተቋማት በማሳወቅ ተገቢውን የክፍያ ሰነድ እንዲልኩ፣ የላኩትንም ሰነድ በመፈተሽና በማረጋገጥ ክፍያውን በመፈጸም ነጻ የማድረግ ስራ ይሰራል” ብለዋል፡፡

በባለስልጣኑ የሬጉሌተሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂኒየር ፀጋዬ ቦርሴ በበኩላቸው፣ ከአዲስ አበባ ወደ ምዕራቡ የሀገራችን ክፍል መውጫ፣ ብዙ የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት ወሳኝ መንገድ ነው፡፡ ፕሮጀክቱን በፍጥነት አጠናቅቆ ለአገልግሎት እንዲበቃ ማድረግ ያልተቻለበት ምክንያት ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች እስከዛሬ ድረስ ባለመፈታታቸው ነው፡፡ የመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት በተለይም መብራት ኃይል በመንገዱ በቀኝ በኩል የሚገኘውን የመብራት መስመር ለማንሳት የጠየቀው የካሳ ክፍያ ከነምንዛሬው የፕሮጀክቱን ግማሽ ዋጋ መጠየቁና ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ደግሞ የካሳ ክፍያውን እንዲቀንሱ ምክክር ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይህ ረጅም ጊዜ ወስዷል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ አካባቢ ማስተካከያ እንዲደረግ የተጠየቀውን የካሳ ክፍያ በመቀነሳቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በቅርቡ ክፍያውን በመፈጸም ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

“ለፕሮጀክቱ መጓተት ከወሰን ማስከበሩ በተጨማሪ የስራ ተቋራጩ የስራ አፈጻጸም ድክመት ሌላው ምክንያት ነው” ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ ነጻ የተደረጉትን ከስር ከስር አጠናቅቆ ያለማስረከብ ችግር አለበት፡፡ በዚህም ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል። የመጨረሻ አማራጭ ውለታውን ማቋረጥ ነው፤ ይህም በሂደት ቀጣይ በሚኖረው የስራ አፈፃፀም የሚታይ ይሆናል። ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ያለውን አማራጭ አሟጥጦ መጠቀም ስላለበት በዚህ ደረጃ ስራውን ሲያስኬድ ቆይቷል፡፡ የ2018 በጀት ዓመት የክረምቱ ወቅት እንደተጠናቀቀ ወደስራ በመግባት ፕሮጀክቱ ለአገልግሎት እንዲበቃ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

## ተናፋቂዎቹ... ከገጽ 10 የዞረ

አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል” ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ልክ እንደ ሽኖዬ ሁሉ አሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይና ሶለል በዓል ልጃገረዶች በአደባባይ ደምቀው የሚታዩበት በዓል መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር መምህር አስቴር ሙሉ (ዶ/ር)፣ በዓሉ ነሐሴ ሲገባ ጀምሮ ዝግጅት የሚደረግበትና ከነሐሴ 16 ቀን ጀምሮ ደግሞ እንደየአካባቢው ሁኔታ ልምድና ስርዓት የሚከናወን ነው” ይላሉ፡፡

እንደ ፎክሎር መምህሯ ገለጻ፣ የበዓሉ ክዋኔ፤ ልጃገረዶች ካላቸው የራሳቸውን፣ ከሌላቸው ደግሞ ከጎረቤቶቻቸው ወይም ከታላላቅ እህቶቻቸው በመውሰድ በተለያዩ አልባሳት፣ የፀጉር ስራ፣ ጌጣጌጦች አምረውና ተውበው የሚታዩበት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ሴቶቹ ያገባች ያላገባች፣ የታጨች ያልታጨች የሚለውን የአለባበስ ስርዓትና ባህል አስጠብቀው የሚያሳዩበት ነው፡፡

ልጃገረዶቹ ክዋኔውን የሚጀምሩት ከቤተ ክርስቲያን መሆኑን የነገሩን መምህርቷ፤ ከዚያም አመስግነው ሲመለሱ እንደየ ማህበረሰቡ ደረጃ ከትልልቅ አባቶች ቤት በመጀመር በሁሉም ቤት በመሄድ በድምቀት ያከብሩታል፡፡

በኢትዮጵያ ባህል ሴት ልጆችን ከአደጋ ከመጠበቅ፣ ስርዓት ከማስተማር፣ የወላጆችን አኗኗር እንዲማሩ ከመፈለግ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች ከቤት ውጭ ስለማያስወጧቸው እንደዚህ ክብረ በዓል ነፃነታቸውን የሚያገኙበት ቀን የለም፡፡ በዚህ ቀን በነፃነት በአደባባይ ይዘምራሉ፣ ይዘፍናሉ፣ ማህበረሰቡን ያወድሳሉ፡፡ ከማህበረሰቡም የሚሰጣቸውን ስጦታ በባህሉና ትውፊቱ መሰረት ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡበትም በዓል ነው፡፡

አሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይና ሶለል በዓል ሴቶች ለበዓሉ ሲዘጋጁ እርስ በእርሳቸው የሚመራረጡበት በመሆኑ አስተዳደራዊ ስርዓትን ይማሩበታል፡፡ አብረው ሲውሉ ደግሞ አብሮነትን፣ መቻቻልን፣ አብሮ ያገኙትን መካፈልንና የመሳሰሉትን ማህበራዊ ግንኙነቶችን ያዳብሩበታል፡፡

በዓሉ ልጃገረዶች ከቤት ባሻገር ውጭ ላይ ያለውን የአካባቢያቸውን ሁኔታ የሚያዩበት፣ በግጥሞቻቸው ውስጥ የራሳቸውን ማንነት የሚገነቡበት፣ በራስ መተማመናቸውን የሚጨምሩበት፣ የግል ፍላጎታቸውን የሚያንፀባርቁበት ክብረ በዓል በመሆኑ ነፃነታቸውን ለማወጅ ፋይዳው ከፍ ያለ ነው፡፡ ይህ የፎክሎር ሃብት ልጆቹን ለመጭው ህይወት እንዲዘጋጁና ኃላፊነትን እንዲወስዱ የሚያደርግ፣ ለወደፊት ነገሮችን የሚረዱበትንና የሚለምዱበትን መንገድ የሚያሳይ በመሆኑ ኃይማኖታዊና ባህላዊ ትውፊቱ ተጠብቆ እንዲቀጥል በማድረግ በኩል የራሱ ጉልህ ሚና እንዳለው አንስተዋል፡፡

ይህ የበዓል ክዋኔ የማህበረሰቡ ማንነት፣ ስነ ልቦናው ምን እንደሚመስል የሚታይበት በመሆኑ የማህበረሰብ ማንነት የሚያስጨንቀው ማንኛውም አካል ለልጆች መሰረታዊ የሆኑትን ነገሮች በማስጨበጥ እና ኃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቱን በማስቀጠል ተልዕኮውን እንዲወጣ ሲሉ አደራ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

ሁለቱ ምሁራን እንደገለጹት በዓላቱ የሴቶችን ነጻነት ከማጎናጸፍ አንጻር አበርክቷቸው ትልቅ በመሆኑ አጠንክሮ ማስቀጠል ከሚመለከታቸው አካላት ይጠበቃል መልዕክታችን ነው፡፡

## ተሻጋሪው... ከገጽ 16 የዞረ

አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎት የሚገልፅ ውል ከተፈራረሙ በኋላ በኃላፊነት ወስደው ያለሙ፡፡ በተዋረድ ያለው የስራ ክፍልም በቼክ ሊስት ይገመግማል፡፡ ያልፀደቁ የደረቁ ችግኞችን በባለቤትነት ሲንከባከብ የነበረው አካል መልሶ ችግኙ ወደነበረበት አረንጓዴነቱን እንዲያስጠብቅ ይደረጋል፡፡ ኃላፊነት ወስዶ የሚንከባከበው አካል የገጠመውን ችግር መነሻ በማድረግ በሙያተኞች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ጠንከር ያለ ግብረ መልስ እንደሚሰጥ ጭምር አቶ ሲሳይ አስታውቀዋል፡፡

ዳይሬክተሩ አክለውም፤ “የችግኞች የፅድቀት ምጣኔ ላይ ከወትሮው በተለየ አግባብ ለመስራት የታቀደ መሆኑን ተከትሎ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት የሚሰጡ ባለሙያዎች ሳይት ድረስ እየሄዱ ቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋሉ። ከዚህ በተጨማሪም ከስራችን ጋር በቀጥታ የሚገናኙ የትምህርት ዘርፍ ስልጠናዎችን ለማህበራት፣ ለግለሰቦች ብሎም ለተቋማት ይሰጣል፡፡ ከቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተዛማጅነት ያላቸው በመሆኑ የምርጥ ዘር ምርጫችን ምን መሆን እንዳለበት፣ ችግኞችን እንዴት ማፍላት እንደምንችል፣ የችግኝ አተካከል ቅደም ተከተል ሂደቶችን እንዲሁም የቦታ አጠቃቀም ምን መሆን እንዳለበት ሳይንሳዊ አሰራርን በተከተለ አግባብ ማህበረሰቡ ዘላቂነት ያለው ስራ እንዲሰራ በትኩረት የምንከታተለው ጉዳይ ነው” ብለዋል፡፡

አዲስ አበባን በማስተር ፕላኑ መሰረት አረንጓዴ የማድረጉ ሂደት ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት አቶ ሲሳይ፣ ተቋማት ብሎም ግለሰቦች የተከሏቸውን ችግኞች የመኮትኮት፣ የማረም ብሎም አስፈላጊውን እንክብካቤ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ችግኞቹም በእንስሳት እንዳይጠፉ እንዲሁም በግለሰቦች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ከደንብ ማስከበር ጋር በመሆን የደንብ ጥሰቱን ለመከላከል እንደሚሰራ አስረድተዋል፡፡

## የጨረታ ማስታወቂያ ለተጫራቾች

### የጨረታ ቁጥር 1

ተስፋ የመዝናኛ አገልግሎት አ.ማ አቃቂ ቃሊቲ ወረዳ 08 በሚገኘው ቦታ ላይ አጠቃላይ የጊቢውን አቀማመጥ የሚያሳይ ማስተር ፕላን በመስራት እንዲሁም የሁሉንም ህንጻዎች ኢንጅነሪንግ ዲዛይን ሰርቶ በሚመለከተው የመንግስት አካል ግንባታ ፍቃድ ለማዉጣት በህንጻ ምህንድስና ዘርፍ ደረጃ 1 አማካሪዎችን በጨረታ አወዳድሮ ለማሰራት ይፈልጋል።

ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ብቁ የሆኑ አማካሪዎችን ስራውን ለማከናወን ጨረታውን እንዲሳተፉ ይጋብዛል።

1. ተጫራቾች የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ተመዝጋቢ የሆኑ፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ በጨረታዎች ለመሳተፍ ፈቃድ ያላቸው እና ከግብር እዳ ነጻ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል።
2. የፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜ ዉል ከተፈረመበት ቀን አንስቶ በአጠቃላይ በ45 የስራ ቀናት ውስጥ ይሆናል።
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 8 የስራ ቀናት ዉስጥ በአቅራቢያቸው ከሚገኝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ የማይመለስ አንድ ሺ ብር (1000.00 ብር) በሂሳብ ቁጥር 100037406608 ለተስፋ የመዝናኛ አገልግሎት አ/ማ የዲዛይን ጨረታ በሚል ገቢ በማድረግና የከፈሉበትን የገቢ ደረሰኝ ኮፒ (Deposit Slip Copy) በመያዝ ሰነዱን በተጠቀሱት ቀናት በስራ ሰዓት ከቢሮዋችን ማግኘት ይችላሉ፡፡
4. በጨረታው የሚካፈል ማንኛውም ተጫራች ለሚጫረትበት ሃምሳ ሺህ ብር (50,000.00 ብር) የጨረታ ማስከበሪያ (Bid Bond) የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ (CPO) በተስፋ የመዝናኛ አገልግሎት ስም ማስያዝ ይኖርበታል።
5. ተጫራቾች በጨረታው ደንብ መሠረት የመጫረቻ ሠነዳቸውን (ቴክኒካልና ፋይናንሻል) ዋናውን እና ኮፒውን በኤንቨሎፕ አሽገው ለተስፋ የመዝናኛ አገልግሎት ጽ/ቤት ክፍል በስምንተኛው የስራ ቀን እስከ ረፋዱ 4፡00 ሰዓትድረስ ብቻ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዉስጥ ገቢ ማድረግ አለባቸው። ጨረታው ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት በማህበሩ ቢሮ የጨረታ መክፈቻ ቦታ በተመሳሳይ ቀን ከቀኑ4፡30 ሰዓት ይከፈታል።

**ለተጨማሪ ማብራሪያ፡-** የተስፋ የመዝናኛ አገልግሎት አ/ማ 0913076780/0777076780

አክሲዮን ማህበሩ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ተስፋ የመዝናኛ አገልግሎት አክስዮን ማህበር**

---

እነ ወ/ሮ ሊያ ረታ ገብረአምላክ /2ሰዎች/ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 ነዋሪ የሆኑት የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር 2/2/1137/01 የሴሪ ቁጥር 07228427 በቀን 28/02/2016ዓ.ም ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለው/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትክ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090703599 የሆነው በአቶ ቢኒያም በለጠ አዲስ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ/ የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 06/12/2017 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ሰርተፍኬት /ካርታ/ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ90(ዘጠና) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ አዚዛ ሀይደር አስፋው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 030729 ሴሪ ቁጥር 014180 የቦታው ስፋት 287 ካሬ ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትክ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር MK-B13-00--454 በአቶ ለወየ ታደለ አረጋኸኝ ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA0000913000091300454 ሴሪ ቁጥር C 047248 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 13/12/2017 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ90 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ ከበደ መንግስቱ ወ/ማርያም ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) AA000080109694 የሆነው ካርታ የሴሪ ቁጥሩ 0102098 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አዳነ ሀይሌ ዘለቀ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ መለያ ቁጥር AA0000610072581740222 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በሰለሞን ተፈራ አራጌ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061201251 ሴሪ ቁጥር R 035420 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

መሐመድ ሱለይማን ኢሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ካርታ ቁጥር ቦሌ12/227/86-3844/00 ሴሪ ቁጥር 008763 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሙሉሀይልሽ ታረቀኝ አለሙ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ ወረዳ 1 የሚገኘው የይዞታ/ የቤቱ/ ልዩ መለያ /ካርታ/ ቁጥር AA0000801031051820003 ሴሪ ቁጥር C 226259 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ / ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ ሀና አሸናፊ ሃይሉ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090306118690322 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በ12/12/2017 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ ወ/ት እነ ሄኖክ አሰፋ እና መቅደስ መዝገቡ የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ቀበሌ - ወይም በቀድሞው ወረዳ - ቀበሌ - የቤት ቁጥር - የካርታ ቁጥር የካ/195061/08 ሴሪ ቁጥር 0134317 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ።**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በወረዳ 13 በ ዘውዲቱ በቀለ እጅጉ ስም የተመዘገበ የይዞታው ልዩ መለያ ቁጥሩ AA000051305670 የተሰጠበት ቀን 09/05/2009 ዓ.ም እና ሴሪ ቁጥር R 001648 የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፖ/ለ/ቀ/15/1402/17 በቀን 14/12/2017 ዓ.ም የሚገልጽ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ ባይ በ90 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች በምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የቅጥር ማስታወቂያ

## የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የሀብት አስተዳደር ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 1 | የሰራተኛ የስፖርት ክለቦች አስተባባሪ | VIII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በስፖርት ሳይንስ ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ | ስ/18.868 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| 2 | የሰው ሀይል ስልጠናና ልማት ባለሙያ | VII | ቢ.ኤ/ ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በሰው ኃብት ሥራአመራር፣ በማኔጅመንት፣ በህዝብ አስተዳደር፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ | ስ/18.873 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. 2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. 3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. 4. የምዝገባው ቀን ከነሐሴ 19 ቀን 2017 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ
5. 5. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
6. 6. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

---

አዲሱ ገነቱ ገዳሙ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000061400206051307 ሴሪ ቁጥር R 0622543 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ አስተዳደር ውስጥ ቱሉ ዲምቱ 2 ሳይት ህንፃ ቁጥር ቢ376 የቤት ቁጥር በ376/19 በካርታ ቁጥር 034260 በሴሪ ቁጥር 13332 በ ወ/ሮ ሎሚ ከበበው ብርሃኑ የተመዘገበ ኮንደሚኒየም ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ20 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አ/ቶ/ ሰላምሰው ጥላሁን ወርቁ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) 01/90/9851/00 የሆነው ካርታ የሴሪ ቁጥሩ 033554 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 589 በወ/ሮ መሰረት ተስፋዬ ወልደየስ ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር (ካርታ ቁጥር) AA000020201168 በቀን 08/05/2016 ሴሪ ቁጥር 0200538 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 14/12/2017 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ90 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የአቶ ገዛኸኝ ገብሬ ድረታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ12/47/2/2/22259/109402/01 ሴሪ ቁጥር 035378 ተመዝግቦ የነበረው ኦሪጅናል/ ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 20 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ለይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የአቶ ጌታቸው ከበደ ታዬ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር - ካርታ ቁጥር K16/01-9-56-80/2532/01 በሴሪ ቁጥር 0645140 የተሰጣቸው ካርታ በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ20 ቀን ውስጥ ጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ማህደሩ እና ካርታው /ደብተሩ/ እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የአቶ ጌታቸው ከበደ ታዬ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር - ካርታ ቁጥር K16/01-9-56-80/2532/01 በሴሪ ቁጥር 0645140 የተሰጣቸው ካርታ በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ20 ቀን ውስጥ ጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ማህደሩ እና ካርታው /ደብተሩ/ እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር ውስጥ ቱሉ ዲምቱ በካርታ ቁጥር 034286 በሴሪ ቁጥር 134602 በ አቶ እድሪስ ዴካ ቢፍቱ የተመዘገበ ኮንደሚንየም ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ20 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ለአትሌቲክሱ ፍትሐዊነት የቴክኖሎጂ ሚና




ፎቶ- ከገፀ ድር
ለአትሌቶች ውጤታማነት ተጨማሪ አቅም ከሚፈጥሩ ቴክኖሎጂዎች ጥቂቶቹ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የአትሌቲክስ ስፖርትን ጨምሮ በየትኛውም ስፖርታዊ ውድድር ፍትሐዊነት ዋነኛው ምሰሶ ነው። የሰው ዐይን ብቻውን ሊያየው የማይችለውን ትንሹን ቅጽበት፣ የጥቂት ሚሊ ሜትር ርቀትንና የውድድሩን ህግጋት መጣስ በትክክል ለመለየትና ፍትሐዊነትን ለማስፈን ደግሞ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በስፖርት ውስጥ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከቀላል የሰዓት መለኪያ መሣሪያዎች ተጀምሮ ዛሬ ባለው ውስብስብ የዲጂታል ዘመን የውድድሩ ዋነኛ አካል ሆኗል።

ምንም እንኳን ቴክኖሎጂዎች የሰውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ባይተኩም የቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ መዋል የውድድሮችን ፍትሐዊነት ከፍ ከማድረጉም በላይ የአትሌቶችን አፈጻጸም ለመተንተን እና ለማሻሻል እየተሰጡት ያለው ጥቅም ቀላል አለመሆኑን የዓለም አትሌቲክስ መረጃ ያሳያል፡፡ እንደዚሁም አሰልጣኞች እና አትሌቶች በውድድሩ ወቅት ስህተቶቻቸውን በመመልከት አፈጻጸማቸውን ለማስተካከል ይረዳቸዋል።

በስፖርታዊ ውድድሮች ላይ በጣም ቀላልና መሰረታዊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን አገልግሎት ላይ ማዋል ከተጀመረ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። በስፖርት ውስጥ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የመጀመሪያዎቹ እርምጃዎች መካከል የሩጫ ሰዓቶች፣ ፎቶ ፊኒሽ (Photo-Finish) እና ኤሌክትሮኒክ የውጤት ሰሌዳዎች (Electronic Scoreboards) በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡

የውድድሩን ፍፃሜ በትክክል ለመለየት በ1881 በፈረስ እሽቅድምድም ላይ የመጀመሪያው ፎቶ ፊኒሽ ቴክኖሎጂ እንደተሞከረ መረጃዎች ያሳያሉ። ከዚያ በኋላም በተለይ በአጭር ርቀት ሩጫዎች ላይ የፍጻሜውን መስመር ማን እንደቀደመ ለመለየት ጥቅም ላይ ውሏል። እ.ኤ.አ በ2016ቱ የሪዮ ኦሊምፒክ የ400 ሜትር የሴቶች ሩጫ ላይ አሊሰን ፊሊክስ እና ሻውኔ ሚለር በፍጻሜው መስመር ላይ በደረሱበት ቅጽበት አሸናፊውን ለመለየት የተቻለው ፎቶ ፊኒሽ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ነበር፡፡ በኦሎምፒክ ጨዋታዎች ላይ እንደዚሁ እ.ኤ.አ በ1912 ስቶክሆልም ኦሎምፒክ ላይ በ1 ሺህ 500 ሜትር ሩጫ ላይ ኤሌክትሮኒክ የውጤት ሰሌዳዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ከእነዚህ የመጀመሪያ እርምጃዎች በኋላ ቴክኖሎጂ በየጊዜው እያደገ መጥቶ እ.ኤ.አ በ1963 ለመጀመሪያ ጊዜ የቴሌቪዥን በቅጽበት ዳግም ማሳያ (Instant Replay) ተጀመረ። በ1970ዎቹ ደግሞ የልብ ምት መለኪያ እና ሌሎች የአትሌቶች እንቅስቃሴን የሚከታተሉ ቴክኖሎጂዎች ለስልጠና መዋል ጀመሩ። አሁን ላይ ግልጋሎት እየሰጡ ያሉት የጂፒኤስ መከታተያዎች፣ የቪዲዮ ዳኛ (VAR) እና ሌሎች ውስብስብ ቴክኖሎጂዎችም የዚያ ሂደት ውጤቶች ስለመሆናቸው ከአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ (IAAF) ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት የውድድር መጀመሪያ ላይ የተሳሳተ ጅማሬ (false start) መሆኑን የሚወስኑት የሰው ዳኞች ብቻ ነበሩ። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ምላሽ ከ0 ነጥብ 100 ሰከንድ በታች ሊሆን ስለማይችል፣ አንድ አትሌት በዚያ ፍጥነት ከተነሳ የሰው ዳኛ ለመወሰን ይቸገራል። ዘመናዊው የኤሌክትሮኒክስ ዳሳሽ (Electronic Sensor) ቴክኖሎጂ ግን ይህንን ስህተት አርሟል። ይህ ቴክኖሎጂ አትሌቱ በጀማሪው ብሎክ ላይ የፈጠረውን ኃይል የሚለካ ሲሆን፣ ጥይቱ ከመተኮሱ በፊት የሚፈጠር ማንኛውም እንቅስቃሴ በቅጽበት ይለያል። በዚህም ምክንያት የውሸት ጅማሬ ለመፈጸም ከ0 ነጥብ 100 ሰከንድ ባነሰ ጊዜ ውስጥ የተነሳ አትሌት ቴክኖሎጂው በማሳወቁ ከውድድር ሊሰረዝ ይችላል። በዚህ መንገድ የቴክኖሎጂው መረጃ በሰው ዳኞች ሊፈጠር ይችል የነበረውን ስህተት አርሞ ፍትሐዊነትን ያረጋግጣል።

በቅርቡ በሚካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ ፍትሐዊነትን ለማሳደግ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ተስፋ ተጥሎባቸዋል። የካሜራ ዳሳሾች (Cameras and Sensors) አንዱ ሲሆን፣ ውድድሩን ከሁሉም አቅጣጫ ለመቅረጽ የሚያስችሉ ካሜራዎች እየበዙ ይገኛሉ። ይህም ዳኞችን በውድድሩ ወቅት ለሚፈጠሩ ጥቃቅን ውሳኔዎች ለመርዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትና በከፍተኛ ዝላይ (High Jump) እና የረዥም ዝላይ (Long Jump) ውድድሮች ላይ የአትሌቱን አፈጻጸም በትክክል ለመለየት ያገለግላል ተብሎ ይጠበቃል።

የተሻሻለ የፎቶ ፊኒሽ ቴክኖሎጂ (Improved Photo-Finish Technology) እንደዚሁ አዳዲስ የፎቶ ፊኒሽ ሲስተሞች ከበፊቱ በበለጠ ከፍተኛ ጥራት ባለው ፍሬም ሩጫዎችን ለመመዝገብ ይችላሉ። ይህ በቅጽበት የተሻሉ ምስሎችን በመያዝ ትክክለኛ ውጤት ለመስጠት ይረዳል ይላሉ የአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ ቴክኒካል ቡድን አባሉ አይ ጉዬ።

በእርግጥ በአትሌቲክስ ውድድሮች ወቅት አወዳዳሪው አካል ብቻ ሳይሆን አትሌቶችም የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ በአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ አትሌቶች የሚጠቀሟቸው ቴክኖሎጂዎች በዋነኛነት ለስልጠና እና ለአፈፃፀም ብቃት ማሻሻያ የሚያገለግሉ ሲሆን፣ በውድድሩ ወቅት ደግሞ የውድድሩን ህግጋት ከጠበቁ ቴክኖሎጂዎች ብቻ ይጠቀማሉ።

አትሌቶች ስማርት ሰዓቶችና የመከታተያ መሳሪያዎችን (Fitness Trackers and GPS Watches) ተጠቅመው የአትሌቱን የልብ ምት፣ የሩጫ ፍጥነት፣ የተጓዘበትን ርቀት፣ የእንቅልፍ ጥራት እና ሌሎች የጤና መረጃዎችን ይመዘግባሉ። ይህ መረጃ አሰልጣኞች ለአትሌቱ ትክክለኛውን የስልጠና መርሃ ግብር እንዲያዘጋጁና የድካም ደረጃውን እንዲገመግሙ ይረዳቸዋል።

አትሌቶች የሩጫ ቴክኒካቸውን፣ የዝላይ አቀማመጣቸውን ወይም የውርወራ እንቅስቃሴያቸውን በዝግታ በመመልከት ስህተቶቻቸውን በቀላሉ ለማረም የሚረዳው ሌላኛው ቴክኖሎጂ የቪዲዮና የ3ዲ እንቅስቃሴ ትንተና ነው፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ የአካል ክፍሎች እንቅስቃሴን ከሁሉም አቅጣጫ ስለሚቀርጽ፣ አትሌቶች ትክክለኛውን እንቅስቃሴ በመማር የአፈጻጸም ብቃታቸውን ከፍ ያደርጋሉ።

አንዳንድ አትሌቶች በስልጠና ወቅት ሰውነታቸው ኦክሲጅንን እንዴት እንደሚጠቀም ለመረዳት የመተንፈሻ መሳሪያዎች ይጠቀማሉ። ይህም የመተንፈስ ችሎታቸውን ከፍ ለማድረግ እና በውድድር ወቅት ድካምን ለመቋቋም ይረዳቸዋል።

በውድድር ህጎች መሰረት አትሌቶች የሚፈቀድላቸውን ቴክኖሎጂዎች ብቻ መጠቀም ይችላሉ። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ እና የውድድሩን ህግጋት ለመጠበቅ ወሳኝ ናቸው። በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ህግ መሰረት የተሰሩ የስፖርት ጫማዎች ይፈቀዳሉ። እነዚህ ጫማዎች በአብዛኛው ከካርቦን ፋይበር የተሰሩና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች ሊኖራቸው ይችላል። ይሁንና የጫማው ውፍረት እና የሰሌዳው አይነት በህግ ቁጥጥር ስር ናቸው። በተለይም በቅርብ ዓመታት ውስጥ የተሰሩት ዘመናዊ ጫማዎች፣ ከዚህ ቀደም ከነበሩት በተለየ መልኩ የአትሌቶችን አፈጻጸም በእጅጉ የሚያሻሽሉ መሆናቸው ተረጋግጧል። ይህ ቴክኖሎጂ አትሌቶች ክብረ ወሰን እንዲሰብርና ፈጣን ሰዓቶችን እንዲያስመዘግቡ በመርዳት ላይ ይገኛል።

የቴክኖሎጂው እድገት አትሌቲክስን የበለጠ ፍትሐዊ ለማድረግ ለዓለም አትሌቲክስ ፌዴሬሽን (World Athletics) ፈተና ሆኖበታል። በመሆኑም ፌዴሬሽኑ አትሌቶች የሚለብሷቸውን ጫማዎች በተመለከተ የሚከተሉትን ህጎች አውጥቷል። ለየሩጫው ርቀት የጫማው ውፍረት ከፍተኛ ገደብ ተጥሎበታል። ለምሳሌ፣ ለጎዳና ላይ ውድድሮች (ማራቶን) የጫማው ሶል ውፍረት ከ40 ሚሊ ሜትር መብለጥ የለበትም። ለትራክ ውድድሮች ደግሞ ውፍረቱ ከ20 እስከ 25 ሚሊ ሜትር መብለጥ የለበትም።

በመጪው በቶኪዮ 2025 የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ በርካታ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ የሚድጉ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ ዋነኞቹ የውድድሩን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ እና ለተመልካች የተሻለ የውድድር ልምድ ለማቅረብ የሚውሉ ናቸው። የሻምፒዮናው ይፋዊ ቴክኖሎጂ አጋር የሆነው ሶኒ (Sony) እና ሌሎች አጋሮች በመተባበር የሚያቀርቧቸውን ቴክኖሎጂዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

ሃውክ-አይ ኢኖቬሽን የሶኒ ንዑስ ኩባንያ ሲሆን፣ የቪዲዮ ዳኝነት ስርዓቱን በሁሉም የትራክ እና የሜዳ ውድድሮች ላይ ይዘረጋል። ይህ ሲስተም ለዳኞች ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ የቪዲዮ ምስሎችን በማሳየት ፍትሐዊ እና ትክክለኛ ውሳኔ እንዲሰጡ ይረዳል። ለምሳሌ ያህል፣ በዝላይ ውድድሮች ላይ የአትሌቱን አፈጻጸም፣ በሩጫ ውድድሮች ላይ ደግሞ የውሸት ጅማሬ (False Start) መኖሩን ለመወሰን ያግዛል ተብሎለታል።

የሻምፒዮናው ቀረጻ የሚካሄደው አልፋ (Alpha™) በተሰኙ መስታወት አልባ ካሜራዎች እና ጂ ማስተር (G Master™) ሌንሶች ነው። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች የአትሌቶችን እንቅስቃሴ በሲኒማ ጥራት ለመቅረጽ እና በቅጽበት ለስርጭት ለማቅረብ ያስችላሉ። ይህም የአትሌቶቹን ድንቅ እንቅስቃሴዎች በቅርበት እና በግልጽ እንዲያዩ ይረዳል የተባለው ቴክኖሎጂ በተግባር ላይ እንደሚውል ተገልጧል።

በአጠቃላይ የአትሌቶች የመሮጫ ጫማ ቴክኖሎጂ ፍጥነትን እና ብቃትን በማሳደግ በስፖርቱ ላይ ትልቅ ለውጥ አምጥቷል። ሆኖም የፌዴሬሽኑ ህጎች ይህ ቴክኖሎጂ ከአትሌቱ የራሱ ተሰጥኦና ጥረት በላይ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ለመቆጣጠር ይረዳሉ።